# የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት፡የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ
## መደበኛ እትም

# የሐዋሪያት ስራ

የትምህርቱ አዘጋጅች፡ ዊልሰን ፓሮሺ

ትርጉም ፡- ብሩክ ፈለቀ
በረከት ፈለቀ

ይህ የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ የሚዘጋጀው በሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ዋና መስሪያ ቤት በሆነው በጀነራል ኮንፍረንስ ውስጥ ሆኖ፤ የጎልማሶች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያን በሚያዘጋጀው ቢሮ ነው፡፡ መምሪያዎቹ የሚዘጋጁት የጀነራል ኮንፈረንስ አስተዳደር ኮሚቴ ንዑስ ኮሚቴ በሆነውና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያዎችን በሚያሳትመው የሰንበት ትምህርት ሕትመት ቦርድ ነው፡፡ የታተመው መምሪያ በውስጡ ዓለም አቀፋዊ የሆነ የምዘና ኮሚቴ ሀሳቦችንና የሰንበት ትምህርት ሕትመት ቦርድን ማረጋገጫ ስለሚያንጸባርቅ የአዘጋጁን (የአዘጋጆችን) ሀሳብ ብቻ የሚወክል አይደለም፡፡ በተለየ ካልተጠቀሰ በቀር በዚህ ሰንበት ትምህርት ጥቅም ላይ የዋሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው፡፡

በኢትዮጵያ አድቬንቲስት ማተሚያ ቤት ታተመ

3ኛ ሩብ ዓመት

ከሰኔ 23 2010 - መስከረም 18 2011 ዓ.ም

# ማውጫ


| አርዕስት | ቀን | ገጽ |
|---|---|---|
| 1.ምስክሮቼ ትሆናላችሁ | ሰኔ 23 - 29 | 5 |
| 2. ጴንጤቆስጤ | ሰኔ 30 - ሐምሌ 6 | 14 |
| 3. ህይወት በቀዳሚዋ ቤተክርስቲያን | ሐምሌ 7 - ሐምሌ 13 | 22 |
| 4. የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን መሪዎች | ሐምሌ 14 - ሐምሌ 20 | 30 |
| 5. የጳውሎስ መለወጥ | ሐምሌ 21 - ሐምሌ 27 | 38 |
| 6. የጴጥሮስ አገልግሎት | ሐምሌ 28 - ነሐሴ 4 | 47 |
| 7. የጳውሎስ የመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ጉዞ | ነሐሴ 5 - ነሐሴ 11 | 55 |
| 8. የኢየሩሳሌም ጉባኤ | ነሐሴ 12 - ነሐሴ 18 | 64 |
| 9. የጳውሎስ ሁለተኛ ሚስዮናዊ ጉዞ | ነሐሴ 19 - ነሐሴ 25 | 73 |
| 10. ሦስተኛው ሚስዮናዊ ጉዞ | ነሐሴ 26 - ጳጉሜ 2 | 82 |
| 11. በኢየሩሳሌም መታሰር | ጳጉሜ 3 - መስከረም 4 | 92 |
| 12. በቄሳርያ መታሰር | መስከረም 5 - መስከረም 11 | 102 |
| 13. ጉዞ ወደ ሮም | መስከረም 12 - መስከረም 18 | 111 |

# የወንጌል ጽል አጽራጊነት

ብዙ የታሪክ ጠበብት እንደሚያምኑበት ከሆነ የአለማችን ታሪክ ሶስት ወሳኝ አስርት አመታት የነበሩት በብዛት አይሁዳዊ የሆኑና ጥቂት ቁጥር ያላቸው ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት ወንጌልን ለአለም ያዳረሱበት ጊዜያትናቸው፡፡ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እነዚያን ከኢየሱስ ትንሳኤ አንስቶ (ከክ.ል. በኋላ 31 ዓ.ም.) እስከ መጀመሪያው የጳውሎስ በሮም እስር ቤት መግባት 62 ዓ.ም. (ሐዋ.28:30) ድረስ ያሉትን ወሳኝ ሶስት አስርት አመታት ያስቃኘናል፡፡ መጽሐፉ ታሪኩን የሚያበቃው በዚህ ወቅት ስለሆነ የተጻፈው ከታሠረ ጥቂት ጊዜያት በኋላ ነው ማለት እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ሌሎች ማስረጃዎች እንደሚያመላክቱት ከሆነ ጳውሎስ ከጥቂት አመታት በኋላ በድጋሚ በሮም ተይዞ እስኪታሰርና በኋላም በ67 ዓ.ም እስኪሞት ድረስ ከመጀመሪያው እስር ተፈትቶ የወንጌል አገልግሎቱንና ስብከቱን በተለያዩ ስፍራዎች በመጓዝ ቀጥሎ ነበር፡፡

ስለ መጽሐፉ ደራሲ መጽሐፉ የሚለን ነገር ባይኖርም የቤተክርስትያን ትውፊቶች ግን «የተወደደው ሐኪም» ተብሎ በቆላስያስ 4፡14 የተጠቀሰውና ከጳውሎስ ጋር አብሮ የተጓዘው (2ጢሞ. 4፡11፤ ፊሊሞና 24) ሉቃስ ስለመሆኑ ይናገራሉ፡፡ አዎን ያለ ጥርጥር ሉቃስ ከወንጌል መጽሐፍት ውስጥ ሦስተኛውን ስለመጻፋም ይታመናል፡ ፡ በሐዋ.1፡1 ላይም «ቀደም ያለው መጽሐፉን» ጠቅሷል (ከሉቃስ 1፡3 ጋር ያነፃጽሩ) ፡፡ የሉቃስና የሐዋሪያት መጽሐፍት በክርስትና ጅማሮ ውስጥ በተለይ ስለ አነሳሱና (ስለ የሱስ ህይወት እና አገለግሎት) እና ስለ ወንጌሉ መስፋፋት (የሐዋሪያት የወንጌል እንቅስቃሴን) የሚገልፁ መንታ የሆኑ ጥራዝ መጽሐፎች ናቸው፡፡

ሁለቱም መጽሐፎች በአንድነት ከአዲስ ኪዳን መጽሐፎች 27 በመቶ የሚሆነውን ክፍል የሚሸፍኑ ሲሆን ይህም ከአንድየመጽሐፍ ፀሐፊየተበረከተ ትልቁ አስተዋጽኦ ሆኗል፡፡ጳውሎስ ለቆላስያስ ሰዎች ሲጽፍ ሉቃስን የገለጸው እንደ አህዛብ የሥራ አጋሩ አድርጎ ስለሆነ እርሱ «ያልተገረዘ» ነበር (ቆላ.4፡7-14) ፡፡ ስለዚህ ሉቃስ ከአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ደራሲያን ሁሉ አይሁዳዊ ያልሆነ ግለሰብ ነው ማለት ነው፡፡

ይህም ከርሱ ዋነኛ ፍሬ ሀሳቦች መካከል የሆነውን ይገልጻል፤ ያም የድነትን አለማቀፋዊነት፡፡እግዚአብሔር ለማንም አያደላም፡፡ቤተክርስቲያን የተጠራችው ዘር፤ የአኗኗር ደረጃን እና ጾታን ሳትለይ ለሁሉም እንድትመሰክር ነው (ሐዋ.1፡8፤2፡21፤39-40፤3፡25፣10፡28፣34-35) ፡፡ በጭፍን ጥላቻ ወይም በመመቻቸት ይህንን ማድረግ ካልቻለች ወንጌል የተዛባ ይሆናል፤ ይህ ደግሞ ከእግዚአብሄር ቃል መሠረታዊ እውነት ጋር ተፃራሪ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ሁላችን አንድ ነን፤ በየሱስ ክርስቶስ መዋጀት የሚያሻን ኃጢያተኞች፡፡

የሉቃስ ዋንኛ ጀግናው ጳውሎስ መሆኑ ባጋጣሚ የሆነ ነገር አይደለም፡፡ «የአህዛብ ሐዋሪያ» (ሮሜ11፡13) እንደመሆኑ ወደ ሁለት ሶስተኛ የሚጠጋው የሐዋሪያት ስራ መጽሐፍ የተጻፈው ስለ ጳውሎስ ነው፡፡

በሐዋሪያት ስራ የተካተቱ ሌሎች ወሳኝ ፍሬ ሀሳቦች ስለ እግዚአብሔር ሉአላዊነት እና ስለ መለኮታዊ እቅዱ (ሐዋ.17፡24-25፤20፡27፤23፡11) የሱስ እንደ ጌታና አዳኝ ስለ መክበሩ (ሐዋ.2፡32፤36፤3፡13-15፤4፡10-12፤5፡30-31) ቤተክርስቲያን ላላት ተልዕኮ መንፈስ ቅዱስ በማጠንከርና በመምራት ስላለው ሚና (ሐዋ.2፡1-4፣4፡24-31፣8፡14-17፣29፣39፣ 10፡19-20) የቀደምቷ ቤተክርስቲያን ስኬት የሰብአዊ ዘር ጥበብና ችሎታ ውጤት ባይሆንም ሌሎች ሐዋሪያት ማድረግ ያልቻሉትን እንደ ጳውሎስ ባለ ሰው ትልቅ ተጽእኖ በአለም ላይ መፍጠሩ እግዚአብሄርን አስደስቶታል (1ቆሮ. 15፡10) ፡፡

የሐዋሪያት ስራ መጽሐፍ ስለ ቀዳሚዋ ቤተክርስቲያን መደራጀት፣ስለ አስተደዳራዊ ጉዳይ ብሎም ስለ መለኮታዊ እድገትዋ ያወሳል፡፡ ለአብነት ያህል ይህን የምናገኘው ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጻት ቀን፤ በአህዛብ መዳን ሁኔታ እና እምነት በመዳን ጉዳይ ያለው ሚናን በተመለከተ የተነሱ ጥያቄዎችን በመለሱበት ሁኔታ ነው፡፡በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ቀዳሚዋ ቤተክርስቲያን ያገኘችው ስኬት ልባቸውን በጸሎት አዋርደው፣ ልዩነታቸውን ሁሉ ጥለው መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲጠቀምባቸው ሲፈቅዱ በነርሱ ውስጥ እግዚአብሔር ማድረግ የሚችለውን ነገር ማሳያ ነው፡፡

የሐዋሪያት ስራ መጽሐፍ በእግዚአብሔር ስም የተጠሩት የወንጌሉን ስራ ስለ መጀመራቸው ያወሳል፡፡ እኛስ በእርሱ ስም የተጠራን ስራውን ለመጨረስ ከእነርሱ ታሪክ የምንማረው ምን ነገር አለ?

ዊልሰን ፓሮሺ በኢንጌንሄሮኮኤልሆ ሳኦፖሎ ብራዚል በሚገኘው የአድቬንቲስት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በአዲስ ኪዳን መፅሀፍ አተረጓጎም ፕሮፌሰር ናቸው፡፡ በአንድሪውስ ዩኒቨርሲቲ (2004እ.ኤ. አ) በአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ላይ ፒ.ኤች. ዲያቸውን ሰርተዋል፡ ፡ የድህረ ዶክትሬት ጥናታቸውን ደግሞ በሄደልበርግ ዩኒቨርሲቲ ጀርመን (2011 እ.ኤ.አ) አጠናቀዋል፡፡

# 1ኛ ትምህርት ከሰኔ 23 - 29

# ምስክሮቼ ትሆናላችሁ

**ሰንበት ከሰአት**

ለዚህ ሳምንት ጥናት የሚከተሉቱትን ጥቅሶች ያንብቡ፡- ሐዋ.1፡6-8፣ሉቃስ 24፡25፣ ሉቃስ 24፡44-48፣ ዘዳ.19፡15፣ ሐዋ.1፡9-26፣ ምሳሌ 16፡33፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ**፡-‹‹ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌም፤ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፤ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ፡፡›› (ሐዋ.1፡8)

በምድር የነበረው የየሱስ ተልዕኮ አበቃ፡፡ እግዚአብሄር ወዲያውኑ መንፈስ ቅዱሱን በመላክ የደቀ መዛሙርቱን ስራ በድንቅና ተአምራት በማጀብና በማጠናከር እስከ አለም ዳርቻ የመድረስ ጥረታቸውን ሊያግዝ ነው፡፡ የሱስ ሁልጊዜ በስጋ አብሮአቸው መሆን አይችልም፡፡ በስጋ መገለጡ ከአለም አቀፉ ተልዕኮ አንፃር በአካል ውሱን እንዲሆን ማድረጉ እንዳለ ሆኖ መንፈስ ቅዱስ እንዲመጣ ደግሞ የእርሱ ወደ ላይ ማረግና በሰማይ መክበር አስፈላጊ ነበር፡፡

እስከ የሱስ ትንሳኤ ድረስ ደቀ መዛሙርቱ በግልጽ ይህንን አልተረዱም፡፡ ሁሉንም ነገር ትተው ሲከተሉት እርሱ የፖለቲካ ነጻ አውጪያቸው በመሆን አንድ ቀን ሮማያውያንን ከቂያቸው ጠራርጎ በማስወጣትና የዳዊትን መንግስት በሚቋቋም እስራኤልን ወደ ቀድሞ ክብርዋ ይመልሳታል ብለው ተማምነው ነበር፡፡ ከዚህ ውጪ ሌላ ነገር ማሰብ ለእነርሱ ቀላል አልነበረም፡፡

የሱስ በሐዋ. ሥራ1 ላይ በስተመጨረሻ ለደቀ መዛሙርቱ ያስተላለፈው መመሪያ ዋና ጉዳይ ይህ ነበር፡፡ የመንፈስ ቅዱስ የተስፋ ቃል የተሰጠው በዚህ አውድ (ወንጌልን በማዳረስ) ነው፡፡ ምእራፉ ስለ የሱስ ወደ ሰማይ መመለስና ቀዳሚዋ ቤተክርስቲያን ራስዋን እንዴት ለጴንጤቆስጤ ቀን እንደዘጋጀች ያወሳል፡፡

የዚህን ሳምንት ትምህርት አጥንተው ለሰኔ 30 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡

# እሁድ ሰኔ 24

## የእስራኤል መታደስ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ መሲሁ የተነገሩ ሁለት ትንቢቶች አሉ፡- አንዱ መሲሁ ንጉስ ሆኖ ለዘላለም እንደሚገዛ የሚናገር ሲሆን (መዝ.89፡3-4፣35-37፣ኢሳ.9፡6-7 ፣ህዝ.37፡25፣ ዳን. 2፡44፣ 7፡13-14) ሌላኛው ደግሞ ለአለም ህዝቦች ኃጢያት ሲል ስለሚሞተው መሲህ የሚተርከው ነው(ኢሳ.52፡13- 53፡12፣ ዳን.9፡26)፡፡ እንደነዚህ ያሉ ትንቢቶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም ፡፡ በመሲሁ አገልግሎት ውስጥ በቅደም ተከተል ስለሚከናወኑ ሁለት ክፍሎች ማለትም በቅድሚያ እንደሚሰቃይ በመቀጠል ግን ንጉስ እንደሚሆን አመላካች የሆኑ ትንቢቶች ናቸው (ሉቃስ 17፡24-25፣24፡25-26)፡፡

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩ አይሁዶች ችግር ስለ መሲሁ ይጠባበቁ የነበረው በአንዱ ገፅታ ብቻ መሆኑ ነበር፡፡ ንጉስ የሚሆነው መሲህ የፖለቲካ ነጻ አውጫቸው ሆኖ የመምጣቱ ተስፋ መጥቶ እንደሚሰቃይና እንደሚሞት ያለውን ትንቢት እንዳያስተውሉ ጋርዷቸው ነበር፡፡

ደቀ መዛሙርቱም ቀድመው የተናገሩት መሲሁ ይነግስልናል የሚለውን ሀሳብ ነበር፡ ፡ የሱስ መሲህ ስለመሆኑ በሚገባ አምነው ተቀብለዋል (ማቴ.16፡16-20) ፡፡ አልፎ አልፎም የሱስ በዙፋኑ በሚቀመጥበት ጊዜ ማን በቀኙ ወይም በግራው እንደሚቀመጥ አንስተው ይከራከሩ ነበር፡፡ የሱስ ስለሚጠብቀው የወደፊት እጣ ፈንታ በማንሳት ቢያስጠነቅቃቸውም እነርሱ ግንምን ማለቱ እንደሆነ አልገባቸውም፡፡ ስለዚህም በሞተ ጊዜ ግራ ተጋብተው እጅጉን ተስፋ ቆረጡ፡፡ በሌላ አባባል ያሰቡት እንዲህ ነበር «እኛ ግን እስራኤልን ይቤዣል ብለን ተስፋ ያደረግነው እርሱን ነበር» (ሉቃስ 24፡21) ፡፡

ሐዋ. ሥራ 1:6ን ያንብቡ፡፡ ይህ ጥያቄ እስካሁን ስላላስተዋሉት ጉዳይ ምን የሚያሳየን ነገር አለው? የሱስ በሐዋ. ሥራ 1:7 ላይ ምን ምላሽ ሰጣቸው?

---

---

የየሱስ ሞት የደቀ መዛሙርቱን ተስፋ ያመከነ እንደሆነ ቢያመላክትም ትንሳኤው ደግሞ ተስፋቸውን አነቃቅቶ በከፍተኛ ደረጃ ከፖለቲካ ጭቆና ነጻ የመውጣት ተስፋቸው እንዲያንሰራራ አደረገ፡፡ የየሱስ ትንሳኤ መሲሁ በስተመጨረሻ የራሱን መንግስት እንደሚያቋቁም ጠንካራ ማሳያ ነው ብሎ መደምደም ትክክለኛ አስተሳሰብ መሠለ፡፡

ነገር ግን የሱስ ለጥያቄአቸው ቀጥተኛ የሆነ ምላሽ አልሰጣቸውም። ከደቀ መዛሙርቱ ጥያቄ ጀርባ ስላለው ስለማይቀረው መንግስቱ መምጣት እየተቃወመ አልነበረም፣እያፀደቀውም አልነበረም። የእግዚአብሔር የጊዜ ውሳኔ የእርሱ ብቻ ስለሆነና ይህ ደግሞ የሰው ልጅ ሊደርስበት የሚችለው እውቀት ስላልሆነ ጉዳዩን በእንጥልጥል ተወው።

ሉቃስ 24፡25ን ሲያነቡ የደቀመዛሙርቱ እውነተኛ ችግር ምን ሆኖ አገኙት? መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረን በተቃራኒ እኛ ማመን የምንፈልገውን ብቻ ማመን ቀላል የሚሆንልን ለምንድን ነው? ከዚህ ወጥመድ እንዴት ልናመልጥ እንችላለን?

## ሰኞ ሰኔ 25

### የደቀ መዛሙርቱ ተልዕኮ

ሐዋ. ሥራ 1፡8ን ያንብቡ። በትንቢት የተሰጠውን ሃሳብ ለራስ ፍላጎት ከመተርጎም ይልቅ ደቀመዛሙርቱ ምን እንዲያደርጉ ነበር የታዘዙት?

__________________________________________________

__________________________________________________

በዚህ ክፍል ውስጥ ስለደቀመዛሙርቱ ተልእኮ የሚናገሩ አራት ወሳኝ ነጥቦች አሉ።

1. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፡- መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ህዝቦች መካከል ለመስራት ሁሌም ዝግጁ ነው። ነብያትም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በልዩ ሁኔታ እንደሚፈስ ተናግረው ነበር (ኢሳ.44፡3፣ ኢዩኤል 2፡28-29) ። የሱስ ራሱ ወደ ምድራዊ አገልግሎቱ ከመግባቱ በፊት በመንፈስ ቅዱስ እንደ መቀባቱ በአገልግሎቱም መንፈስ ቅዱስ በስራ ላይ ነበር (ሉቃስ 4፡18-21) ። ነገር ግን የሱስ ወደ ሰማይ እስኪያርግ ድረስ በይፋ ስራውን አልጀመረም ነበር (ዮሐ.7፡39፣ ሐዋ.2፡33) ።

2. የመስካሪው ሚና፡- ምስክርነት የአይን እማኝ ስራ ነው። ደቀመዛመርቱ ለዚህ ምስክርነት ሙሉ በሙሉ የበቁ ነበሩ (ሐዋ.1፡21-22፣ 4፡20ን ከ1ዮሐ.1፡1-3ጋር ያነፃፅሩ) ።ስለዚህ ከየሱስ ጋር የነበራቸውን የህይወት ልምምድ ለአለም እንዲያጋሩ ይህ ተልእኮ ተሰጣቸው።

3. የተልእኮው እቅድ፡-ደቀመዛመርቱ በቅድሚያ በየሩሳሌም ከዛም በይሁዳና በሰማርያ በስተመጨረሻም እስከ አለም ዳርቻ ድረስ መመስከር ነበረባቸው።

እቅዱም እየሰፋ የሚሄድ ነበር፡፡ እየሩሳሌም ለአይሁድ እምነት ማዕከላዊ ስፍራ ነበረች፤ የሱስም የተኮነነውና የተሰቀለው በዚህ ስፍራ ነበር፡፡ ይሁዳና ሰማርያ ደግሞ የሱስ ሄዶ ያገለገለባቸው የጎረቤት ክልሎች ነበሩ፡፡ ደቀመዛመርቱ በነዚህ ስፈራዎች ብቻ እንዲወሰኑ አልተጠሩም፤የተልእኳቸው ጥግ መላው አለምን የሚያዳርስ ነውና፡፡

4. የተልእኮው አካሄድ ፡- በብሉይ ኪዳን ጊዜ ሌሎች ሕዘቦች ወደ እግዚአብሄር እንዲመጡ ይጠበቅባቸው ነበር (ኢሳ. 2፡1-5ንይመልከቱ) ፤ እስራኤላውያን አልነበሩም እግዚአብሄርን ወደ ሌሎች ህዝቦች «የሚወስዱት»፡፡ ጥቂቶች (ለምሳሌ ዮናስ) ወደ ሌሎች መሄዳቸው ይህን መሰረታዊ ህግ አይቃረንም፡፡አሁን ግን እቅዱ የተለየ ነው ፡፡ እየሩሳሌም ያኔም ማዕከላዊ ስፍራ ነበረች፤ ነገር ግን በዚህ ስፍራ ብቻ ቆይተው ሥር እንዲሰዱ ሳይሆን እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ተንቀሳቅሰው እንዲመሰክሩ ተጠሩ፡፡

ሉቃስ 24፡44-48ን ያንብቡ፡፡ ደቀመዛሙርቱ መስበክ የሚገባቸው መሰረታዊ መልእክት ምን ነበር?

የሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ለአርባ ቀናት ከደቀመዛመርቶቹ ጋር ቆይቷል (ሐዋ.1፡3)፡፡ በሐዋ.1፡6 ላይ የጠየቁት ጥያቄ ብዙ መረዳት እንዳልነበራቸው ቢያመለክትም የሱስ ስለ እግዚአብሄር መንግስት ሁኔታ ብዙ እውነቶችን ይገልፅላቸው እንደነበር መገመት አይከብድም፡፡ ስለተነገሩት ትንቢቶች የሚያውቁ ቢሆንም ከመስቀሉና ባዶ ከሆነው መቃብሩ በፈነጠቀው አዲስ ብርሃን አማካኝነት ነገሮችን በግልጽ ማየት ቻሉ፡፡ (ሐዋ.3፡17-19ን ይመልከቱ)፡፡

## ማክሰኞ ሰኔ 26

### ዳግም ይመጣል

ሐዋ.1፡9-11ን ያንብቡ፡፡ሉቃስ የክርስቶስን እርገት እንዴት አድርጎ ነው የገለፀው? ሁለቱ መላእክት ለነርሱ የተናገሩት ንግግር አስፈላጊነት ምንድነው? (ዘዳ.19፡15ን ተመልከቱ)፡፡

---

---

ሉቃስ ስለ የሱስ ወደላይ ማረግ የገለጸው በአጭሩ ነው፡፡ የሱስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር በደብረ ዘይት ተራራ እየባረካቸው አብሮአቸው ቆይቶ ነበር (ሉቃስ 24፡51)፡፡ ከዛ ወደ ሰማይ ተወሰደ፡፡ ሁኔታው የተገለጸው የሰው አይን ያየውን ሁኔታ መግለጽ በሚችለው ቋንቋ እንጂ ከስተቱ ከዚህም በላይ አስገራሚነበር፡፡ የሱስ ይህንን ምድር ለቆሲሄድበአይን እንዲታይ ወደላይ ከመውጣት ሌላ መንገድ አልነበረም፡፡

የክርስቶስ እርገት እግዚአብሄር ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ሀይሉ ካደረጋቸው ተዓምራት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህ ሉቃስ በፃፈው ሀሳብ ውስጥ («ወደ ላይ ተወሰደ»ሐዋ.1፡9) በሚለው አገላለፅ ተገልጧል፡፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይህ አገላለጽ እዚህ ብቻ የተጠቀሰ ቢሆንም በግሪኩ የመጽሐፍ ቅጂ በብሉይ ኪዳን ውስጥ (The Septuagint) በተደጋጋሚ ተጠቅሶዋል፡፡ ሁሉም እግዚአብሄር ራሱ ያደረጋቸውን ድርጊቶች(ተዓምራት) የሚገልፁ ሲሆኑ ይህም አብ ራሱ የሱስን ከሞት እንዳስነሳው ሁሉ ወደ ሰማይም እንደወሰደው ይነግረናል (ሐዋ.2፡24፤32፤ ሮሜ 6፡4፤10፡9)፡፡

የሱስ በደመና ከተሰወረ በኋላ ነጫጭ ልብስ ለብሰው በደቀ መዛመርቱ አጠገብ ስለ ነበሩት ሁለት ሰዎች ሉቃስ በሐዋርያት ስራ ላይ ብቻ ፅፏል፡፡ አገላለፁ በሌላ ስፍራ መላእክቱ አንጸባራቂ ልብስ ለብሰው ከመገለጣቸው ክስተት ጋር የሚመሳሰል ነው (ሐዋ.10፡30፤ዮሐ.20፡12)፡፡የመምጣታቸው ምክንያት ሲሄድ ያዩት የሱስ ወደ ላይ እንደወጣ እንደዚያው ዳግም እንደሚመለስ ለደቀ መዛመርቱ ለማረጋገጥ ነበር፡፡ የሱስ «እያዩት» ወደ ላይ እንደወጣ የሚተርክልን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ብቻ ነው (ሐዋ.1፡9)፡፡

ስለዚህ እያዩት ወደ ላይ ማረጉ እያዩት ተመልሶ እንደሚመለስ ማረጋገጫ ሆኗቸዋል፤ይህም «በኃይልና በታላቅ ክብር» (ሉቃስ 22፡27)በደመና ይሆናል፡፡ «አይን ሁሉ ያየዋል» (ራዕይ 1፡7) ተብሎ ስለተፃፈ በስውር የሚከናወን ነገር የለም፡፡ ሲመለስም ብቻውን አይሆንም (ሉቃስ9፡26፤2ተሰ.1፡7) የዳግም ምፃቱ ክብር መጀመርያ ሲያርግ ከነበረው ክብር በብዙ ይልቃልና፡፡

የዳግም መፃቱን እውነታነትና ተስፋ እንዴት አድርገን ነው ሁልጊዜ ከአእምሯችን እንዳይጠፋ አድርገን ለመያዝ መማር የምንችለው?ይህ ታላቅ እውነታ የህይወት ክፍሎቻችንን ማለትም በገንዘባችን፤ ቅድሚያ በምንሰጠው ነገርና በግብረገብ ምርጫችን ላይ ተጽእኖ ሊያሳድርብን የሚገባው እንዴት ነው?

## ረቡዕ ሰኔ 27

### ለጴንጤቆስጤ ቀን መዘጋጀት

በሐዋ.1፡7-8 ላይ የሱስ ሲመልስ ጊዜን በተመለከተ ምንም ያለው ነገር አልነበረም፡፡ ነገር ግን ከንግግሩ የምንረዳው ነገር ቢኖር መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ደቀመዛመርቱም ተልእኮአቸውን ሲፈጽሙ እርሱ ዳግም ይመለሳል (ማቴ.24፡14)፡፡መላእክቱም ቢሆኑ ሲናገሩ (ሐዋ.1፡11) የክርስቶስ መንግስት መቼ እንደምትመጣ በመግለጽ ጥያቄያቸውን አልመለሱም ነገር ግን ጊዜው እሩቅ እንደማይሆን መረዳት ይቻላል፡፡ ደቀመዛሙርቶቹ ከዛ በኋላ «በታላቅ ደስታ ወደ እየሩሳሌም ተመለሱ»(ሉቃስ 24፡52) የተባለው በዚህ ምክንያት ይመስላል፡፡ተልእኮአቸውን በአግባቡ እንዲወጡ

ታላቅ ብርታትን ሊሰጣቸው የሚገባውና በጊዜ ስሌት ተወስኖ ያልተነገረው የየሱስ ዳግም ምጻት ተስፋ መጨረሻው በደጅ ስለመሆኑ ያመላከተናል፡፡ በሐዋርያት ስራ ላይ ያሉ ሌሎች ማብራሪያዎች ይህንን ሀሳብ በደንብ ይገልፃሉ፡፡

ሐዋ.1፡12-14ን ያንብቡ፡፡ በላይኛው ክፍል ውስጥ ሌሎች እነማን ነበሩ? መንፈስ ቅዱስ በነርሱ ላይ እንዲወርድ ያደረጉት ዝግጅትስ ምን ይመስላል?

---

---

ከደብረዘይት ተራራ በተመለሱ ጊዜ ደቀመዛርቱ ሁለት ፎቅ ባለው መኖሪያ ቤት ውስጥ በላይኛው የእንግዳ ክፍል (በላቲን ሴናኩለም) ተሰበሰቡ፡፡ የክርስቶስ ተከታዮች የነበሩ ሴቶች (ሉቃስ 8፡1-3፣ 23፡49፣ 24፡1-12) እንዲሁም የኢየሱስ እናትና ወንድሞች ከደቀመዛርቱ ጋር አብረው ነበሩ፡፡

የየሱስ ወንድሞች ሲባል የኢየሱስ ታናሽ የሆኑ የዮሴፍና የማሪያም ወንድ ልጆች (ማር.6፡3) ወይም ዮሴፍ ማርያምን ከማግባቱ በፊት ከመጀመርያ ጋብቻው(ከሞተችው ሚስቱ)ያገኛቸው ልጆች እንደሆኑ ይገመታል፡፡ ስለ የሱስ ያላቸው መረዳት በጥርጥር የተሞላ ስለነበረ በደቀመዛመርቶቹ መካከል መገኘታቸው የሚያስደንቅ ነው (ማር.3፡21፤ዮሐ.7፡5)፡፡ የሱስ ከሞት እንደተነሳ በልዩ ሁኔታ ቀድሞ ለያዕቆብ መታየቱ (1ቆሮ.15፡7)ትልቅ ልዩነትን አምጥቶ ይሆናል፡፡ በኋላም ያዕቆብ የክርስትያኑን ማህበረሰብ በመምራት ሂደት ውስጥ ጴጥሮስን ተክቶ ሲቆም እናየዋለን (ሐዋ.12፡17፣15፡13፣21፡18፣ገላ.2፡9-12)፡፡

ያለማቋረጥ ተግተው በመፀለይ (ሐዋ.1፡14) ያለሚቋረጥ በመቅደሱ ውስጥ ምስጋናን እያቀረቡ (ሉቃስ 24፡53) በመናዘዝ ንስሐ በመግባትና ኃጢያታቸውን በማስወገድ ተጠምደው ነበር፡፡ የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ወደ ክርስቶስ ምፃት እንደሚመራቸው በአእምሮአቸው ቢያስቡም የፀሎት ምላሽ ሆኖ መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ለሚፈጠረው ነገር መንፈሳዊ ዝግጅት አድርገው ነበር፡፡

በየቀኑ የህይወት ምርጫዎቻችን ላይ መንፈስ ቅዱስ ስራውን እንዲሰራ ጥርጊያ መንገዱን እንዴት አድርገን ነው ልናዘጋጅለት የምንችለው?

## ሐሙስ ሰኔ 28

### አስራ ሁለተኛው ሐዋርያ

120 አባላት ላሉትቀደምት የክርስትያን ማህበር የይሁዳ ምትክ ሊሆን የሚችለውን ሰው መምረጥ የመጀመርያው አስተዳደራዊ እርምጃ ነበር (ሐዋ.1፡15)፡፡

ሐዋ.1፡21-22ን ያንብቡ፡፡ ይሁዳን ሊተካ የሚመረጠው ሰው ሊያሟላው የሚገባው መስፈርት ምን ነበር ? ይህ ወሳኝ ነገር የሆነው ለምንድን ነው?

---

---

የተፈለገው የትንሳኤው ምስክር ሆኖ የሚቆም ሰውነበር (ከሐዋ. ሥራ 4፡33 ጋር ያነፃጽሩ)፡፡ ትንሳኤው ስለ የሱስ መሲህነት እና ስለ ክርስትና እምነት እውነታነት ሁነኛ ማረጋገጫ ስለነበረ በጣም አስፈላጊ ነበር፡፡

ምርጫው መከናወን ያለበት በየሱስ የአገልግሎት ወቅት ከሐዋሪያት ጋር አብረው ከነበሩት መካከል መሆን ነበረበት፡፡ ጳውሎስ የሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ሳይሆን ቆየት ብሎ ብቅ ያለ ስለነበር ሐዋርያ ተብሎ ወዲያው አልተጠራም፡፡በደማስቆ መንገድ ላይ የሱስን ስለተገናኘ ግን የትንሳኤው ምስክር ይሆን ዘንድ አስችሎታል(1ቆሮ. 9፡1)፡፡ «እንደ ጭንጋፍ ለምቆጠር» ብሎ ስለራሱ ቢናገርም (1ቆሮ.15፡8) ለሐዋሪያነት ብቁ ከመሆን አንፃር ከሌሎች ሐዋርያት ራሱን ያነሰ ያደረገ አይቆጥርም (1ቆሮ. 9፡2፣ ገላ. 2፡6-9)፡፡ ስለዚህ «ሐዋርያ» የሚለው ስያሜ ከቤተክስቲያን አመራርና ኃላፊነት አንጻር የሚያካትተው አስራ ሁለቱንና ጳውሎስን ብቻ ነበር ማለት ይቻላል (ሐዋ.1፡25-26)፡፡ ነገር ግን ጠቅለል ባለ መልኩ ቃሉ መልዕክተኛና ወኪል የሚል ትርጉም እንዳለው አድርገን ስናስብ መልእክቱን ለተሸከሙ ሌሎች የወንጌል ሰራተኞች መገለጫም ሆኖ ሊያገለግል ይችላል(ሐዋ.14፡4፣14፤ገላ.1፡19)፡፡

ሐዋ.1፡23-26ን ያንብቡ፡፡ **ማቲያስ የተመረጠው እንዴት ነበር?**

---

---

ማቲያስን የመረጡበት መንገድ እንግዳ ቢሆንም ነገር ግን ከጥንት ጀምሮ እጣ መጣል አንድን ውሳኔ ለመወሰን የሚያገለግል ሂደት ነበር(ለምሳሌ ዘሌ.16፡5-10፣ ዘሁ.26፡55)፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ምርጫው ከሁለት እኩል በሆነ ሁኔታ መስፈርቱን ከሚያሟሉ ሰዎች መካከል እንጂ ወደማይታወቅ ውጤት ለመምራት አልነበረም፡፡ አማኞችም የሚታየው ውጤት የፈቃድ መግለጫ እንዲሆን ወደ እግዚአብሄር ፀልየዋል(ከምሳሌ16፡ 33 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ውሳኔው ስህተት ተብሎ ክርክር እንደተነሳ የሚያመላክት ምንም ፍንጭ የለም፡፡ ከጴንጤቆስጤ ቀን በኋላ የመንፈስ ቅዱስ ቀጥተኛ ምሪት ስለነበረ እጣ የመጣሉ ሂደት አስፈላጊነት አከተመ (ሐዋ.5፡3፤11፡15-18፤13፡2፤16፡6-9)፡፡

**አንድ ሰው ወደ እርስዎ መጥቶ‹‹እግዚአብሄር ለህይወቴ ያለውን ፈቃድ እንዴት አድርጌ ማወቅ እችላለሁ?›› ብሎ ቢጠይቅዎ ምላሽዎ ምን ይሆን? ለምን?**

## ዓርብ | ሰኔ 29

ተጨማሪ ጥናት፡-«በጴንጤቆስጤ ቀንና ፓሮሲያ (ዳግም ምፃት) መካከል ያለው ጊዜ (ይነስም ይብዛም) አለማቀፋዊቷ ቤተክርቲያን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልታ ተልእኮዋን የምትፈጽምበት ጊዜ ነው፡፡ የክርስቶስ ተከታዮች የሱስ በመጀመርያ ምፃቱ ወቅት ምን እንዳከናወነ በመናገር ሰዎች ንስሃ ገብተው ለዳግም ምጻቱ በመዘጋጀት እንዲያምኑ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ "እስከ አለም ዳርቻ ድረስ" (ሐዋ. 1፡8) «እስከ ፍፃሜ ጊዜ ድረስ» ምስክሮቹ እንዲሆኑ ተጠርተዋል፡፡ ... ሁለቱን ጥጎች እስከንደርስ ሥራችንን ለማቋረጥ ነፃነት አልተሰጠንም፡፡» - John R.W.Stott, The Message Of Acts : The Spirit, The Church And The World (Downers Grove: Interrarsity, 1990)P.44::

«ለደቀመዛመርቱ የተሰጠው የአዳኛችን ተልዕኮ ሁሉንም አማኝ የሚያካትት ነው፡፡ እስከ አለም ፍፃሜ ድረስ በክርስቶስ የሚያምኑትን በሙሉ ያካትታል ፡፡ ነፍሳትን የመማረክ ስራ ለተቀቡ አገልጋዮች ብቻ የተተወ አገልገሎት ነው ብሎ ማሰብ ትልቅ ስህተት ነው፡፡ሰማያዊ መነሳሳት ለመጣለት ሰው ሁሉ የወንጌል አደራ ተጥሎበታል፡፡የየሱስን ህይወት ለተቀበሉ ሁሉ ሰዎችን ወደ ድነት ለመጥራት ተቀብተዋል፡፡ ለዚህ ተግባር ሲባል ቤተክርስቲያን ተመስርታለች፤ ይህ የተቀደሰ ተግባር እንደሆነ አምነው ቃል የገቡ ሁሉ የየሱስ የስራ ባልደረቦች ሆነው ይሳተፋሉ፡፡»- ELLEN G.WHITE THE DESIRE OF AGES,P.822.

# የመወያያ ጥያቄዎች

1 ሐዋ.1፡7 የሚያስታውሰን ማር.13፡32ን ነው፡፡ «ነገር ግን ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰአት ከአብ በቀር የሰማይ መላእክት ቢሆኑ ወልድም ቢሆን ማንም አያውቅም፡፡» ኤለን ጂ.ኋይት ስትናገር «ከዚህ በኋላ ጊዜን በተመለከተ ለእግዚአብሔር ህዝቦች የሚመጣ መልእክት አይኖርም፡፡ስለ መንፈስ ቅዱስ መውረድም ሆነ ስለ ክርስቶስ ምፃት ትክክለኛ ሰአት ልናውቅ አይቻለንም፡፡» SELECTED MESSAGES, VOL.1,P.188:: እዚሁ ላይ ስታክልም ስለ ክርስቶስ መገለጥ ሰአቲቱን በተመለከተ መልእክት አለኝ ብሎ መናገር የሚጀምር ሰው ካለ ያ ሰው በራሱ ላይ ቀንበር እንዳደረገና የሱስ ያልሰጠውን መልእክት እያወጀ እንዳለ ይቆጠራል፡፡» ADVENT REVIEW AND SABBATH HERALD, SEPT.12,1883 :: እንዲህ አይነቱ አገላለፅ ዛሬ ለኛ ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው?

2. አንድ ሰው ሲናገር «እግዚአብሄር ከጠበቆች ይልቅ ምስክሮችን ይሻል» ብሏል ስለዚህ አባባል እርስዎ ምን ይሰማዎታል?

3.ቀዳሚ በነበረችው ቤተክርስቲያን ውስጥ የፀሎት ሚና ምን ያህል ነበር? ትልቅ ውሳኔ ለሚያሻቸው ጉዳዮች በሙሉ ፀሎት ማድረጋቸው እንዲሁ የአጋጣሚ ነገር ይመስለናል? (ሐዋ.1፡24፤8፡14-17፤9፡11-12፤10፡4፣9፣30፣13፡2-3) በህይወታችን ውስጥ ፀሎት ያለው ሚና ምንድነው?

**2ኛ ትምህርት** ከሰኔ 30 - ሐምሌ 6

# ጴንጤቆስጤ

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሳምንት ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ:-ሐዋርያት ሥራ 2፡1-4፣ዮሃንስ 14፡16፣ ሐዋ.ሥራ 2፡5-13፣ ኢዮኤል 2፡28-32፣ ሐዋ.ሥራ 2፡22-39፣ መዝ.110፡1-3

**መታሰቢያ ጥቅስ** ፡- "ይህን ኢየሱስ፣ እግዚአብሔር ከሞት አስነሳው፤ እኛም ሁላችን ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ካለ በኋላ፣ የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ ከአብ ተቀብሎ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው፡፡" /ሐዋሪያት ሥራ 2፡32-33/

"ጴንጤቆስጤ" የግሪክ ቃል ሲሆን የአይሁድን የሰባት ሱባኤ በዓል /ዘፀ.34፡ 22/ ለመግለፅ እንዲሁም በሌላ ስሙ የመከር በዓል /ዘሁልቅ 28፡26/ የሚባለውን ለመግለፅ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው፡፡ ጥሬ ቃሉ "ሃምሳኛው" የሚል ትርጉም ያለው ሲሆን ከፋሲካ በዓል ቀጥሎ ባለው ቀን ከቀረበው የእህል ቁርባን ጀምሮ ሲቆጠር በ50ኛው ቀን ስለሚከበር ይህ ስም ተሰጥቶታል፡፡ የእስራኤል ሕዝብ "ከስንዴው መከር በኩራትን" በእግዚአብሔር ፊት ሲያቀርብ የደስታና የምስጋና ቀን ይሆን ነበር/ ዘፀ. 34፡22/፡፡

ይህ በዓል መንፈስ ቅዱስ ከሌላው ጊዜ ይልቅ በሙላት በቤተክርስቲያን ላይ በወረደበት ቀን ከተሰበሰበው መከር ማለትም በዚያ ቀን ከተጠመቁት ሶስት ሺህ ነፍሳት መከር ጋር ገጣሚ የሆነ ምልክት ሆነ/ሐዋ ሥራ 2፡41/፡፡ የክርስቶስን ማረግና በሰማያዊ ስፍራ መክበር ተከትሎ ይህ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ድንገተኛና መለኮታዊ ክስተት ሲሆን ሐዋሪያቱን ከተራ ገሊላውያን ዓለምን ወደሚለውጡ ቆራጥና ብርቱ ሰዎች ለውጧቸዋል፡፡

በአብዛኛው ጴንጤቆስጤ የክርስቶስ ተከታይ የሆኑ አይሁድና በኋላም አሕዛብ እንደ አዲሱ በምድር ያለ የእግዚአብሔር ሕዝብ ተቀባይነት ያገኙበት ስለሆነ የቤተክርስትያን ልደት ቀን ተብሎ ይጠራል፡፡ለሐምሌ 7 ሰንበት ለመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ያጥኑ፡፡

**እሁድ** **ሐምሌ 1**

## የመንፈስ ቅዱስ አመጣጥ

የክርስቶስን ትዕዛዝ በመታዘዝ አማኞቹ ከልብ በሆነ ፀሎት፣ ምስጋናና ንስሐ በኢየሩሳሌም ቃል የተገባውን መንፈስ ቅዱስን እየጠበቁ ነበር፡፡ ያ ቀን ሲደርስ ሁሉም በአንድነት በአንድ ስፍራ"/ሐዋ.2፡1/፡፡ ምናልባት ሐዋርያት ሥራ 1 ላይ በተጠቀሰው በላይኛው ክፍል /ሰገነት/ ውስጥ ነበሩ፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ግን ብዙዎች ወደሚሰበሰቡበት ቦታ ሊሻገሩ ነበር/ሐዋ.ሥራ 2፡6-13/፡፡

ሐዋሪያት ሥራ 2፡1-3ን ያንብቡ፡፡ መንፈስ ቅዱስ በሚወርድበት ጊዜ ምን አይነት ተአምር ተከሰተ?

____________________________________________________

____________________________________________________

ታላቅ ክስተት ነበር፤ መጀመሪያ እንደ ታላቅ አውሎ ነፋስ አይነት ድምፅ ቤቱን በድንገት ሞላው፤ ከዚያም በዚያ በነበሩበት ራስ ላይ እንደ እሳት ነበልባል አይነት ነገሮች አረፉባቸው፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ንፋስና እሳት በአብዛኛው ከመለኮታዊ ኃይል መገለጥ /ቲዮፋኒ/ ጋር ተገናኝቷል (ለምሳሌ ዘፀ. 3፡2፣19፡18፣ዘዳ. 4፡15)፡፡ በተጨማሪም ንፋስና እሳት የእግዚአብሔርን መንፈስ ለመግለፅም ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል /ዮሐ.3፡8፣ ማቴ.3፡11/፡፡ ወደ ጴንጤቆስጤ ቀን ስንመጣ የክስተቱ ትርጉም ምንም ይሁን ምን በድነት ታሪክ ውስጥ የልዩ ቅፅበት ጅማሮ ምልክት ነበር፤ ያም ተስፋ የተገባው የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜም በስራ ላይ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን በነበሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ላይም የመንፈስ ተፅዕኖ ግልፅ በሆነ ሁኔታ በተደጋጋሚ የተገለጠ ሲሆን በሙላት ግን አልተገለጠም፡፡ "በአበው ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ተፅዕኖ በተደጋጋሚ በግልፅ የታየ ቢሆንም በሙላት ግን አልተገለጠም፡፡ የአዳኛቸውን ቃል በመታዘዝ ደቀመዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን እንዲልክላቸው ለመኑ፤ ክርስቶስም በሰማይ ማለደላቸው፡፡ አባቱ መንፈስ ቅዱስን በሕዝቡ ላይ ያፈስ ዘንድ ጠየቀ፡፡" *Ellen G. white, the acts of the apostles, pg 37*

መጥምቁ ዮሐንስ አስቀድሞ መሲሁ በመንፈስ እንደሚያጠምቅ የተናገረ ሲሆን /ሉቃ.3፡16ን ከሐዋ.ሥራ 11፡16 ጋር ያነፃፅሩ/ ኢየሱስም በተደጋጋሚ ስለዚህ ጉዳይ ተናግሯል /ሉቃስ 24፡49፣ሐዋ.ሥራ 1፡8/፡፡

ይህ የመንፈስ መውረድ ኢየሱስ በአባቱ ፊት ያደረገው የመጀመሪያ ምልጃው ነበር /ዮሐንስ 14፡16፤26፤15፡26/፡፡ በጴንጤቆስጤ ቀን ተስፋው ተፈፀመ፡፡

በጴንጤቆስጤ ቀን የተፈፀመው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ክርስቶስ በመስቀሉ ከተቀዳጀው ድልና በሰማይ ከመክበሩ ጋር የተያያዘ ልዩ ክስተት ቢሆንም በመንፈስ ቅዱስ መሞላት በአማኞች ህይወት በቀጣይነት መደገም ያለበት ልምምድ ነው፡፡ /ሐዋ.ሥራ 4፡8፤31፤11፡24፤ 13፡9፤ ኤፌ. 5፡18/

መንፈስ ቅዱስ በህይወትዎ እየሰራ ለመሆኑ ምን ማስረጃ አለዎት?

ሰኞ ሐምሌ 2

## የልሳን ስጦታ

በሐዋርያት ሥራ 2፡4 ላይ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በልሳን ውስጥ ተገልጧል፡፡ ይህ ግን ከብዙዎቹ የመንፈስ ስጦታዎች አንዱ ብቻ ነበር /ሐዋ.ሥራ 10፡45-46፤19፡6/ ሌሎቹ ስጦታዎች የትንቢት /የወደፊቱን መናገር /ሐዋ.ሥራ 11፡28/፤ ራዕይ /ሐዋ.ሥራ 7፡55/ ስብከት /ሐዋ.ሥራ 2፡8፤28፡25/፤ መፈወስ /ሐዋ.ሥራ3፡6፤12፤5፡12፤16/ ለተለየ አገልግሎት መሾም /ሐዋ. 6፡3-5/ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የልሳን ስጦታ በጴንጤቆስጤ ቀን የተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ መኖር ብቸኛው መገለጫ ወይም በጣም ቅልቁ ማስረጃ ስለሆነ አይደለም፡፡ በዚህ ጊዜ የተገለጠው የቤተክርስቲያኗን አለም አቀፋዊ ተልዕኮ በይፋ ለማስጀመር ነበር፡፡ ይህ ማለት በሐዋርያት ሥራ 1፡8 ላይ የተሰጠው ተልዕኮ የልሳንን ስጦታ ይጠይቅ ነበር ማለት ነው፡፡ ሐዋርያቱ የባህልን ግድግዳ አልፈው እስከ ዓለም ዳርቻዎች በወንጌል አለምን ለመድረስ በሰሚዎቻቸው ቋንቋዎች መናገር ያስፈልጋቸው ነበር፡፡

ሐዋሪያት ሥራ 2፡5-12ን ያንብቡ፡፡ በጴንጤቆስጤ ቀን ሐዋርያቱ በዚያን ዘመን በነበሩ ሌሎች ቋንቋዎች ለመናገራቸው ምን ማስረጃ አለ?

---

በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን በዓለም ከስምንት እስከ አስር ሚሊዮን አይሁዶች እንደነበሩ የሚገመት ሲሆን ከነዛ ውስጥ 60 በመቶው ከአይሁድ ውጪ ይኖሩ ነበር፡፡ ሆኖም በዓሉን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ከመጡት አብዛኞቹ ከሌሎች አገሮች የመጡና አይሁዳውያን በጊዜው ይናገሩት የነበረውን አረማይክ ቋንቋ የማይናገሩ ነበሩ፡፡

በጴንጤቆስጤ ቀን ከተጠመቁት አብዛኞቹ ከሌሎች ሃገሮች የመጡና ወንጌሉን በራሳቸው ቋንቋ የሰሙ አይሁዶች ለመሆናቸው ምንም ጥያቄ የለውም:: ሐዋርያት ከማይስተዋል ቋንቋ ይልቅ የሌሎች አገር ሰዎች በሚናገሯቸው ቋንቋዎች ለመናገራቸው ማስረጃው ድያሌክቶስ /ሐዋ.ሥራ 2፡6-8/ የሚለውና የአንድ አገር ወይም አካባቢ ቋንቋ የሚል ትርጓሜ ያለው ቃል ነው /ከሐዋ.ሥራ21፡40፣22፡2ና 26፡14 ጋር ያነፃፅሩ/:: ስለዚህ በግልፅ በነዚህ የተለያዩ ቋንቋዎች ይናገሩ ነበር ማለት ነው:: አስደናቂው ነገር ከሰዓታት በፊት ያንን ቋንቋ መናገር የማይችሉ የነበሩት ተራ የገሊላ ሰዎች አሁን መናገር መቻላቸው ነው:: እነዚያን ቋንቋዎች የማያውቁት፣ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩትና ይህንን ትዕይንት የተከታተሉት አይሁዳውያን እነርሱ የማይገባቸውን ቋንቋ ሲናገሩ ሲሰሙ ሐዋሪያት ጠጥተው እንደሰከሩ ገመቱ:: “ሌሎች ግን እያፌዘባቸው ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል:: አሉ::” /ሐዋ. ሥራ 2፡13/

ታላቅ የእግዚአብሔር ኃይል መገለጥ እየተካሄደ በአይናቸው እያዩ እንኳን ስካር ብቻ ነው ብለው አሰቡ:: እኛ ራሳችን መንፈሳዊ አይነ ስውሮች እንዳንሆን መጠንቀቅ የምንችለው እንዴት ነው?

## ማክሰኞ ሐምሌ 3

## የጴጥሮስ ስብከት

ጠጥታችሁ ሰክራችኋል መባላቸው ጴጥሮስ ምን እየተከሰተ እንደሆነ እንዲናገር እድል ሰጠው:: በንግግሩ መጀመሪያ ሐዋርያውያ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ የትንቢት ፍፃሜ እንደሆነ በመጠቆም ወደ መጽሐፍ ቅዱስ አመላከተ /ሐዋ. ሥራ 2፡16-21/::

ሐዋርያት ሥራ 2፡17ን ከኢዮኤል 2፡28 ጋር ያነፃፅሩ:: የኢዮኤል ትንቢት የሚፈፀምበትን ጊዜ ጴጥሮስ እንዴት አስተዋለ?

---

የኢዮኤል ትንቢት በመንፈስ ቅዱስ መውረድና በታላላቅ ተአምራት ስለሚገለፀው የወደፊት የመዳን ዘመን ነበር/ኢዮኤል 2፡32/:: በጴንጤቆስጤ ቀን የተከሰተውን ክስተት ከእንደዚህ አይነት ትንቢት ጋር ጴጥሮስ ያያያዘው የክስተቱን ታሪካዊ ቦታ አጠንክሮ ለማስቀመጥ ስለፈለገ ነው:: ኢዮኤልን ሲጠቅስ ግን አንድ አስፈላጊና ለየት ያለ ነገርን እናገኛለን:: ወደ አንድ የወደፊት ጊዜ በሚያሳየውና ኢዮኤል “ከዚህ በኋላ” ባለው አገላለፅ ምትክ ጴጥሮስ “በመጨረሻው ዘመን” /ሐዋ. ሥራ 2፡17/ አለ፤ ይህም የታላቁ የመዳን(የድነት) ድራማ የመጨረሻ ተግባር እየጀመረ መሆኑን የሚያሳይ ነበር::

ይህ በርግጥ የመጨረሻው ዘመን ክስተቶችን በሙላት የሚገልጽ ባይሆንም በተለይ የቀደመችዋ ቤተክርስቲያን እጅግ በፍጥነት ማድረግ ስላለባት ስራ እንደ ማስረጃ የሚቀመጥ ነበር፡፡ ፍፃሜው መቼ እንደሚሆን ባያውቁም ብዙ ሊቆይ እንደማይችል ግን ተረድተው ነበር፡፡

ሐዋርያት ሥራ 2፡22-32ን ያንብቡ፡፡ ጴጥሮስ ስለ ወንጌል በተናገረው ውስጥ ዋናው ነጥብ ምን ነበር?

---

---

የጴንጤቆስጤውን ክስተት ትንቢታዊነት ከጠቀሰ በኋላ ጴጥሮስ ቅርብ ወደነበረው ወደ ኢየሱስ ህይወት፣ ሞትና ትንሳኤ ተሻገረ። ትልቅ ትኩረት የተሰጠው ግን ትንሳኤው ነበር፤ ምክንያቱም በወንጌል ታሪክ ውስጥ ወሳኙን ሁኔታ ስለሚገልፅ ነበር፡፡ ለጴጥሮስ የክርስቶስ ትንሳኤ ተቀባይነት የማግኘቱ ብቸኛ መገለጫ /ሐዋ. ሥራ 2፡22፣27/ ሲሆን የትንሳኤውን ትርጉም ለመግለፅ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ተጠቅሟል፡፡

ኢየሱስ መሲሁ/የተቀባው/ ስለነበር ሞት ሊይዘው አይችልም፡፡ ስለዚህ ለጴጥሮስና ለሌሎች የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች የክርስቶስ ትንሳኤ ስለ መሲህነቱ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ስለ ድነት መልዕክት ጠንካራ ማስረጃ ሆነ፡፡

ሞት በዙሪያችን እኛንና በአካባቢያችን ያሉትን የምንወዳቸውን ሁልጊዜ እያስፈራራን ባለንበት ሁኔታ የኢየሱስ መነሳት አስፈላጊ እውነት የሆነው ለምንድነው?

## ረቡዕ ሐምሌ 4

### የኢየሱስ መክበር

“ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ካለ በኋላ የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ ከአብ ተቀብሎ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው፡፡”/ሐዋ. ሥራ 2፡33/

በንግግሩ በሦስተኛ ደረጃ ሰዎቹን በቅድሚያ ስለሳባቸው ስለ ልሳን ጉዳይ መናገር ጀመረ፡፡ ከጠዋቱ 3 ሰዓት ላይ ያልተለመደ ከሆነው ጠጥቶ መስከር ይልቅ መንፈስ ቅዱስ ከሰማይ ስለፈሰሰባቸዉ በቋንቋቸው /በልሳን / እየተናገሩ ነበረ፡፡

ሐዋ.ሥራ 2፡33-36ን ያንብቡ፡፡ የኢየሱስ በእግዚአብሐር ቀኝ መክበርና የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ምን ግንኙነት አላቸው?

የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ስልጣንን የሚገልፅ ነው /መዝ.110፡1-3/፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመስርቶ ጴጥሮስ ሲሞግት ኢየሱስ በተከታዮቹ ላይ መንፈስን ያፈሰሰው በሰማይ ስለከበረ ነው ይላል፡፡ ያ መክበር ክርስቶስ በፊት ያልነበረውን ስልጣን የሰጠ አልነበረም (ዮሐንስ 1፡1-3፤17፡5) በተቃራኒው እንደ ጌታና እንደ አዳኝ ያለውን ቦታ አብ የገለፀበትን ሁኔታ ይወክላል (ሐዋ. ሥራ 2፡36)፡፡

ይህ ክስተት በርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ወደሆነው መልዕክት ይመራናል፡- በመልካምና በክፉው መካከል ስለሚካሄደው ታላቁ ተጋድሎ፡፡ ነጥቡ ኢየሱስ ካልከበረ መንፈስ ቅዱስ በሙላት ሊመጣ አይችልም(ዮሐ. 7፡39)፤ኢየሱስ በመስቀል ላይ ድል ባያደርግ ደግሞ አይከብርም ነበር (ዮሐ. 17፡4-5)፡፡ በሌላ አማርኛ መንፈስ ቅዱስ ከመውረዱ በፊት ኢየሱስ መክበር ነበረበት፤ምክንያቱም ያ ሁኔታ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የተቀዳጀው ድል እንዲሁም የዚህ ዓለም ገዢነትን በጉልበቱ የወሰደው የሰይጣን ሽንፈት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱን የሚያሳይ ክስተት ስለነበረ ነው (ዮሐ. 12፡31)፡፡

የኃጢአት ወደ ዓለም መግባት በእግዚአብሔር ላይ ጥያቄ እንዲነሳ አድርጓል፡፡ የኢየሱስ መሞት ሰብአዊ ዘርን ለመዋጀት ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፃድቅነትና የሰይጣንን ተንኮለኝነት ለማጋለጥ አስፈላጊ ነበር፡፡ በኢየሱስ አገልግሎት የተወደደችው የጌታ ዓመት ጀምራለች (ሉቃስ 4፡18-21)፡፡ አጋንንትን ሲያስወጣና ኃጢአትን ይቅር ሲል የሰይጣን ምርኮኞች የነበሩትን ነፃ እያወጣ ነበር፡፡ ሆኖም ያንን ለማድረግ ሙሉ ስልጣን የሚሰጠው መስቀሉ ነበር፡፡ ስለዚህ የክርስቶስ ራሱን መስጠት በሰማይ ተቀባይነትን ሲያገኝ ሰይጣን ታላቅ ሽንፈት ደረሰበት፤ ለክርስቶስ ዳግም ምፃት ህዝቦችን ለማዘጋጀትም መንፈስ ቅዱስ ወረደ፡፡

## ሐሙስ ሐምሌ 5

### ***የመጀመሪያዎቹ ፍሬዎች***

የጴጥሮስ አዳማጮች በተናገራቸው ቃላት ልባቸው ተነካ፡፡ አንዳንዶቹ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ኢየሱስ እንዲሰቀል ከሚጠይቁት መካከል ሊሆኑ የሚችሉ ነበሩ (ሉቃስ 23፡ 13-25)፡፡ አሁን ግን የናዝሬቱ ኢየሱስ የተቀባው የእግዚአብሔር መሲህ መሆኑን አምነው «ምን እናድርግ?» ብለው ጮኹ (ሐዋ. ሥራ 2፡37)፡፡

ሐዋ.ሥራ 2፡38ን ያንብቡ፡፡ ይቅርታን ለማግኘት ሁለቱ ቅድመ ሁኔታዎች ምንድናቸው?

ንስሐ ከሐዘን ወይም ፀፀት ስሜት ይልቅ የህይወት አቅጣጫ ለውጥ፣ ለኃጢአትም ጀርባን መስጠት ነው፡፡ ልክ እንደ እምነት ንስሐም የእግዚአብሔር ስጦታ ሲሆን ላለመቀበል መምረጥ እንችላለን (ሐዋ. ሥራ 5፡31-33፤26፡19-21፤ ሮሜ 2፡4)፡፡

ከመጥምቁ ዮሐንስ ዘመን ጀምሮ ንስሐ ከጥምቀት ጋር ተያይዟል (ማርቆስ 1፡4)፡፡ ማለትም ጥምቀት ከኃጢያት የመንፃትና በመንፈስ እንደገና የመወለድ ምልክት ሆኖ የንስሐ መገለጫ ሆኗል (ሐዋ. ሥራ 2፡38፤22፡16ን ከቲቶ 3፡5-7 ጋር ያነፃፅሩ)፡፡

ሐዋ.ሥራ 2፡38-39ን ያንብቡ፡፡ ንስሐ ለገቡና ለተጠመቁ ምን የተለየ ቃል ተገብቶላቸዋል?

በጴንጤቆስጤ የነበሩት ሰዎች ያገኙት የኃጢአትን ይቅርታ ብቻ ሳይሆን ለመንፈሳዊ ዕድገት፣በቤተክርስቲያን ለማገልገልና በዋናነት ወንጌልን ለማዳረስ የሚያግዘውን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ነበር፡፡ ይህ ከበረከቶቹ ሁሉ የበለጠው ነው፤ ምክንያቱም ቤተክርስቲያን ያለችው የወንጌልን መልካም ዜና ለማካፈል ስለሆነ ነው (1 ጴጥ. 2፡9)፡፡ ስለዚህ ከዚህ ጊዜ በኋላ ለመዳናቸው ማረጋገጫና ቤተክርስትያን ለተጠራችበት ተልዕኮ ለማብቃት የመንፈስ ቅዱስን ኃይል አግኝተዋል፡፡

«የኃጢአት ይቅርታ» ማግኘታችንን መረዳታችን ወንጌልን ለመናገር ለሚፈልግ ሰው ሁሉ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው? ቀድሞውኑስ ቢሆን እርስዎ ያ ተስፋ ከሌለዎት ለሌሎች ያንን ተስፋ እንዴት ሊሰጡ ይችላሉ?

## ዓርብ | ሐምሌ 6

**ተጨማሪ ኃሳቦች**፡- በጴንጤቆስጤ ቀን የመንፈስ ቅዱስ መውረድ በሰማይ ስለተካሄደው ነገርና አብ ለኃጢአት የተደረገውን የክርስቶስን መስዋዕት የመቀበሉን እውነት ግልፅ አድርጓል፡፡ ይህ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ በምድር ላይ መስዋዕት በመሆኑ ላይ የተመሠረተውን ክርስቶስ በሠማይ የሚሰራውን የምልጃ ሥራ በይፋ አስጀምሯል፡፡ እነዚህ አስደናቂ ክስተቶች ምድርና ሰማይ አሁን ሙሉ ለሙሉ ልናስተውል በማንችለው መልኩ የተቆራኙ (የተገናኙ) የመሆናቸው አስደናቂ እውነታ መገለጫ ናቸው፡፡

«የክርስቶስ ወደ ሰማይ ማረግ የርሱ ተከታዮች ቃል የተገባላቸውን በረከት ሊቀበሉ እንደሆነ ምልክት የሚሆናቸው ነበር፡፡... ክርስቶስ የሰማይን በሮች አልፎ ሲገባ መላዕክት በውዳሴ አጅበውት ነበር፡፡ይህ ስርዓት እንደተጠናቀቀ መንፈስ

ቅዱስ በሐዋሪያት ላይ በታላቅ ኃይል ወረደ፤ ክርስቶስም ከጥንት ጀምሮ በአባቱ ዘንድ በነበረው ክብር ከበረ፡፡ በጴንጤቆስጤ ቀን መንፈስ ቅዱስ መውረዱ ሰማይ የአዳኙ አገልግሎት መጀመሩን ያሳወቀበት ክስተት ነበር፡፡ ቃል እንደገባው እንደ ካህንና ንጉስ በሰማይና በምድር ሁሉ ላይ ስልጣን መቀበሉን በሚገልፅ ሁኔታ ለተከታዮቹ መንፈስ ቅዱስን ልኮላቸዋል፡፡» Ellen G.white, The Acts of the Apostles, PP.38,39

*የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ዛሬ ቤተክርስቲያን በጴንጤቆስጤ ቀን ከሆነው የትኛውን ልትጠብቅ ይገባታል? የሚደገመው የትኛው ነው? የማይደገመውስ የቱ ነው?

2. ጴጥሮስ በመልዕክቱ የኢየሱስን ትንሳኤ እጅግ ጠቃሚ አድርጎ ማስቀመጡ ላይ ያሰላስሉ፡፡ ትንሳኤውን እጅግ አስገራሚ የሚያደርገው ደግሞ አይሁዶች ስለ መሲሁ የሚጠብቋቸው ነገሮች ቢኖሩም መሲሁ ከሞት ይነሳል ብሎ የሚጠብቅ ማንም አልነበረም፡፡ ይህ በማንም መንፈሳዊ ግምት ውስጥ ስለ መሲሁ በነበራቸው ምልከታ ውስጥም አልነበረም፡፡ በዘመናችን ከሚስተማሩትና ብዙ እውቅና ከተሰጣቸው ትምህርቶች በተቃራኒ መጽሐፍ ቅዱስ በነዚያ ጉዳዮች ላይ ስለሚናገረው ነገር ማወቅ ያለብን ለምንድነው?

3. ሐዋ. *ሥራ* 2፡38 ስለ ጥምቀት አስፈላጊነት ይናገራል፡፡ ስለዚህ ይህ ማለት አንድ በየሱስ ያመነና ከመጠመቁ በፊት የሞተ ሰው ይጠፋል ማለት ነው? መልስዎትን ያብራሩ::

# 3ኛ ትምህርት ከሰኔ 23 - 29

## ህይወት በቀዳሚዋ ቤተክርስቲያን

ሰንበት ከሰዓት

*ለዚህ ሳምንት ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡- ሐዋ.2፡42-46፤ ሐዋ.4፡34-35 ፤ ሐዋ.3፡1-26፤ ሐዋ.4፡1-18፤ ሐዋ. 5፡34-39፡፡*

**<u>መታሰቢያ ጥቅስ</u>**፡- ‹‹በየዕለቱ በቤተመቅደስ በአንድነት እየተገናኙ በቤታቸውም እንጀራ እየቆረሱ በደስታና በቀና ልብ ይመገቡ ነበር፡፡እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝቡ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው፡፡››(ሐዋ.2፡46-47)

የቀደምቷ ቤተክርስትያን የችኮላ ስሜት ከዚያ በላይ ሊጨምር አይችልም ነበር፡፡ የሱስ ስለ መንግስቱ መቋቋም ለቀረበለት ጥያቄ በሰጠው ምላሽ የጊዜውን ጉዳይ አለመናገሩ (ሐዋ.1፡6-8) የሚያሳየው ሁሉም የሚወሰነው በመንፈስ ቅዱስ መውረድና በሐዋሪያቱ ተልእኳቸውን መፈፀም ላይ መሆኑን ነው፡፡ በጴንጤቆስጤ ቀን እነዛ ቀደምት ምዕመናን ሁሉም ነገር ፍፃሜን አገኘ ብለው ነበር፡፡መንፈስ ቅዱስን ተቀብለናል ወንጌልን ለአለም አዳርሰናል ብለው አስበዋል፤ ደቀመዛሙርቱ እየሩሳሌምን ሳይለቁና ወደ አለም ሳይሄዱ አለም ወደ እነርሱ መጣች (ሐዋ.2፡5-11)፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ቤተክርስቲያን ራስዋን ከቁሳቁስ ነፃ አደረገች፡፡ ጊዜው አጭር እንደሆነ ተረድተው ያላቸውን ሁሉ ሸጠው ለመማርና ህብረት ለማድረግ ብሎም ለየሱስ ምስክር ለመሆን ራሳቸውን ሰጡ፤ከኢየሩሳሌም ግን አልወጡም፡፡ የመሠረቱት የህብረት ኑሮ ድሆችን ለመርዳት ቢጠቅማቸውም የኋላ ኋላ ችግር አመጣባቸው፤ እግዚአብሄርም የቤተክርስቲያንን አንድነት ለመጠበቅ ሲል ጣልቃ ገባ፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር ከብዙ ተቃምዎች ጋር መጋፈጥ የጀመሩት፡፡ በዚህ ሁሉ ከባድ ወቅት ግን እምነታቸው አልተናወጠም፡፡

የዚህን ሳምንት ትምህርት አጥንተው ለ ሐምሌ 14 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡

## እሁድ ሐምሌ 8

# ማስተማርና ህብረት ማድረግ

ከጴንጤቆስጤ ቀን በኋላ ሉቃስ ትረካውን በእየሩሳሌም በምትገኘው ቤተክርስቲያን አጠቃላይ ውስጣዊ ኑሮ ላይ ያነጣጥራል፡፡ « እነርሱም በሐዋሪያት ትምህርትና በህብረት እንጀራውንም በመቁረስና በፀሎት ይተጉ ነበር፡፡» (ሐዋ. 2፡42) እዚህ ጋ የተጠቀሱት አራት ነገሮች ሲጠቃለሉ ትምህርት እና ህብረት ማድረግ ናቸው፡፡ ቁጥር 46 እንደሚነግረን ከሆነ ትምህርቱ ይከናወን የነበረው በቤተ መቅደስ ውስጥ ሲሆን በአንድነት የሚያሳልፉት ደግሞ በእያንዳንዳቸው ቤቶችነበር፡፡

የቤተ መቅደሱ ሸንጎ በጣሪያ የተከለለ ሲሆን ብዙውን ጊዜ መምህራን ደንቦቻቸውን የሚያስተምሩበት ስፍራ ነው፡፡ አማኞች ሁሉ ለሐዋሪያት ትምህርት የተሰጡ መሆናቸው የሚያሳየው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሀሳባዊ ወደሆነ ሀይማኖተኝነት ሳይሆን በድንቅና ተአምራት ወደ ታጀበውና ጥልቅ ወደ ሆነው የሐዋሪያት ትምህርት እንደመራቸው ነው (ሐዋ.2፡43)፡፡

መንፈሳዊ ህብረት ለቀዳሚዋ ቤተክርስቲያን ሁነኛ መገለጫዋ ነበር ፡፡ አማኞች በቤተ መቅደስ ብቻ ሳይሆን በቤቶቻቸውም ያልተቋረጠ አብሮነት ነበራቸው፡፡ አብረው ምግብ ይቆርሱ ነበር፤ የጌታን እራት ያከብሩ ነበር፤ ይፀልዩም ነበር (ሐዋ.2፡42-46)፡ ፡በየዕለቱ ይህንን በማከበር የቀድሞ ክርስትያኖች የሱስ በቅርቡ ዳግም እንደሚገለጽ ያላቸውን ተስፋ በመግለጽ የመሲሁ መንግስት ሲቋቋም ከእርሱ ጋር እንደገና አብረው እንደሚሆኑ ያምኑ ነበር(ማቴ.26፡29)፡፡

በቀደሞዋ ቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የግለሰቦች ቤት ወሳኙን ሚና ተጫውቷል፡ ፡ አማኞች በየቀኑ የቤተመቅደሱን ስርአት ይካፈላሉ(ሐዋ.3፡1)፤ በሰንበት ቀን ደግሞ ከአይሁድ ወዳጆቻቸው ጋር በመሆን በምኩራብ ይቀመጣሉ (ያዕ.2፡2)፡፡ ነገር ግን ልዩ የሆነው የአምልኮ ክፍል ይከናወን የነበረው በቤት ውስጥ ነበር፡፡

ሐዋ.2፡44-45፣ 4፡34-35ን ያንብቡ፡፡ ቀዳሚ የሆኑ ክርስቲያኖች ያደርጉት የነበረ ወሳኝ ነገር ምን ነበር?

________________________________________

________________________________________

የመጨረሻው ጊዜ ቅርብ እንደሆነ ስላመኑ ንብረቶቻቸውን «የየግል መጠቀሚያ እቃቸውን» (በየቀኑ የሚጠቀሙባቸውን ነገሮች) ምንም ያህል አስፈላጊ ሆነው

አልታዩዋቸውም፡፡ ስለዚህ ንብረቶቻቸውን መጋራታቸውና በጋራ መጠቀማቸው ተገቢ ነበር፡፡ መሲሁ መንግስቱን ሲያቋቁም የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንደሚሰጣቸው ስለሚያውቁ ስለነገ መጨነቅ እንደሌለባቸው አመኑ(ሉቃስ 22፡29-30)፡፡ በአብሮነት ንብረታቸውን የመጋራታቸው ሁኔታ እጅግ ታላቅ የልግስና አርአያዎች ከመሆን ባለፈ ጥልቅ የሆነ ህብረትን እንዲያጣጥሙ አደረጋቸው፡፡

ጌታ ከሰጠዎት ነገር ላይ እርስዎም ለሌላው ለመለገስ ምን ያህል ፈቃደኛ ነዎት?

## ሰኞ ሐምሌ 9

### የሽባው ሰው መፈወስ

በሐዋ. 3፡1 ላይ ጴጥሮስና ዮሐንስ ከቀኑ በዘጠኝ ሰአት በቤተ መቅደስ ለሚደረገው የፀሎት አገልግሎት ለመሳተፍ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዱ፡፡ ይህ የሚያሳየው በዚያን ወቅት የነበረው የክርስትና እምነት ውስጥ ስለነበሩ አይሁዳዊ ባህሪያት ነው፡፡ ይህም ማለት ሐዋሪያት ወደ ቤተ መቅደስ የሚሄዱት መመሪያ ለመስጠት ወይንም ሰዎች ልባቸው እንዲለወጥ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን ጴጥሮስና ዮሐንስ አይሁዳዊ ስለነበሩ የአይሁድ ሃይማኖታዊ ስርአትንም ለመፈፀም(ሐዋ.20፡16፤21፡17-26) ነበር (ቢያንስ እስከዚህኛው ክስተት ድረስ)፡፡ በዛም እጅግ አስደናቂ ተአምር ተከናወነና (ሐዋ.3፡1-10) ጴጥሮስ ሌላ ስብከት እንዲሰብክ እድል አገኘ፡፡

ሐዋ.3፡12-26ን አንብቡ፡፡ በጴጥሮስ ስብከት ውስጥ ያለው ዋነኛ ትኩረት ምን ነበር?

---

---

በቀድሞ ክርስቲያኖች ስብከት ውስጥ የሚንፀባረቁ አምስት ወሳኝ ነጥቦች ነበሩ፡- የሱስ መከራ የተቀበለው መሲህ ነው(ሐዋ.3፡18)፤ እግዚአብሔርም ከሙታን አስነሳው(ሐዋ. 3፡15)፤ የሱስ በሰማይ ከብሯል (ሐዋ.3፡13)፤ ዳግም ተመልሶም ይመጣል(ሐዋ.3፡20)፤ የኃጢያትን ይቅርታ ለማግኘት ንስሃ መግባት ያስፈልጋል(ሐዋ.3፡19)፡፡

ዓውዱ ቢለወጥም ለአለም ይዘን የምንሄደው መልእክት በብዙ መንገድ ከዚህ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ሐዋሪያት በአይሁድ ጥላ ስር ስለነበሩ ህዝቡ ሃይማኖቱን እንዲቀይር ከማድረግ ይልቅ ከብሉይ ኪዳን ወደ አዲስ ኪዳን «እንዲፈልሱ»አደረጉ፡፡ እንደ እግዚአብሄር ህዝብነታቸው መሲሁን መቀበልና እርሱንም በመቀበል የሚገኘውን አዲስ ልደት መለማመድ ነበረባቸው፡፡

ዛሬ ያለው ሁኔታ ከድሮው የተለየ ቢሆንም መልእክቱ ግን አሁንም አልተቀየረም፡፡ ክርስቶስ ለሐጢያታችን ሲል ሞተ፤ ከሞትም ተነሳ፤ እናም ደግሞ ተመልሶ ይመጣል ፡፡ ይህም ማለት በእርሱ አማካኝነት ድነትን እናገኛለን፡፡ በራእይ 14ላይ ከሚገኘው የሶስቱ መላእክት መልእክት አውድ አንጻር ስንቃኘው እንኳን የምናውጀው መልእክታችን ማዕከል ሊሆን የሚገባው የየሱስ መሞት፣ መነሳት እና ዳግም መመለስ ነው፡፡

«ክርስቶስን ከሚመሰክሩ ክርስትያኖች ሁሉ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች የሱስን ከማንም በላይ ከፍ አድርገው ለአለም ሊመስከሩ ይገባቸዋል፡፡ የሶስተኛው መልእክ መልዕክት ጥሪ የሚያመላክተን ስለ ሰንበት እውነትነት ነው፡፡ ይህ እውነትና ሌሎችም በውስጥ ያሉ መልእክቶች መታወጅ ይገባቸዋል፡፡ ነገር ግን የትኩረታችን ትልቁ ማዕከል የሆነው የሱስ ክርስቶስ ፈጽሞ ሊዘነጋ አይገባም፡፡ በርሱ መስቀል ላይ ነው ምህረት እና እውነት የተስማሙት ጽድቅና ሰላምም የተሳሳሙት፡፡ ኃጢያተኛው ወደቀራኒዮ አይኑን እንዲያቀናልንመራው ይገባል፡፡ ይህም እንደ ትንሽ ህጻን አዳኙን በማመን ብቻ ጽድቁን መቀበል በምህረቱም መታመን ነው፡፡» -Ellen G. White,Gospel Workers, Pp.156-157፡፡

## ማክሰኞ ሐምሌ 10

### የግጭት መነሳት

ብዙም ሳይቆይ ነበር የቤተክርስቲያኒቱን ስኬታማነት ተከትሎ በአንዳንድ የእየሩሳሌም መሪዎች አማካኝነት ግጭት ብቅ ማለት የጀመረው፡፡ የእየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የሚመራው በሊቀ ካህናት እና በረዳቶቻቸው አማካኝነት ሲሆን ብዙዎቹ ደግሞ ሰዱቃውያን ነበሩ፡፡ ሊቀ ካህኑ በወቅቱ በአብዛኛው ሰዱቃውያንንና ፈሪሳውያንን ይይዝ በነበረው ሸንጎ መሪ ነበር፡፡ሰዱቃውያን በሙታን ትንሳኤ ስለማያምኑ ጴጥሮስና ዮሐንስ ስለ የሱስ ከሞት መነሳት በመስበካቸው እጅጉን ተረበሹ፡፡ ሐዋሪያቱ በቤተ መቅደሱ ጠባቂዎች ተይዘው በማግስቱ በሸንጎ ፊት እስኪቀርቡ ድረስ በወህኒ ቤት ቆዩ(ሐዋ.4፡1-7)፡፡

ሐዋ.4፡1-18ን ያንብቡ፡፡ ይህንን በምን ስልጣን ያደርጉ እንደነበር ሲጠየቁ ጴጥሮስ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር? ጴጥሮስ በመለሰላቸው መልስ ውስጥ መሪዎቹ ስጋት ውስጥ እንዲወድቁ ያደረጋቸው ወሳኝ መልእክት ምን ነበር?

የአይሁድ መሪዎች ስልጣንን በተመለከተ መጠየቃቸው ኃይልን ለማግኘት ያላቸውን ፍላጎት ያሳያል፡፡ ጴጥሮስ ግን ይህ ተአምር በየሱስ ስም እንደሆነ ከመናገር በተጨማሪ የድነት ምንጩ እርሱ ብቻ እንደ ሆነ አወጀ፡፡ ሐዋሪያቱ በአይሁድ ማህበረሰብ ውስጥ ከፍተኛው አካል ፊት ቢቀርቡም ከፈራጆቹ በላይ የሆነውን አምላክ ያገለግሉ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች ተራና ያልተማሩ የገሊላ አሳ አጥማጆች ሆነው የነበራቸው ድፍረትና መተማመን በስፍራው የነበሩ ሰዎችን አስገረመ፡፡ እነዚህ መሪዎች ባያስተውሉትም ሐዋሪያት ልክ የሱስ ቀድሞ እንደተናገረው በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ስለነበር ነው (ማቴ.10፡16-20)፡፡

የተፈወሰው ሰው ሁሉም እንዲያየው በፊታቸው ስለቀረበ የሸንጎው አባላት ተዓምሩን መካድ ባይችሉም ሐዋሪያቱ መስበካቸውን እንዲያቆሙ አስጠነቀቋቸው፡፡ የህዝቡ ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ በሄደ ቁጥር የሐዋሪያቱ መልእክቱ ያስፈራቸው ጀመር፡፡ ትክክለኛ ማስረጃ ማቅረብ ስለተሰናቸውና መከላከል ስለፈለጉ ኢ-ፍትሃዊ የሆነ ውሳኔ እንዲተላለፍ ፈቀዱ፡፡

ጴጥሮስ የተናገረው የመጨረሻ ቃል በሐዋሪያት ስራ መጽሀፍ ውስጥ በአስደማሚነቱ የሚታወስ ንግግር ነው፡፡ «ከእግዚብሄር ይልቅ ለእናንተ መታዘዝ በእግዚአብሄር ፊት ይገባ እንደሆነ እስቲ እናንተ ፍረዱ፤ እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ወደ ኋላ አንልም፡፡» (ሐዋ.4፡19-20)፡፡ ስለ ስልጣን ጥማት እስቲ ያስቡ፡፡ በማንኛውም ደረጃና ሁኔታ ይህ ክፉ ስሜት ምን ያህል አደገኛ መሆኑን ያስቡ፡፡አገልጋይ እንዲሆኑ እንደተጠሩ ክርስትያኖች ለስልጣን ከመጓለል ፈተና መጠበቅ ያለብን ለምንድነው?

**ረቡዕ ሐምሌ 11**

## ሐናንያና ሰጲራ

ንብረትን በሙሉ ማምጣት በቀድሞ ቤተክርስቲያን ውስጥ እንደ ግዴታ የሚቆጠር ነገር አልነበረም፤ ይህም ማለት የቤተክርስቲያን አባል ለመሆን የሚደረግ መስፈርት አልነበረም፡፡ ነገር ግን መላውን የህብረተሰብ ክፍልን በማነቃቃት በለጋስነታቸው ትልቅ ምሳሌ የሆኑ ሰዎች ነበሩ፡፡ ከእነዚህ ምሳሌዎች አንዱ በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ የኋለኛ ክፍል ቁልፍ ሚናን የሚጫወተው በርናባስ ነበር (ሐዋ.4፡36-37)፡፡

ሆኖም ከቤተክርስቲያን ውጪ ያሉ ጥቃት ቤተክርስቲያን ላይ እየደረሰ ባለበት ሰአት በቤተክርስቲያን ውስጥም አሉታዊ ምሳሌ በመሆን የቤተክርስትያንን ህብረት አደጋ ላይ የጣሉ ሰዎችም ነበሩ፡፡

ሐዋ.5፡1-11ን አንብቡ፡፡ ከዚህ ታሪክ የምናገኘው ትምህርት ምንድነው?

ምንም እንኳን ሉቃስ ዝርዝር ጉዳዩን ባይጽፍልንም መሰረታዊው ችግር ሐናኒያና ሰጲራ ገንዘቡን ለማስቀረት መሞከራቸው ሳይሆን በማህበረሰቡ ውስጥ ያደረጉት የማታለል ተግባር መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ሐጢያታቸው እንደው በጥድፊያና በድንገት የተከናወነ ሳይሆን በጥንቃቄ አቅደውና አውቀው «የጌታን መንፈስ ለመፈታተን» (ሐዋ. ሥራ 5፡9) የሰሩት ነገር ነው፡፡ንብረቶቻቸውን ሁሉ ሸጠው ገንዘቡን ለቤተክርስቲያን የማምጣት ግዴታ አልነበረባቸውም፡፡ ነገር ግን ይህንን ለማድረግ ሲወስኑ ምናልባትም ለራሳቸው ጥቅም ብቻ አስበው በለጋስነት ተግባራቸው በወንድሞች መካከል ትልቅ ተፅእኖን ለመፍጠር አስበው ሊሆን ይችላል፡፡

እግዚአብሄር በከፋ ሁኔታ እንዲቀጣቸው ያደረገው ይህ ሊሆን ይችላል፡፡ ቤተክርስቲያን በሙሉ በአንድነት ሆነው መኖርን እንዲጀምሩ ያደረገው የሱስ በቅርቡ ይመጣል የሚለው እምነታቸው ቢሆንም የሐናንያና የሰጲራ ተግባር ቀዳሚ በሆነችው ቤተክርስቲያን ለእግዚአብሄር ታማኝ የመሆንን ተግባር የሚያጎድፍና በአማኞች ዘንድ መጥፎ ተጽእኖ የፈጠረ ነበር፡፡ ሐናንያ ልክ እንደ ሰጲራ(ሐዋ. ሥራ 5፡8) ንስሃ ለመግባት እድል እንደተሰጠው ባናነብም ምናልባትም በአጭሩ ብቻ ስለተፃፈ ሊሆን ይችላል፡፡

መሰረታዊው ነገር ከመጀመሪያው አንስቶ እስከ መጨረሻው ድረስ ያሳዩት ተግባር በሐጢያት የተሞላ ነበር፡፡ምንም እንኳን ሁልጊዜ ወዲያውኑ ባይቀጣንም ሐጢያት በእግዚብሄር ፊት ያለው ቦታ የገዘፈ ነው (ሕዝ.18፡20፤ ሮሜ 6፡23)፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ቅጣቱ መዘግየቱ የእግዚብሄርን ፀጋብዛት ሊያስታውሰን ይገባል (2ጴጥ.3፡9)፡፡

እነዚህ ሁለት የቤተክርስቲያን አባላት እንዳደረጉት የእግዚብሄርን የጸጋ ገደብ ላለመግፋት ምን ያህል ልንጠነቀቅ ይገባናል?

## ሐሙስ                ሐምሌ 12

### ለሁለተኛ ጊዜ መታሰር

ሐዋሪያት ልክ ሐናንያና ሰጲራ ላይ እንደሆነው የእግዚአብሄር ፍርድ እንዲመጣ መጠቀሚያ ከሆኑ የእግዚአብሄር ፀጋ በሐጢያተኞች ላይ እንዲመጣም መጠቀሚያ መሆን ይችላሉ፡፡ በሐይል ተሞልቶ የነበረው የፈውስ አገልግሎታቸው (ሐዋ.5፡12-16) የእግዚአብሄር መንፈስ በእነርሱ እየሰራ እንዳለ ተጨባጭ ማስረጃ ነው፡፡ የጴጥሮስ ጥላ ሳይቀር ሰዎች ላይ አርፎ እንደሚፈውሳቸው መታመኑ የሚገርም ነው፡፡ ከዚህ

ታሪክ ጋር የሚቀራረበው ሌላ ታሪክ የየሱስን የልብሱን ጫፍ ነክታ የተፈወሰቸው ሴት ናት (ሉቃስ 8፡43-44)፡፡ ሉቃስ የጴጥሮስ ጥላ የመፈወስ ሀይል አለው እያለ ሳይሆን ሕዝቡ ግን ይህ ይሆናል ብለው አሰቡ ነው ያለን ፡፡ ምንም እንኳን እንዲህ አይነት የማይመስሉ እምነቶች በስፋት ቢኖሩም እግዚአብሄር ግን ፀጋውን ያድላል፡፡

ሐዋሪያቱ በመንፈስ ቅዱስ የበለጠ በተሞሉ ቁጥር ድንቅና ተአምራት በበዙላቸው ቁጥር የሃይማኖት መሪዎች የበለጠ በቅናት ይነዱ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ሐዋሪያትን ለሁለተኛ ጊዜ እንዲይዟቸው አደረጋቸው(ሐዋ.5፡17-18)፡፡ በተአምር ከእስር ቤት ከወጡና (ሐዋ.5፡19-24) ጴጥሮስ«ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሄር ልንታዘዝ ይገባል!» የሚል ሌላ የድፍረት ቃል ከተናገረ (ሐዋ.5፡29) በኋላ አንዳንድ ባለ ስልጣናት ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ሀይል በስራ ላይ ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ጀመሩ፡፡

ሐዋ.5፡34-39ን አንብቡ፡፡ ገማልያል እንዴት አድርጎ ነው በዛ ሸንጎ መሐል ሐዋሪያትን ከመግደል እንዲታቀቡ ያሳመናቸው?

---

---

ሸንጎውን የተቆጣጠሩት ሰዱቃውያን ሲሆኑ ፈሪሳውያንም በሸንጎ መሐል አነስ ያለ ስልጣን ነበራቸው፡፡ ገማልያል ደግሞ ፈሪሳዊ ሲሆን የህግ ዶክተር ነበር፡፡ በአይሁድ ማህበረሰብ ውስጥ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ሰው ሲሆን «ረቢ» (የኔ መምህር) ብለው ከሚጠሩት ይልቅ «ራባን» (የኛ መምህር) ብለው ነበር የሚጠሩት፡፡ ጳውሎስ ደግሞ ከሱ ተማሪዎች መካከል አንዱ ነበር (ሐዋ.22፡3)፡፡

ገማልያልም በእስራኤል ቀደምት ታሪክ ውስጥ ተከስተው ስለነበሩ ሁለት የአመጽ እንቅስቃሴዎች በማውሳት የተፈጠረውን ግርግርና ያፈሩትን ተከታዮች ብዛት በማስታወስ ተናገረ፡፡ ቢሆንም የዚህ እንቅስቃሴ መሪዎች ሲገደሉ ተከታዮቻቸውም ተበታትነዋል፡፡ ከዚህ ታሪክ ላይ ማስተላለፍ የፈለገው ነገር ቢኖር የክርስትያኖች እንቅስቃሴ መነሻው ሰዋዊ ከሆነ ፈጥኖ ይከስማል፡፡ በሌላ አባባል ሐዋሪያት እንዳረጋገጡት መነሻው መለኮታዊ ከሆነ እንዴት ልትቋቋሙት ይቻላችኃል? ብሎ ነው ምክሩን የለገሳቸው፡፡ ሐዋሪያቱም ተገረፉና ዳግም በየሱስ ስም እንዳይሰብኩ ታዘዙ፡፡

ይህ ታሪክ ስለ መልካም አማካሪ አስፈላጊነትና አጋዥነት ምን ይነግረናል? ምንም ያህል ለመስማት የማንሻው ነገር ቢሆንም ምክርን ለመቀበል ክፍት ሙኖንን የምንማረው እንዴት ነው?

**ዓርብ** | ሐምሌ 13

**ተጨማሪ ጥናት፡-** «እኛ ጌታችን በዚህ ለማገልገል መጥቶ የነበረውን በኋላም አደራ ሰጥቶ የሄደውን የእርሱን ንብረት ለመጠበቅና መሻቱን እንድንፈጽም አምኖ የሰጠን መጋቢዎች ነን፡፡ ወደ ሰማይ ተመልሶ ሲያርግ ሐላፊነቱን የተወልን ለኛ ነው፡፡ እኛም የእርሱን መመለስ በንቃት እንድንጠብቅ ይፈልግብናል፡፡ ለተጣለብን አደራ ታማኞች እንሁን በድንገት ሲመጣ አንቀላፍተን እንዳያገኘን፡፡ » Ellen G.white, Testimonies for the church vol.8, P.37

«ሰዎች ስለገቡት ስለት ቅዱስነትና ለእግዚአብሄር ቃል ስለገቡት ነገር ሊጨነቁ ይገባል፡፡ እንደነዚህ አይነት ቃል ኪዳኖች ሰው ከሰው ጋር እንደሚያደርጋቸው እንኳን አስገዳጅ ተደርገው አይቆጠሩም፡፡ ነገር ግን ይህ ቃል የተገባው ለእግዚአብሄር ስለሆነ ቅድስናውና አስገዳጅነቱ ይቀንሳል? ክርስቲያኖች በህግ አስገዳጅነት ጥላ ስር ባለመደረጉ የገቡትን ቃል ሳያከብሩ ማለፍ አለባቸውን? ከየትኛውም ህግና ደንብ ይልቅ ለእግዚብሄር የገባነው ቃል ኪዳን የበለጠ ያስገድደናል፡፡» *Ellen G.white comments, The SDA Bible Commentry, Vol.6,1056*

## የመወያያ ጥያቄ

1. ከብዙ ነገሮች መካከል የሱስ ሁለት ቅርሶችን ለደቀመዛመርቱ ትቶላቸው ሄደ ፡፡ የርሱን በቅርብ መገለጥ እንዲጠባበቁና አለማቀፋዊ ተልእኮአቸውን እንዲያከናውኑ፡፡ እንዴት ነው እነዚህ ሁለት ነገሮች በተልእኳችን እና ወንጌልን ለአለም ለመስበክ በተጠራነው ጥሪ ላይ ተጽእኖ ሊፈጥሩ የሚችሉት?
2. አንድ ሰው ሲናገር «የሱስ ዛሬ እንደሚመጣ አስበን ልንዘጋጅ ነገር ግን ስራችንን ስንሰራ (የቤተክርስቲያንን ተልእኮ )ደግሞ መቶ አመት ቆይቶ እንደሚመጣ ማሰብ አለብን» ብሏል፡፡ ከዚህ አባባል ላይ የምናገኘው ጥበብ ምንድነው? በህይወት ጥሪያችንስ ውስጥ ተግባራዊ ልናደርገው የምንችለው እንዴት ነው?
3. የየሱስ ህይወት፣ሞት፣ትንሳኤ እና ዳግም ምጻት የስብከታችን ማዕከል መሆን ያለበት ለምንድነው?ደግሞ እንዲህ ብላችሁ እስቲ አስቡት ከዚህ ውጪ ሌላ ምን የምስራች ልንናገር እንችላለን?
4. ከሐናንያና ሰጲራ ታሪክ የሰውን ልብ ማወቅ (መልካምም ይሁን ክፉ) ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ምን እንማራለን?
5. የዘመኑ ገማልያል ናቸው ብላችሁ የምታስቧቸው ሰዎች እነማን ናቸው? ወይም እርስዎ ገማልያል የተጫወተውን ሚና ለመጫወት የሚያስችል ስፍራ ላይ ነዎት? በክፍል ውይይታችሁ ወቅት መልካም ምክርን መቀበልም ሆነ መስጠት ያመጣውን በጎ ነገር ምሳሌን በመጥቀስ ተነጋገሩ፡፡ ከዚህ ምን ልንማር እንችላለን?

# ፋኛ ትምህርት ከሐምሌ 14 - 20

## የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን መሪዎች

ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሳምንት ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡- ሐዋ. ሥራ 6፣ ሐዋ.ሥራ 7፡48፣ ዕብ.5፡11-14፣ ሚኪያስ 6፡1-16፣ ሐዋ.ሥራ 7፣ሐዋ. ሥራ 8፡4-25፡፡

**<u>መታሰቢያ ጥቅስ</u>** ፡-የእግዚአብሔርም ቃል እየሰፋ ሄደ፤ የደቀመዛሙርቱም ቁጥር በኢየሩሳሌም እጅግ እየበዛ ሄደ፤ከካህናትም ብዙዎቹ ለእምነት የታዘዙ ሆኑ"። /ሐዋ. ሥራ 6፡7/

በጴንጤቆስጤ ቀን ራሳቸውን ለጌታ ከሰጡት አብዛኞቹ ሔለናዊያን አይሁዶች ማለትም በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ ግሪካውያንና ሮማውያን የሆኑ አይሁዶች ናቸው /ሐዋ. ሥራ 2፡5፣9-11/፡፡ አይሁዳውያን ተብለው ቢጠሩም በሐዋ. ሥራ 6፡1 ላይ "ዕብራውያን" ተብለው ከተጠሩትና ሙሉ በሙሉ አይሁዳውያን ከሆኑት ጋር ሲታዩ ግልፅ የሆነ ልዩነት ነበራቸው፡፡ ዋናው ልዩነትም በይሁዳ ምድር ይነገር የነበረውን አረማይክ ቋንቋ አለመናገራቸው ነው፡፡

ሌሎችም ብዙ ባህላዊም ሃይማኖታዊም ልዩነቶች ነበሯቸው፡፡ በሌላ አገር የተወለዱ በመሆናቸው ከአይሁድ ወግና ልማድ ጋር እንደ ሃገሩ ተወላጆች ስር የሰደዱ አልነበሩም፡፡ ከቤተ መቅደሱ ሥርዓቶች ጋር እንዲሁም በእስራኤል አገር ብቻ ይተገበሩ ከነበሩት የሙሴ ህግጋት ጋር እምብዛም የተቆራኙ አልነበሩም፡፡

አብዛኛውን እድሜያቸውን በግሪካውያንና ሮማውያን ተከበው ከአህዛብ ጋር ስላሳለፉ ሁሉን አቃፊ የሆነውን የክርስትና እምነት ገፅታ ለመረዳት ይቀላቸዋል፡፡ እንደውም ለዓለም ሁሉ ምስክር እንዲሆኑ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ከግብ ለማድረስ እግዚአብሔር ብዙ ሔለናዊ/ግሪካዊ/ አማኞችን ተጠቅሟል፡፡

ለሐምሌ 21 ሰንበት ለመዘጋጀት የዚህንሳምንት ትምህርት ያጥኑ፡፡

## እሁድ ሐምሌ 15

### የሰባቱ ሹመት

ሐዋ. ሥራ 6፡1ን ያንብቡ፡፡ የግሪካውያን አማኞቹ ማጉረምረም ይዘት ምን ነበር?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

"ማጉረምረሙ የመጣው በየዕለቱ ይከናወን የነበረው ምግብ የማደል አሠራር ላይ ከግሪክ ወገን የሆኑት መበለቶች ችላ ተብለው ስለነበረ ነው፡፡ ማዳላት ከወንጌሉ መንፈስ ተቃራኒ ነበር፤ ሰይጣን ግን ጥርጥርን በመዝራት ተሳክቶለት ነበር፡፡ ጠላት በአማኞች መካከል መከፋፈልን ለማምጣት በሚያደርገው ጥረት ሙሉ ስኬትን እንዳያገኝና ክፍተትን ሁሉ ለማጥፋት ፈጣን እርምጃዎች መወሰድ ነበረባቸው፡፡" Ellen G. white The Acts of Apostles p.88"

ሐዋርያቱ ያመጡት መፍትሔ እነርሱ በጸሎትና በቃሉ ሲተጉ የማዕዱን አገልግሎት ያስተናግዱ ዘንድ ሰባት ሰዎችን ከነርሱ መካከል መምረጥ ነበር/ሐዋ. ሥራ 6፡2-4/፡፡ በሐዋ. ሥራ 6፡2 "ማዕድ" የሚለው ቃልና በሐዋ. ሥራ 6፡4 "ቃሉ" ተብሎ የተተረጎመው ቃል ዲያኮኖና ዲያኮንያ ከሚሉ ተመሳሳይ ሥር ካላቸው ቃላት የመጡ ናቸው፡፡

ይህ "በየእለቱ" ከሚለው መግለጫ ጋር የቀዳሚቷ ቤተክርስቲያንን ሁለት ዋና ዕለታዊ ትኩረቶች ይገልጽልናል:- "ቃሉን" ማስተማርና ህብረት ማድረግ /"ማዕድ"/፡፡ ሁለተኛው በየዕለቱ የሚቆርሱትን እንጀራ፣የጌታ ራትንና አብሮ መጸለይን ይገልፃል፡፡ /ሐዋ. ሥራ 2፡42፣46፣5፡42/፡፡

ይህም ማለት ሐዋርያቱ የክርስቶስን አስተምህሮ በባለ አደራነት ስለተቀበሉ በአብዛኛው ቃሉን በማስተማርና በጸሎት ጊዜያቸውን ሲያሳልፉ ሰባቱ ደግሞ በተለያዩ የቤት ለቤት ህብረቶች ህብረት የማድረግን ጉዳይ ይቆጣጠሩ ነበር፡፡ ኃላፊነታቸው ዛሬ ለዲያቆናት በሰጠናቸው ቦታ ብቻ የተወሰነ አልነበረም፡፡ የቤተክርስቲያኒቱ የመጀመሪያዎቹ መሪዎችም ሆነው ነበር፡፡

ሐዋ ሥራ 6፡2-6ን ያንብቡ፡፡ ሰባቱ ዲያቆናት የተመረጡበትና ለአገልግሎት የተለዩበት ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?______________________________

______________________________________________________________

እጩዎቹ የተለዩት በግብረገብ፣ በመንፈሳዊና በተግባር መለኪያዎች ነበር፤ በሌሎች ዘንድ መልካም ተቀባይነት ያላቸው፣ በጥበብና በመንፈስ የተሞሉ መሆን ነበረባቸው፡፡

ከማህበረሰቡ ባገኙት ማረጋገጫ ሰባቱ ሰዎች በፀሎትና እጅ በመጫን ለዚያ አገልግሎት ተለዩ/ተመረጡ/፡፡ ስርአቱ በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት የማግኘትንና እንደ ዲያቆን ለማገልገል ስልጣን ማግኘትን የሚያመላክት ነበር፡፡

በስልጣን ባሉት ዘንድ ጠብን መዝራት በጣም ቀላል ነው፤ አይደል? እግዚአብሔር በሰጠን አቅም በመካከላችን ሰላምን ለመጠበቅና በተልዕኮአችን ላይ ትኩረት ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው?

| ሰኞ | ሐምሌ 16 |
|---|---|

## የእስጢፋኖስ አገልግሎት

ኃላፊነት ከተቀበሉ በኋላ ሰባቱ በቤተክርስትያን አገልግሎት ብቻ ሳይገደቡ ውጤታማ በሆነ ምስክርነት ላይም ተሳትፈዋል፡፡ በውጤቱም ወንጌል መስፋፋቱን ቀጠለ የአማኞችም ቁጥር ጨመረ/ሐዋ. ሥራ 6፡7/፡፡ ይህ እድገት ሲጀምርም በእርግጥ በቀደምቷ ቤተክርስቲያን ላይ ተቃውሞ መጥቶባታል፡፡ ከዚያ ታሪኩ ለየት ያለ መንፈሳዊ ጥንካሬ ባለው እስጢፋኖስ ላይ ያተኩራል፡፡

ሐዋ. ሥራ 6፡8-16ን ያንብቡ፡፡ እነዚህ ቁጥሮች ስለ እስጢፋኖስ፣ ስለ እምነቱና ስለ ባህሪው ምን ያስተምሩናል?ተቃዋሚዎቹ ያን ያክል እንዲቆጡ ያደረጋቸውና እስጢፋኖስ ሲሰብክ የነበረው ምንድነው?

________________________________________________

________________________________________________

ከግሪክ የመጣ አይሁዳዊ እንደመሆኑ እስጢፋኖስ በኢየሩሳሌም በሚገኙና ግሪካውያን በሚሰበሰቡባቸው ምኩራቦች ወንጌልን ይሰብክ ነበር፡፡ በከተማይቱ እንደዚህ አይነት ብዙ ምኩራቦች ነበሩ፤ ሐዋ. ሥራ 6፡9 ሁለቱን ይጠቅሳል፡፡ አንዱ ከደቡብ ለመጡ ስደተኞች /ከቀሬናና አሌክሳንድሪያ ለመጡ አይሁዶች/ ሌላው ደግሞ ከሰሜን ለመጡ ስደተኞች /ከሲሲሊያና ኢስያ ለመጡት/ ነበሩ፡፡

የክርክራቸው ዋና ጉዳይ የሱስ መሆኑ ባያጠያይቅም በእስጢፋኖስ ላይ የቀረበው ክስ እርሱ ወንጌልን የተረዳበትና ያስተማረበት ሁኔታ ከአይሁድ አማኞች ማስተዋል ያለፈ እንደነበረ ያሳያል፡፡ እስጢፋኖስ የተከሰሰው በሙሴና በእግዚአብሔር ላይ ማለትም በህጉና በቤተ መቅደሱ ላይ የስድብ ቃል ተናግሯል ተብሎ ነው፡፡ በአንዳንድ ነጥቦች በስህተት ቢያስተውሉትም ወይም ቃላቱን አውቀው ቢያጣምሙበትና የሐሰት ምስክር ቢያቆሙበትም ልክ እንደ ኢየሱስ ሁሉ ክሱ ሙሉ በሙሉ ውሸት አልነበረም/ ማርቆስ 14፡58፣ ዮሐ.2፡19/፡፡ እስጢፋኖስ በግልፅ ለቤተ መቅደሱ እየሰጡት የነበረው አክብሮት የበዛ መሆኑን ማውገዙ /ሐዋ. ሥራ 7፡48/ የኢየሱስ ሞት የሚያስተምረንን

ጥልቅ ትምህርት፣ ወዴት እንደሚያመራ ቢያንስ ከቤተ መቅደሱና ከአገልግሎቶቹ አንፃር ያለውን አንድምታ መረዳቱን ይገልፃል፡፡

በሌላ አባባል ምናልባትም ብዙ አይሁድ አማኞች ከቤተ መቅደሱና ከስርዓቶቹ ጋር ተሳስረው/ሐዋ. ሥራ 3፡1፤15፡1፤5፤21፡17-24/ ለመተውም ሲከብዳቸው /ገላ.5፡ 2-4፤ዕብ. 5፡11-14/ እስጢፋኖስና ሌሎች ከግሪክ የመጡ አማኞች የኢየሱስ መሞት መላውን የቤተ መቅደሱን አገልግሎት ማብቃት የሚያመለክት መሆኑን አስተውለው ነበር፡፡

እኛ በምንወዳቸው አመለካከቶች ተጠምደን አዲስ ብርሃን ሲመጣ የተዘጋን እንዳንሆን ጠንቃቆች መሆን ያለብን ለምንድነው?

## ማክሰኞ ሐምሌ 17

### በሸንጎው ፊት

ሐዋ. ሥራ 7፡1-53ንያንብቡ፡፡ እስጢፋኖስ ለከሳሾቹ እያላቸው የነበረው ምንድነው?

---

---

በእስጢፋኖስ ላይ የቀረቡት ክሶች እንዲታሰርና በሸንጐ ፊት እንዲቀርብ አደረጉት፡፡ እንደ አይሁድ ልማድ ከሆነ ህጉና የቤተመቅደሱ አገልግሎቶች ዓለም ከቆመባቸው ሦስት ምሰሶዎች ሁለቱ ነበሩ፡- ሦስተኛው ደግሞ መልካም ሥራ ነበር፡ ፡ የሙሴ ስርዓቶች አልፈዋል ብሎ በግልፅ መናገር በአይሁድነት ውስጥ እጅግ ቅዱስ የነበረው ላይ ጥቃት እንደ መሰንዘርና እግዚአብሔርን እንደ መሳደብ የሚቆጠር ነበር /ሐዋ. ሥራ 6፡11/፡፡

የእስጢፋኖስ ምላሽ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ረጅሙ ንግግር ሲሆን ይህም የጉዳዩን አስፈላጊነት የሚያሳይ ነው፡፡ መጀመሪያ ሲታይ የእስራኤልን ታሪክ በሌላ ቃላት ከመድገም የማያልፍ ንግግር ቢመስልም ይህንን ንግግር ከብሉይ ኪዳን መመሪያና እስራኤልን ወደህጉ ለመመለስ ነቢያቱ እንደተሐድሶ ሰዎች ይዘቱን ከተጠቀሙበት መንገድ ጋር አያይዘን ልናስተውለው ይገባል፡፡ ሕዝቡ በሚወድቁበት ጊዜ ሕዘቡ በቃልኪዳናቸው ስላልፀኑ እግዚአብሔር በራሱ ህዝብ ላይ የሚወስደውን እርምጃ ለመግለፅ በዕብራይስጥ “ሪብ /rib/”የሚለውንና “ቃልኪዳናዊ ሙግት” የሚል ትርጓሜ ያለውን ቃል ይጠቀማሉ፡፡

ለምሳሌ በሚክያስ 6፡1-2 ላይ “ሪብ” /ክርክር/ ሦስት ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ ከዚያም የሲናውን ኪዳን አካሄድ በመከተል /ዘፀ.20-23/ ሚክያስ እግዚአብሔር ለሕዝቡ

ያደረገውን ያስታውሳቸዋል/ሚክያስ 6፡3-5/፤ ቃልኪዳኑ ያስቀመጣቸው ነገሮች መጣሳቸውን/ሚኪያስ 6፡6-12/ እና ጥሰቱ ያመጣቸውን እርግማኖች በመጨረሻ ይነግራቸዋል /ሚክ. 6፡13-16/፡፡

የእስጢፋኖስ ንግግር መነሻም ይህ ይመስላል፡፡ ያደረገውን እንዲገልፅ ሲጠየቅ የቀረበበት ክስ ስህተት መሆኑን ለማስረዳት ወይም ያመነውን ለመከላከል አልሞከረም፡፡ በተቃራኒው ቀደምት ነቢያት ያደርጉት እንደነበረው ድምፁን ከፍ አድርጐ በእስራኤል ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ራሳቸው እንዳመጡ ተናገረ፡፡ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ቀድሞ የነበረውን ግንኙነት ያስታወሳቸው አመስጋኝ አለመሆናቸውንና አመፀኝነታቸውን ለመግለፅ ነበር፡፡

በእርግጥም በሐዋ.ሥራ 7፡51-53 ላይ እስጢፋኖስ ተከሳሽ መሆኑ ቀርቶ የእግዚአብሔር ጠበቃ ሆኖ በመሪዎቹ ላይ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ሙግት አቀረበ፡፡ አባቶቻቸው ነቢያትን በመግደል ጥፋተኛ ከነበሩ የእነርሱ ኃጢያት ደግሞ ጨምሮ ነበር፡፡ "አባቶቻችን" ከማለት /ሐዋ.ሥራ 7፡11፣19፣38፣44፣45/ "አባቶቻችሁ" ወደ ማለት መሻገሩ ወሳኝ ነው፡- እስጢፋኖስ ከህዝቡ ጋር ያለውን አንድነት ትቶ ለኢየሱስ ቀጥ ብሎ ቆመ፡፡ ብዙ ችግር የሚያመጣበት ቢሆንም ቃላቱ ፍርሃት ወይም ቁጭት በውስጣቸው አልነበረም፡፡

እርስዎ ለኢየሱስ ጠንካራና የማይደራደር አቋም ለመያዝ የተፈተኑት መቼ ነበር? ወይስ ወደቁ? ወድቀው ከነበረ መለወጥ ያለበት ምን ይሆን?

## ረቡዕ ሐምሌ 18

### ኢየሱስ በሰማዩ ጉባኤ

ነቢይ /በእብራይስጥ nabi/ ማለት ለእግዚአብሔር የሚናገር ሰው እንደመሆኑ እስጢፋኖስ የእግዚአብሔርን ፍርድ /ሙግት/ በእስራኤል ላይ በተናገረባት ቅፅበት ነቢይ ሆኗል፡፡ ሆኖም የነቢይነት ዘመኑ አጭር ነበር፡፡

የሐዋ.ሥራ 7፡55-56ን ያንብቡ፡፡ የእስጢፋኖስ ራዕይ ትርጉሙ ምን ነበር?

"እስጢፋኖስ እዚህ ጋ ሲደርስ በህዝቡ መካከል ሁከት ተነሳ፡፡ ክርስቶስን ከትንቢቶቹ ጋር ሲያያይዝና ስለ ቤተመቅደሱ ሲናገር ሊቀካህኑ እጅግ የተደናገጠ በመምሰል ልብሱን ቀደደ፡፡ ለእስጢፋኖስ ይህ ማለት ልሳኑ ለዘላለም ሊዘጋ የመሆኑ ምልክት ነበር፡፡ ለተናገረው ነገር የህዝቡን ተቃውሞ ሲመለከት የመጨረሻ ንግግሩን እያደረገ

እንደሆነ ገባው፡፡ ስብከቱን ባይጨርስም የግዱን ደመደመው፡፡” Ellen G. white, The acts of the apostles,p.100

እስጢፋኖስ እግዚአብሔር በነርሱ ላይ ያለውን ሙግት በአይሁድ መሪዎች ፊት ቆሞ ሲያስተላልፍ ኢየሱስ በሰማዩ ሸንጎ ቆሞ ነበር -- ማለትም በሰማዩ ቤተ መቅደስ በአባቱ ቀኝ ቆሞ ነበር፡፡ ይህም በምድር ላይ የሚሆነው ፍርድ በሰማይ በትክክል የሚካሄደው ፍርድ መገለጫ መሆኑን የሚያሳይ ነበር፡፡ እግዚአብሔር በእስራኤል ውስጥ ባሉት አስተማሪዎችና መሪዎች ላይ የሚፈርድ መሆኑን ያሳያል፡፡

ቀድሞ በሐዋሪያት ሥራ በተሰጡት ንግግሮች ውስጥ የነበረው የንሰሐ ጥሪ በዚህ ቦታ የሌለው ከዚህ የተነሳ ነበር /ሐዋ. 2፡38፤3፡19፤5፡31/፡፡

የእስራኤል የእግዚአብሔር ወኪልነት ወደ ፍፃሜው መጣ፤ ማለትም የዓለም መዳን ጥሪ ለአብርሃም ቃል እንደተገባው /ዘፍ.12፡3፤18፡18፤22፡18/ በእስራኤል ሕዝብ በኩል መሆኑ ቀርቶ በኢየሱስ ተከታዮች በኩል እንዲነገር ሆነ፤ አይሁድና አሕዛብ ከኢየሩሳሌም ወጥተው ለዓለም ሊመሰክሩ ነበር /ሐዋ.ሥራ 1፡8/፡፡

ሐዋ.ሥራ 7፡57-8፡1-2ን ያንብቡ፡፡ ሉቃስ የእስጢፋኖስን ሞት የዘገበው እንዴት ነበር?

በድንጋይ መውገር እግዚአብሔርን ለመሳደብ የሚሰጥ ቅጣት ነበር /ዘሌ.24፡14/፡፡ ሆኖም እስጢፋኖስ ሞት ተፈርዶበት ይሁን ወይም በወግ-አጥባቂዎች ግርግር መፍጠር ብቻ ይገደል ግልፅ አይደለም፡፡ የትኛውም ቢሆን በእምነቱ አማካኝነት የተገደለ የመጀመሪያው የየሱስ አማኝ ሆኗል፡፡ ምስክሮቹ ልብሳቸውን በሳኦል እግር ስር ማስቀመጣቸው የእስጢፋኖስ ተቃዋሚዎች መሪ እንደነበረ ይገልፃል፡፡ ሆኖም እስጢፋኖስ ለሚወግሩት ሲፀልይ ለሳኦልም ፀልዩለት ነበር፡፡ ታላቅ ባህሪና የማይነቃነቅ እምነት ያለው ሰው ብቻ ይህንን ሊያደርግ ይችላል፤ በዚህም ክርስቶስ በህይወቱ እንደሚሠራና እምነቱ ታላቅ መሆኑ ድንቅ በሆነ ሁኔታ ታየ፡፡

## ሐሙስ ሐምሌ 19

### የወንጌሉ መዳረስ

በእስጢፋኖስ ላይ የተገኘው ድል በኢየሩሳሌም ባሉ አማኞች ላይ ታላቅ ስደት እንዲጫር ምክንያት ሆነ፡፡ የአሳዳጁ ቡድን መሪና በቤተክርስቲያን ላይ ጥቂት የማይባል ጉዳት ያደረሰው ሳኦል ነበር፡፡ ሆኖም ስደቱ መልካም ነገርን አምጥቷል፡፡

በእርግጥም በይሁዳና በሰማሪያ የተበተኑት አማኞች ወንጌልን ሰብከዋል፡፡ በነዚያ ቦታዎች ወንጌልን እንዲያደርሱ የታዘዙት ትዕዛዝ ያኔ ተፈፀመ /ሐዋ.1፡8/፡፡

ሐዋ 8፡4-25ን ያንብቡ፡፡ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ምን ምን ትምህርት ተገልጿል?

---

---

ሰማርያውያን ከሃይማኖታዊውም ይዘት አንፃር ግማሽ እስራኤላውያን ነበሩ፡፡ አምስቱን የሙሴ መጽሐፍት ብቻ የሚቀበሉ፣ አንድ አምላክ አለ ብቻ ባዮች /ሞኖቴይስትስ ወይም የስላሴን ትምህርት የማይቀበሉ/፣ ግዝረትን የሚያካሂዱና መሲሁን የሚጠብቁ ነበሩ፡፡ ለአይሁዶች የሰማሪያውያን እምነት የተሳሳተ ነበር፣ ማለትም ሳምራውያን በእስራኤል የቃልኪዳን በረከት ውስጥ ተካፋዮች አይሆኑም፡፡

የሰማርያውያን ያልተጠበቀ መለወጥ በኢየሩሳሌም ያለችውን ቤተክርስቲያን ስላስገረመ ሁኔታውን ለማየት ጴጥሮስንና ዮሐንስን ላኩላቸው፡፡ እግዚአብሐር ጴጥሮስና ዮሐንስ እስኪመጡ ድረስ መንፈስ ቅዱስን አለመስጠቱ /ሐዋ.ሥራ 8፡14-17/ ሰማርያውያኑ እንደ ሙሉ የቤተ እምነቱ አባላት ተቀባይነት ሊያገኙ እንደሚገባ ለሐዋርያቱ ለማስረዳት ሊሆን ይችላል/ሐዋ.ሥራ 11፡1-18/፡፡

ሆኖም በዚህ ብቻ አላበቃም፡፡ በሐዋ.ሥራ 8፡26-39 የፊሊጶስንና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በኋላ ለመጠመቅ ጥያቄ ያቀረበውን ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ታሪክ እናገኛለን፡፡ "ከዚያም ሁለቱ አብረው ወደ ውሃው ወረዱ፤ ፊልጶስም ጃንደረባውን አጠመቀው /ሐዋ.ሥራ 8፡38/፡፡

መጀመሪያ ሳምራውያኑ ከዚያም ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣውና ከአይሁድ ውጪ የሆነው ኢትዮጵያዊ ተለወጡ፡፡ ልክ በትንቢት እንደተነገረው ወንጌል የእስራኤልን ድንበሮች አልፎ ወደ አለም እየደረሰ ነበር፡፡ ይህ ሁሉ ግን ገና ጅማሮ ብቻ ነበር፤ እነዚያ ቀደምት አይሁድ አማኞች ያኔ በሚታወቀው ዓለም ሁሉ የኃጢአትን ቅጣት ስለከፈለውና ለሁሉም የመዳን ተስፋን ስለሰጠው የኢየሱስ ሞት ዜና በፍጥነት ሊያደርሱ ነበር፡፡

ጴጥሮስ ሲሞንን "በመራራነት ተሞልተሀ፣ በዐመፅ ሰንሰለት ተይዘሃል"/ሐዋ. ሥራ 8፡ 23/ ብሎ ነገረው፡፡ ለችግሩ የሰጠው መፍትሔ ምን ነበር? በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ለሚኖሩትስ የኛ መፍትሔ ምንድነው?

## ዓርብ | ሐምሌ 20

**ተጨማሪ ጥናት**፡- በኢየሩሳሌም በቤተክርስቲያን ላይ የመጣው ስደት ለወንጌል ሥራ ትልቅ ጉልበትን ሰጥቷል፡፡ ቃሉን የመስበኩ ሥራ በዚያ ቦታ ስኬትን አግኝቶ ነበር፤ ነገር ግን ወደ ዓለም ሁሉ የመሄድን ተልዕኮ ረስተው በዚያ ብዙ እንዳይቆዩ ያሰጋ ነበር፡ ፡ ክፉውን መዋጋት /መቃወም/ የሚቻልበት ኃይል የሚገኘው ወደፊት በሚገሰግስ

አገልግሎት አማካኝነት መሆኑን ረስተው በኢየሩሳሌም ያለችዋን ቤተክርስቲያን ከጠላት ጥቃት ከመጠበቅ የበለጠ ሌላ አስፈላጊ ስራ የለም ብለው ማሰብ ጀመሩ፡ ፡ አዲስ አማኞች ወንጌልን ላልሰሙት እንዲያደርሱ ከማሰልጠን ይልቅ ቀደም ብሎ በተሠራው ሥራ ረክቶ ወደ መቀመጥ አደገኛ ሁኔታ እያዘነበሉ ነበር፡፡ የርሱን ወኪሎች ለሌሎች ሊሰሩ ወደሚችሉባቸው ቦታዎች ለመበተን እግዚአብሔር ስደት በነርሱ ላይ እንዲመጣ ፈቀደ፡፡ ከኢየሩሳሌም ሲወጡ በሄዱበት ሁሉ ቃሉን ሰበኩ፡፡"Ellen white, The Acts of the Apostles, P.105

*የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ከላይ እንደተጠቀሰውና ቀደምቷ ቤተክርስቲያን እንዳጋጠማት ባከናወኑትና በራሳቸው የመርካትን አደጋ በተመለከተ ኤለን ጂ. ኃይት የፃፈችውን በጥንቃቄ ያንብቡ፡፡ በመጀመሪያ በጊዜው ከገነነው አመለካከት በተቃራኒ ብዙ አይሁዳውያን የኢየሱስን መሲህነት ተቀብለዋል፡፡ ከዚያም በላይ አስፈላጊው ነገር እንደ ሕዝብ ከዚህ ምን ትምህርት ልንወስድ ይገባናል? ማድረግ ያለብንን ማለትም ለዓለም መድረስን ትተን ያለንን በመከላከል ብቻ አለመጠመዳችንን በምን ማረጋገጥ እንችላለን?

2. የሐዋርያት ዘመን በአይሁዳውያንና በሰማርያውያን መካከል ለረዥም ዘመናት የቆየ ጥላቻ የነገሰበት ነበር፡፡ አይሁድ የሆነው ፊሊጶስ ስለ ኢየሱስ በሰማርያ መስበኩ ምን ያስተምረናል? እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስትነታችን ባህልና ጎሳ ነክ ግጭቶች የማይነኩን አይደለንም፡፡ መስቀሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁላችንም አንድ ስለመሆናችን የሚያስተምረን እንዴት ነው? የክርስቶስ ሞት ለሁሉም የመሆኑ እውነታ ስለ እያንዳንዱ ሰው ውድ የሆነ ዋጋ ምን ያስተምረናል?

3. ፊሊጶስ ኢትዮጵያዊውን የቀረበው እንዴት ነበር /ሐዋ. 8፡27-30/? ወንጌሉን ለሌሎች ለማድረስ እድሎችን ለመጠቀም የበለጠ ዝግጁዎች መሆን የምንችለው እንዴት ነው?

4. ከሐዋ.ሥራ 6 -- 8 ባለው ክፍል ውስጥ ቤተክርስትያናችን የበለጠ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንድትሠራ ሊረዷት የሚችሉ ምን ትምህርቶችን አገኘን?

# 5ኛ ትምህርት ከሐምሌ 21 - 27

# የጳውሎስ መለወጥ

ሰንበት ከሰዓት

የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብበው ለዚህ ሳምንት ትምርት ይዘጋጁ፡- ሐዋ.26፡9-11፣ ዘዳ.21፡23፣ ሐዋ.9፡1-20፣ 1ኛ ቆሮ.9፡1፣ ገላ.1፡1፣ ሐዋ.9፡20-30፡፡

**<u>መታሰቢያ ጥቅስ</u>** ፡-‹‹ሂድ! ይህ ሰው በአሕዛብና በነገስታት ፊት እንዲሁም በእስራኤል ሕዝብ ፊት ስሜን እንዲሸከም የተመረጠ እቃዬ ነው፡፡›› (ሐዋ.9፡15)

የጠርሴሱ ሳውል (በኋላ ጳውሎስ የተባለው) መለወጥ በሐዋሪያት ቤተክርስቲያን ታሪክ ከተከናወኑ አስደናቂ ክስተቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ሆኖም የጳውሎስ ጥቅም ከመለወጥ ያለፈ ነው፤ ምክንያቱም ለቤተክርስቲያን ባላንጣ ከነበሩት ውስጥ ተለውጦ ቀናተኛ ክርስቲያን በመሆን ጳውሎስ ብቸኛው ሰው አልነበረም፡፡ ከዚያ ይልቅ ግን ወሳኙ ጉዳይ ለወንጌል ሲል ከሰራው ገድል ጋር የሚገናኝ ነው፡፡ ጳውሎስ ለቀደምት አማኞች ወደኋላ የማይል ተቃዋሚ ሲሆን በዚያች ጨቅላ በሆነችዋ ቤተክርስቲያን ላይ ብዙ አስከፊ ነገር ሊፈፅም ይችል ነበር፡፡ ቤተክርስቲያንን ለማጥፋት ከነበረው ቁርጠኝነት በተጨማሪ የባለስልጠኖች እገዛ ከፍተኛ ነበር፡፡ ነገር ግን በደማስቆ መንገድ ላይ ሲሄድ የመጣለትን የእግዚአብሔርን ጥሪ በታማኝነት ሳያመነታ ተቀበለና ከሐዋሪያትም ሁሉ የላቀ ስፍራን ያዘ፡፡ «ከነዚያ መራርና ምህረት የለሽ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አሳዳጆች መሃል ቤተክርስቲያንን የሚጠብቅና ወንጌልን በስኬታማነት የሚያበስር ሰው ብቅ አለ»Ellen G. white, sketches from the life of Paul, P.9::

ጳውሎስ ቀድሞ ሲያደርግ የነበረው ቀዳሚዋን ቤተክርስቲያን የማሳደድ ተግባሩ ያልተገባ ስለመሆኑ በጥልቀት እንዲረዳ ቢያደርገውም የእግዚአብሄር ፀጋ በርሱ ላይ ከንቱ ሆኖ እንዳልቀረ በማሰብ ከልቡ ያመሰግናል፡፡ በጳውሎስ መለወጥ ምክንያት ክርስትና ለዘላለም ተቀየረ፡፡

የዚህን ሳምንት ትምህርት አጥንተው ለ ሐምሌ 28 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡

**እሁድ** **ሐምሌ 22**

## የቤተክርስቲያን አሳዳጅ

ጳውሎስ የግሪክ ሥር ያለው አይሁዳዊ ነበር፡፡ የተወለደውም የኪልቅያ ዋና ከተማ በሆነችው ተርሴስ ነው (ሐዋ.21፡39)፡፡ ሆኖም ወደ እየሩሳሌም መጥቶ በጊዜው ታላቅ በነበረው ፈሪሳዊ አስተማሪ ገማልያል ስር በመማሩ (ሐዋ. 22፡3) በተወሰነ መልኩ ከግሪካዊነት ዘረኝነት አፈንግጧል፡፡ እንደ ፈሪሳዊነቱ ጳውሎስ ወግ አጥባቂ ቢሆንም ቅናቱ ወደአክራሪነት መራው(ገላ.1፡14)፡፡ እስጢፋኖስ ወደ ሞት እንዲሄድ የመራውና በማሳደድ ሂደት ውስጥ ቁልፍ ሚና የተጫወተው ለዚህ ነው ፡፡

ሐዋ.26፡9-11ን አንብቡ፡፡ ጳውሎስ እንዴት ቤተክርስቲያንን ይቃወም እንደነበረ የገለፀው በምን መልኩ ነበር?

---

---

ጳውሎስ በሌላ ስፍራ ላይ ወንጌል ለአይሁድ መሰናከል እንደሆነ ተናግሮአል(1ቆሮ.1፡ 23)፡፡ የሱስ አይሁዶች እንደጠበቁት ንጉስ ሆኖ ስላልመጣና የእግዚአብሄር ቃል እንደሚናገር "በመስቀል የሚሰቀል የተረገመ ነው" (ዘዳ. 21፡23) ስለሚል በመስቀል ላይ የተሰቀለን መሲህ መቀበል አዳገታቸው፡፡ ስለዚህ ለአይሁዳውያን ስቅለቱ በራሱ ከጠበቁት ጋር ስለተጋጨባቸው ቤተክርስቲያን ስለ የሱስ የነበራት ግልፅ መረጃ ራሱ ሀሰት ሆነባቸው፡፡

ሐዋ.9፡1-2 እንደሚተርክልን የተርሴሱ ሳውል አማኞችን ተቃውሞ ወደ እንቅስቃሴ ገባ፡፡ ደማስቆ ከእየሩሳሌም በስተሰሜን አቅጣጫ መቶ ሰላሳ አምስት ማይል የሚርቅና አይሁዶች ተከማችተው የሚገኙበት ትልቅና ወሳኝ ከተማ ነበር፡፡ ከአይሁድ ውጪ የሚኖሩ አይሁዳውያን ዋና መቀመጫቸው እየሩሳሌም (የሸንጎ ስፍራ) በሆኑ ማህበራት የተሳሰሩ ሲሆን ምኩራቦቻቸው ደግሞ ለአገሬው ማህበረሰብ እንደ ዋነኛ ማዕከላት ይቆጠሩ ነበር፡፡ በሸንጎውና በእነዚህ ማህበራት መካከል የማያቋርጥ የደብዳቤ ልውውጥ ያለ ሲሆን ይህንንም ደብዳቤ የሚያደርሰው ሻሊያ " Shaliah" ወይም ልዑክ (የተላከ) ነበር።ይህ ልዑክ ብዙ መንፈሳዊ ሥራዎችን እንዲሠራ በሸንጎው የተሾመ ባለስልጣን ነው፡፡

ጳውሎስ የሸንጎውን መሪ ሊቀ ካህን በደማስቆ ለሚገኙት ምኩራቦች ደብዳቤ ለማድረስ ሲጠይቅ ሻሊያ ሆኖ የየሱስ ተከታዮችን በሙሉ እያሰረ ወደ እየሩሳሌም እንዲያመጣ ስልጣን ተሰጠው ማለት ነው (ከሐዋ. 26፡12 ጋር ያነፃፅሩ)። በግሪኩ "shaliah" ለሚለው

ቃል አቻ የሚሆነው ቃል Apostolos(አፖስቶሎስ)የሚለው ሲሆን ሐዋሪያ(apostle) የሚለው ቃል የመጣውም ከዚህ ቃል ነው፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ የየሱስ ክርስቶስ ሐዋሪያ ከመሆኑ አስቀድሞ የሸንጎው ሐዋሪያ ነበር ማለት ነው፡፡

መቼ ነው እርስዎ ለመጨረሻ ጊዜ (ለማይጠቅም ነገር) ቀናተኛ የሆኑትና በኋላ ግን ሀሳቦን የቀየሩት? ከዚህ የህይወት ተሞክሮዎ ምን ይማራሉ?

**ሰኞ** **ሐምሌ 23**

## በደማስቆ መንገድ ላይ

ሐዋ.9፡3-9ን ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ ወደ ደማስቆ እየተቃረበ ሲመጣ ምን ገጠመው? በሐዋ.9፡5 ላይ የሱስ የተናገረው ቃል ወሳኝነት ምን ያህል ነው (ሐዋ.26፡14ን ይመልከቱ)?

---

---

ጳውሎስና አብረውት የነበሩ ሰዎች ወደ ደማስቆ ሲቃረቡ ያልተጠበቀ ነገር ተከሰተ፡፡ በቀትር ፀሐይ ሃይለኛ ብርሃን በራባቸው አንድ ድምጽም ተናገራቸው፡፡ በትንቢት አንፃር እንደምናየው አይነት ራዕይ ሳይሆን በተለይ ለጳውሎስ የታሰበ መለኮታዊ መገለጥ ነበረ፡፡ አብረውት የነበሩት ብርሃን ያዩ ቢሆንም የታወረው ጳውሎስ ብቻ ነበር፤ ድምጹን ቢሰሙም ነገሩን ያስተዋለው ጳውሎስ ብቻ ነበር፡፡ ብርሃኑ ከሞት የተነሳው የየሱስ መለኮታዊ ክብር ሲሆን ለጳውሎስም በዚያች ቅጽበት ለግሉ ተናገረው(ሐዋ.22፡14)፡፡ በሌላ ስፍራ ጳውሎስ የሱስን እንዳየው በማረጋገጥ የእርሱን ትንሳኤ ለማወጅ ሐዋሪያዊ ስልጣን እንዳለውና በዚህም ከአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ተርታ እንደሚሰለፍ ይናገራል (1ቆሮ. 9፡1፤15፡8)፡፡

ጳወሎስ ከየሱስ ጋር ያደረገው ንግግር ከብርሃኑ በበለጠ ልቡን ሰብሮታል፡፡ ጳውሎስ የሱስ የናዝሬቱን የሚከተሉ አማኞችን ማሳደድ አይሁዳዊነትን ከሚያረክስና አደጋ ላይ ከሚጥል ነገር በመከላከል የእግዚአብሄርን ስራ እያከናውነ እንዳለ በፍጹም ልቡ አምኖ ነበር፡፡ ነገር ግን እርሱ በስራው ያፍር ዘንድ የሱስ ህያው እንደ ሆነ ከማመንም ባለፈ በአማኞች ላይ ያደርስ የነበረው ስቃይና እንግልት በየሱስ በራሱ ላይ እያደረሰ እንደሆነም ተረዳ፡፡

የሱስ ከጳውሎስ ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ጳውሎስ ሊገነዘበው በሚችለውና የግሪክ መነሻ አለው ተብሎ በሚታመን ምሳሌያዊ ንግግር አስጠነቀቀው፡- «የመውጊያውን ብረት ብትረግጥ ላንተ ይብስብሃል»(ሐዋ.26፡14)፡፡ ምስሉ ልክ በቀንበር ውስጥ ያለ

በሬ ከቀንበሩ በሌላ አቅጣጫ ለመሄድ ሲጣጣር የሚሆነውን ትዕይንት ይገልጻል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ይህ እንስሳ የበለጠ ራሱን እየጎዳ ይመጣል፡፡

ይህ አባባል በጳውሎስ አዕምሮ ውስጥ የነበረውን ሙግት የሚያሳይ ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ስራ እንደሆነ በማረጋገጥ(ዮሐ.16፡ 8-11) በእስጢፋኖስ ላይ የሆነውን ነገር ያስታውሰናል፡፡ «ሳኦል እስጢፋኖስ ወደ ሸንጎ ቀርቦ እንዲፈረድበት በማድረግ ትልቁን ድርሻ የተወጣ ሲሆን ከሰማዕቱ ጋር የእግዚአብሄርን መገኘት የሚያሳዩ አስደናቂ ማስረጃዎች የየሱስን ተከታዮች በማሳደድ ፅድቅ ይገኛል ብሎ ማመኑን እንዲጠራጠር አደረገው፡፡ አዕምሮው እረፍት እስኪያጣ ደረስ ተበጠበጠ፡፡ በዚህ ግራ መጋባት ውስጥ ሆኖ ጥበብና ቅን ፍርድ አላቸው ብሎ ሙሉ መተማመን ለጣለባቸው ሰዎች አቤት ሲል ጥያቄ አቀረበ፡፡ ከገዥዎችና ካህናት ጋር ባደረገው ክርክርም እስጢፋኖስ የእግዚአብሄርን ስም የተሳደበ ሰው እንደሆነ አመነ፡፡ ሰማዕቱ የሰበከው ክርስቶስ አጭበርባሪ እንደነበርና በትልልቅና ቅዱስ ስፍራ ያሉ አገልጋዮች ትክክል እንደሆኑ አመነ፡፡» Ellen G. white, The acts of the Apostles, Pp.112,113፡፡

ህሊናችሁን በደንብ ማድመጥ ብልህነት ያለው አካሄድ የሆነው ለምንድን ነው?

## ማክሰኞ ሐምሌ 24

## የአናንያ ጉብኝት

ሳኦል እየተነጋገረ ያለው ከየሱስ ጋር መሆኑን ሲረዳ የሱስ በርሱ እንዲሰራ እድል የሚሰጥን ጥያቄ ጠየቀ «ጌታ ሆይ ምን ላድርግ?» (ሐዋ. 22፡10)፡፡ ጥያቄው እስከዚያች ሰዓት ድረስ ስላደረጋቸው ነገሮች መፀፀቱን ቢያመለክትም ከዚህ በላይ ግን ከዚያን ሰአት አንስቶ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሱስ እንዲመራው ፈቃደኛ መሆኑን አመላካች ነበር፡፡ ሳኦል ወደ ደማስቆ ከተወሰደ በኋላም ተጨማሪ መመሪያ ለመቀበል መጠበቅ ነበረበት፡፡

በሐዋ.9፡10-19 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ሲተርክልን ጌታ የደማስቆው ሳኦል ሐዋሪያው ጳውሎስ ሆኖ ለሚኖረው አዲስ ህይወት እንዴት እንዳዘጋጀው ይናገራል፡፡ የሱስ በራዕይ አናንያ ጳውሎስን ሄዶ እንዲጎበኘውና አይኑም ያይ ዘንድ እጁን እንዲጭንበት ተናገረው፡፡ አናንያ ደግሞ ቀድሞውኑ ሳኦል ምን አይነት ሰው እንደሆነና ወገኖች በብዙ እንዲሰቃዩና ብሎም ህይወታቸውን እንዲያጡ ማድረጉን ያውቃል፡፡ ሳኦል ወደ ደማስቆ ለምን አላማም እንደሚሄድ ተነግሮታል በዚህ የተነሳ ወደርሱ ሄዶ የመጀመርያው የጥቃቱ ሰለባ መሆን አይፈልግም፡፡ በዚህ ምክንያት ማቅማማቱ ሊስተዋል የሚገባ ነው፡፡

ነገር ግን አናንያ ያላወቀው ነገር ቢኖር ሳኦል ከየሱስ ጋር ፊት ለፊት መገናኘቱንና በዚህም የተነሳ ህይወቱ ለዘላለም መቀየሩን ነው፡፡ ይህንን ባይረዳም አናንያን ይድነቅህ ሲለው ጳውሎስ ለሸንጎው ከመስራት ይልቅ ለየሱስ ይሰራ ዘንድ ተጠርቷል፡፡ ይህም ማለት ከዚህ በኋላ ሳኦል የሸንጎው ሐዋሪያ ሳይሆን ወንጌልን ለአይሁድና ለአህዛብ የሚያደርስ ለየሱስ የተመረጠ ዕቃ ሆኗል ማለት ነው፡፡

ገላ.1፡1፤11-12ን ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ ሐዋሪያዊ አገልግሎቱን በተመለተ ከምን የመነጨ እንደሆነ ተናገረ?

---

---

በገላትያ መጽሐፍ ጳውሎስ መልእክቱን የተቀበለውና ሐዋሪያነቱን ያገኘው ከሰው ሳይሆን ቀጥታ ከየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡ ሆኖም አናንያ በጳውሎስ መጠራት ውስጥ የተጫወተው ሚና ይህንን ይቃወማል ማለት አይደለም፡፡ የአናንያ ጉብኝት ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ላይ ከየሱስ የተቀበለውን ተልእኮ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

እውነት ለመናገር በሳኦል ላይ የታየው የህይወት ለውጥ አስደናቂ ከመሆኑ የተነሳ በሰብአዊ ተፅዕኖ ምክንያት እንደመጣ ለማሰብ የማይቻል ነው፡፡ የየሱስ ቀንደኛ ተቃዋሚ የነበረው ሰው እንዴት ብሎ በድንገት ሁሉን ትቶ ማለትም ዝናውን፣ ቀድሞ የነበረውን ስራና የፀና እምነቱን ትቶ የሱስን እንደ አዳኙና ጌታው በመቀበል የተሰጠ አስደናቂ ሐዋርያ ስለመሆኑ ሊገልፅልን የሚችለው መለኮታዊ ሀይል ብቻ ነው፡፡

የሳውል መለወጥ የእግዚአብሄርን አስደናቂ ፀጋ የገለጸው በምን መንገድ ነው? በህይወትዎ አይመለሱም የምትሏቸው ሰዎች ሳይቀር ወደ እውነተኛው እምነት ሊመጡ እንደሚችሉ ይህ ታሪክ ምን ያስተምራል?

**ረቡዕ ሐምሌ 25**

## የጳውሎስ አገልግሎት ጅማሮ

ሐዋ.9፡19-25 እንደሚያስቀምጥልን ጳውሎስ ከተቀየረ በኋላ ወደ እየሩሳሌም ከመመለሱ በፊት ለጥቂት ጊዜ በደማስቆ ቆይቷል(ሐዋ.9፡26) ፡፡ እንደውም ገላ.1፡ 17 ላይ ጳውሎስ ሲያክል ወደ እየሩሳሌም ከመመለሱ አስቀድሞ ለብቻው ጥቂት ወደኖረበት አረብ አገር ሄዷል፡፡ «በዚያ ገለልተኛ ሆኖ በበረሃ ሲኖር ጳውሎስ ለማጥናትና ለማሰላሰል ሰፊ ጊዜን አገኘ፡፡» Ellen. G white, The Acts of the Apostles, P.125::

ሐዋ.9፡20-25ን ያንብቡ፡፡ ሉቃስ ጳውሎስ በደማስቆ የነበረውን አገልግሎት እንዴት አደርጎ ነበር የገለጸው?

---

---

ጳውሎስ ከሊቀ ካህናት የተቀበለውን ደብዳቤ ይዞ ከየእሩሳሌም ለቆ የሄደበት አላማ ያነጣጠረው በደማስቆ ምኩራቦች ጥገኛ ሆነው እየኖሩ ባሉ አይሁድ አማኞች ላይ ነው (ሐዋ. 9፡2)፡፡ አሁን ከአረብ አገር ከመጣ በኋላ ግን ወደነዚያ ምኩራቦች መጣ፡ ፡ አማኞችን ለማሰር ሳይሆን እንደውም ቁጥራቸውን ለመጨመር፤ የሱስ አሳሳች ነው ብሎ ስሙን ለማጥፋት ሳይሆን ነገር ግን የእስራኤል መሲህ እንደሆነ ለማወጅ ወደነርሱ መጣ፡፡ አሳዳጃቸው እንደሆነ የሚያውቁት ሰው ስለ የሱስ ሲመሰክር ሲሰሙ በአዕምሮአቸው ውስጥ ምን ይመላለስ ይሆን? የጠርሴሱ ሳኦል ስለ መለወጡና ለቤተክርስቲያን ስላደረገው ነገር በማሰብ ከመደመም በቀር ምን ሊያደርጉ ይችላሉ? (ይህ አዲስ የተለወጠ ሰው የኋላ ኋላ ስለሚፈጥረው ትልቅ ተጽእኖ ምናልባት ማናቸውም ላይገምቱ ይችላሉ)፡፡

አንዳንድ ጳውሎስን ይቃወሙ የነበሩ ሰዎች ኃሳቡን ሊሞግቱ ባይቻላቸውም ህይወቱን ግን ሊያጠፉ አድመውበት ነበር፡፡ ጳውሎስ ታሪኩን እንደገለፀው (2ቆሮ.11፡32-33) የርሱ ባላንጣዎች በስፍራው በሚገኙ ባለ ስልጣናት ፊት ስሙን በማውገዝ አለማቸውን ለማሳካት አልመው ነበር፡፡ ነገር ግን አማኞች ጳውሎስን በከተማው አጥር በመስኮት በኩል በቅርጫት አድርገው አስመለጡት፡፡

ጳውሎስ ተግዳሮት እንደሚገጥመው ቀድሞውኑ ተገንዝቧል (ሐዋ. ሥራ 9፡16)፡ ፡ተቃውሞ፣ ስደት እና ስቃይ ከተለያየ አቅጣጫ በሚያደርገው አገልግሎቱ ላይ ሳይቋረጥ እንደሚመጣበት ያውቃል፡፡ ነገር ግን ከየሱስ ጋር በጀመረው አዲስ ህይወት በእያንዳንዱ እርምጃው የሚገጥሙት ግድድሮሾች እምነቱን አላናወጡትም፤ ተግባሩንም አልገቱትም(2ቆሮ.4፡8-9)፡፡

ብዙ ተግዳሮትና ተቃውሞ ቢደርስበትም ጳውሎስ ግን ፈጽሞ ተስፋ አልቆረጠም፡፡ በተስፋ መቁረጥ እና ተቃውሞ መሃል ሆነን በእምነታችን ፅኑዎች መሆን እንደሚገባን እንዴት ልንማር እንችላለን?

ሐሙስ ሐምሌ 26

## ወደ እየሩሳሌም መመለስ

ከደማስቆ ካመለጠ በኋላ ጳውሎስ አሳዳጅ ሆኖ ወደ ወጣበት እየሩሳሌም ለመጀመሪያ ጊዜ ተመለሰ፡፡ ይህ የሆነው ከተለወጠ ከሦስት አመታት በኋላ ነው(ገላ.1፡18)፡፡ ችግሮች ከቤተክርስቲያን ውስጥና ውጪ እየገጠሙት ባለበት ወቅት ወደ እየሩሳሌም መመለስ ቀላል አልነበረም፡፡

ሐዋ.ሥራ 9፡26-30ን ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ ወደ እየሩሳሌም ሲደርስ ምን ገጠመው?

---

---

በእየሩሳሌም ጳውሎስ ከሐዋሪያት ጋር አብሮ ለመቀላቀል ጣረ፡፡ ክርስትያን ሆኖ ለሦስት አመታት ከቆየ በኋላ ቢመጣምሐዋሪያት ልክ ቀደም ብሎ አናንያ እንዳደረገው መለወጡን የተመለከቱት በጥርጣሬ አይን ነበር፡፡ ነገሩ ሆን ተብሎ የተቀነባበረ ድራማ አድርገው በማሰብ ስጋት ውስጥ ገቡ፡፡ በቆጵሮስ ይኖር የነበረው ሌዋዊው በርናባስ (ሐዋ.4፡36-37) ነበር የሐዋሪያትን ተቃውሞ ጥሶ ጳውሎስን ወስዶ ያስተዋውቃቸው፡፡ እነርሱም ቢሆኑ የእውነቱን መሆኑን ሲረዱ እግዚአብሄር በጳውሎስ ላይ ስለሰራው ስራ ተደንቀዋል፡፡

እንዲህ አይነት ተቃውሞ ሙሉ በሙሉ ይወገዳል ማለት አይቻልም፡፡ ጳውሎስ ቀድሞ ቤተክርስቲያንን ሲያሳድድ ስለነበረ ባይሆን እንኳን በሰበከው ወንጌል ምክንያትየማይቀር ነበር፡፡ የእስጢፋኖስንም ታሪክ ስናይ አይሁዳውያን አማኞች ሐዋሪያትን ጨምሮ በብሉይ ኪዳን ስርአት በተለይም መስዋዕት የማቅረብ ስርአት በየሱስ የመስቀል ሞት መደምሰሱን የሚያምኑትን መሰረታዊ የክርስትና እምነት ለመረዳት እጅግ ዘግይተው ነበር፡፡ ጳውሎስ በይሁዳ ቤተክርስቲያን የነበረው የጠበቀ ግንኙነት ከበርናባስ በተጨማሪ በጥንት ግሪክ ይኖሩ ከነበሩት አማኞች ጋር ነበር፡፡ ከሰባቱ መካከል አንዱ ሆኖ የተመረጠው ፊሊጶስ (ሐዋ.21፡8) እንዲሁም የቆጵሮሱ ሚናሶንም ይገኝበት ነበር (ሐዋ.21፡16)፡፡ ከአያሌ አመታት በኋላ የእየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መሪዎች ጳውሎስን እስጢፋኖስ ሲሰብክ የነበረውን ትምርህት ይሰብካል በሚል ክስ አቀረቡበት (ሐዋ.21፡21)፡፡

ለ15 ቀናትበእየሩሳሌም በቆየባቸው ቀናት (ገላ.1፡18) ጳውሎስ ከጥቂት ጊዜያት በፊት እስጢፋኖስን ለማስወገር ላነሳሳቸውና አማኝ ላልሆኑት አይሁዳውያን በግልጽ ወንጌልን ለማካፈል ወሰነ፡፡ ልክ እንደ እስጢፋኖስ ጥረቱ ለህይወቱ እስኪያሰጋው ድረስ ከባድ ተቃውሞን አመጣበት፡፡ የሱስ በራዕይ ተገልጦ ለደህንነቱ ሲል እየሩሳሌምን ለቆ እንዲሄድ ተናገረው (ሐዋ.22፡17-21)፡፡ በወገኖች እገዛ ወደ ቄሳርያ ከተማ ሄደ ከዛም ይኖርበት ወደነበረበት ከተማ ወደ ኪልቂያ በመሄድ የወንጌል ጉዞውን ከመጀመሩ በፊት ለብዙ አመታት ቆየ፡፡

## ዓርብ | ሐምሌ 27

**ተጨማሪ ጥናት**፡-« በጦርነት አውድማ የተሰዋ ጄነራል ለራሱ ወታደሮች ሽንፈት ቢሆንም ሞቱ ለጠላቶቹ ምንም ያህል ተጨማሪ ጥንካሬን አያመጣላቸውም፡፡ ይህ የታወቀ ሰው የተቃዋሚውን ሃይል ሲቀላቀል አገልግሎቱ ብቻ አልነበረም የጠፋው የተቀላቀላቸው ሰዎች ግን በርሱ መኖር ተጠቃሚ ሆኑ፡፡ የጠርሴሱ ሳውል ደማስቆ መንገድ ላይ ሳለ በቀላሉ በጌታ ሀይል ተመቶ ሊሞት እና አሳዳጅ የነበሩ ሃይሎች ጥንካሬያቸው ሊዳከም ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን እግዚአብሄር በበጎ ፈቃዱ የጳውሎስን ህይወት መታደግ ብቻ ሳይሆን ለወጠውና ጀግናውን ከጠላት ወገን ወደ የሱስ ወገን አሸጋገረው፡፡»-Ellen G. white , The Acts of the Apostles, P.124.

« ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ወደ አህዛብ ሁሉ ሄደው እንዲሚያስተምሩ አዘዛቸው፡፡ ነገር ግን ቀድሞ ከአይሁድ የተማሩት ትምህርት ስለነበር የጌታቸውን ቃል ሙሉ በሙሉ ለመያዝ ተቸግረው ነበር፡፡ ስለዚህም ወደ ተግባር ለመግባት ከብዙ አመታት በኋላ ነበር ጌታ ወደ ሰማይ ሲያርግ የየሱስን ቃላት በሙላት ለመረዳት አዕምሮአቸው ክፍት መሆን የጀመረውና አህዛብ ብሎም አይሁዳውያንን ይለውጡ ዘንድ ስራ መስራትን የጀመሩት፡፡» Ellen. G wihte, sketches form the life of paul, P38.

*የመወያያ ጥያቄዎች*

1. በደማስቆ መንገድ ላይ የሱስ ጳውሎስን በጠየቀው ጥያቄ ላይ ሙሉ ትኩረትዎን ያድርጉ « ለምን ታሳድደኛለህ» (ሐዋ.9፡4)፡፡ ለጳውሎስ ይህ ጥያቄ የሱስ የናዝሬቱ በእርግጥም ከሞት ስለመነሳቱ ያረጋገጠለት ክስተት ነበር፡፡ ከዚህ በላይ ግን በየሱስ እና በቤተክርስቲያን መካከል ያለውን መንፈሳዊ ተዛምዶ ያመለክታል (ማቴ.25፡34-45ን ተመልከቱ)፡፡ የሚያሳየን ነገር ግልጽ ነው ቤተክርስቲያን ላይ የደረሰ ጉዳይ በሙሉ የሱስ ላይ የደረሰ ጉዳት ነው፡፡ ተግባራዊ በሆነ ሁኔታ ስንቃኘው ዛሬ ይህ ለኛ ምን አይነት ትርጉም አለው?

2. ለየሱስ መመስከር ለየሱስ ሲሉ ስቃይ መቀበልን ያካትታል፡፡ የግሪኩ ስርወ ቃል « መመስከር » የሚለውን ቃል ከስቃይ ጋር ያዛመደው በአጋጣሚ አይደለም፡፡ ለየሱስ ሲሉ ስቃይ መቀበል ማለት ምን ማለት ነው?

3. የጥንት የላቲን አባባል አለ «አስተውል ዘንድ አምናለሁ» የሚል ይህ አባባል በጠርሴሱ ሳውል ላይ ከደረሰው ነገር አኳያ ምን እንድናስተውል ያደርገናል? ይህም ማለት ጳውሎስ ከመለወጡ አስቀድሞና በየሱስ ከማመኑ በፊት ምንም የተረዳው ነገር አልነበረም ፡፡ በህይወቱ ያንን ልምምድ ከተለማመደ በኋላ ነው ነገሩን የተነዘበው፡፡ ግልጽ የሆነውን እውነት ማመን የማይፈልጉ ሰዎችን ለማሰብ ተስፋ እንዳንቆርጥ ይህ ታሪክ ምን ያስተምረናል?

# 6ኛ ትምህርት ከሐምሌ 28 - ነሐሴ 4

# የጴጥሮስ አገልግሎት

ሰንበት ከሰዓት

*ለዚህ ሳምንት ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ:- ሐዋ. ሥራ 9፡32-43፣ ሐዋ.ሥራ 10፡9-16፣ ኤፌ.2፡11-19፣ ሐዋ.ሥራ 11፡1-26፣ ሐዋ. ሥራ 12፡1-18።*

**መታሰቢያ ጥቅስ**:-"ጴጥሮስም እንዲህ ሲል መናገር ጀመረ ፤ "እግዚአብሔር ለማንም እንደማያዳላ በእርግጥ ተረድቻለሁ፣ ነገር ግን እርሱን የሚፈሩትንና ጽድቅን የሚያደርጉትን ሁሉ ከየትኛውም ወገን ቢሆኑ ይቀበላቸዋል።" /ሐዋ. ሥራ 10:34-35/

ጳውሎስ ወደ ተርሴስ በመሄዱ ጴጥሮስ ሉቃስ በፃፈው የቀደምቷ ቤተክርስቲያን ትረካ ውስጥ እንደገና ዋና ገፀ-ባህሪ ሆኗል፡፡ ጴጥሮስ በይሁዳ ውስጥና በአካባቢዋም በየቦታው እየሄደ የማገልገል ኃላፊነቱን ሲወጣ እንመለከታለን፡፡ የሐዋሪያት ስራ መጽሐፍ በዚህ ቦታ የሁለት አጫጭር ተዓምራትን ታሪክ ይነግረናል፣ የኤንያ መፈወስና የጣቢታ ከሞት መነሳት፡፡ ከዚያም በምዕራፍ 10 የቆርኔሊዎስ ታሪክ ይከተላል፡፡

የአህዛብ መለወጥ በሐዋሪያት ቤተክርስቲያን ታሪክ ትልቅ ክርክርን ያስነሳ ነበር፡፡ ከቆርኔሊዎስ መጠመቅ በኋላ የተካሄዱት ውይይቶች ችግሮቹን በሙሉ ባይፈቱም የመንፈስ ቅዱስ መውረድ፣ በጴንጤቆስጤ ቀን የተገኙት ሰዎች ጴጥሮስንና በኢየሩሳሌም የነበሩትን ወንድሞች የወንጌሉ በረከት ለአይሁድ ብቻ የተገደበ እንዳልሆነ ለማሳመን ጠቅመዋል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በአንፆኪያ የነበረችው ቤተክርስቲያንም ወደ አህዛብ ለመሄድ ጉዞ ጀምራ ነበር፡፡

የዚህ ሳምንት ጥናት በተጨማሪ በንጉስ ሔሮድስ ዘመን ስለተነሳና ጥቂት ጊዜ ስለቆየው የስደት ጊዜ፣ በሳኦል ከተቀጣጠለው ስደት በተረፉት በሐዋሪያት ላይ ስለፈጠረው ተፅዕኖ ይዳስሳል፡፡

ለነሐሴ 5 ሰንበት ለመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ያጥኑ፡፡

## እሁድ ሐምሌ 29

# በልዳና በኢዮጴ

ጴጥሮስ በይሁዳ የባህር ዳርቻዎች አካባቢ ያሉትን ክርስትያን ህብረተሰቦች እየጐበኘ ነበር፡፡ ምናልባትም አላማው ከቃሉ ለማስተማር /የሐዋ. ስራ 2፡42/ ቢሆንም እግዚአብሔር ግን በኃይል ተጠቅሞበት ልክ በኢየሱስ በራሱ እንደተፈፀሙት ዓይነት ተዓምራት እንዲያደርግ ተጠቀመበት፡፡

ሐዋ. ሥራ 9፡ 32-35ን ያንብቡ፡፡ ኢየሱስ በሉቃስ 5፡17-26 ላይ ያደረገውና በኤንያ መፈወስ ታሪክ ውስጥ ምን የሚያመሳስል ነገር እንመለከታለን?

---

---

ከነዚህ ባለታሪኮች የእምነት ፅናት በተጨማሪ ይህ ተዓምር በቅፍርናሆም የተፈወሰውን ሽባ ሰው ታሪክ ያስታውሰናል /ሉቃስ 5፡17-26/፡፡ ስለ አልጋውም የተነገረው ዝርዝር ተመሳሳይ ነበር፡፡

ሆኖም ዋናው ነገር የኤንያ መፈወስ በልዳ ከተማ ብቻ ሳይሆን በሰሮና በሚኖሩትም ዘንድ ተፅዕኖ ማሳደሩ ነው፡፡ የፈውሱ ሁኔታ እውነት መሆኑን አረጋግጠው ብዙ ሰዎች ወደ ጌታ ተመለሱ፡፡

ሐዋ. ሥራ 9፡36-43ን ያንብቡ፡፡የጣቢታን (ዶርቃ) ከሞት የመነሳት ታሪክ ይመልከቱ፡፡ ስለ እርሷ የተለየ ነገር የሆነው ምን ነበር?

---

---

በአረማይክ ቋንቋ "አጋዘን" የሚል ትርጉም ያለው ስም ያላት ጣቢታ (በግሪክኛ ዶርቃ) በክርስቲያናዊ በጎ-አድራጎቷ የተነሳ በጎረቤቶቿ ዘንድ ተወዳጅ የሆነች አማኝ ነበረች፡፡ የርሷ ከሞት መነሳት በኢየሱስ አማካኝነት ጴጥሮስ እያየ ከሞት ከተነሳችው የኢያኢሮስ ሴት ልጅ ከሞት መነሳት ጋር የሚመሳሰል ነው (ሉቃስ 8፡41-42፤49-56)፡፡ ልክ እንደ ኢየሱስ እርሱም ሁሉም ሰው እንዲወጣ ጠየቀ (ማርቆስ 5፡40ን ይመልከቱ)፡፡ ከዚያም ተንበርክኮ ፀለየና የሞተችዋን ሴት "ጣቢያ ሆይ ተነሺ " (ሐዋ. ሥራ 9፡40) ብሎ አዘዛት፡፡

ሐዋሪያቱ ብዙ ተዓምራት እንዳደረጉ ብንናገርም በነርሱ እጅ እየሠራ የነበረው የእግዚአብሔር እጅ ነበር (ሐዋ. ሥራ 5፡12)፡፡ ከራሱ ከኢየሱስ ተዓምራት ጋር መመሳሰሉ (የሚያስተምረን) መጠቀሚያው ማንም ሆነ ማን ዋናው መለኪያ

ያ ሰው ለእግዚአብሔር ያለው መሰጠት መሆኑን (ዮሐ. 14፡12) በዚያን ዘመን ለነበረችው ቤተክርስቲያንና ለእኛ ለማስታወስ ነው፡፡ እግዚአብሔር ስለ ወንጌሉ እኛን እንዲጠቀምብን ሙሉ በሙሉ ስንፈቅድለት ታላላቅ ነገሮች ይከናወናሉ፡፡ ጴጥሮስ ጣቢታን ከሞት ማስነሳቱ ሳይበቃ በዚያ ተዓምር የተነሳ በኢዮጴ የሚኖሩ ብዙዎች ወደጌታ ተመልሰዋል፡፡ (ሐዋ. ሥራ 9፡42)፡፡

አንዳንድ ሰዎች ልክ እንደዚህ አይነት ተዓምር ቢመለከቱ ኖሮ ያምኑ እንደነበር ያስባሉ፡፡ ምንም እንኳን አንዳንድ ጊዜ ተዓምራት ሰዎችን ወደማመን ቢመሩም መጽሐፍ ቅዱስ ተዓምራትን አይተው ነገር ግን ባላመኑ ሰዎች ታሪክ የተሞላ ነው፡፡ ስለዚህ እምነታችን መመስረት ያለበት በምን ላይ ነው?

## ሰኞ ሐምሌ 30

### በቆርኔሌዎስ ቤት

ጴጥሮስ ስምዖን ከተባለ ከአንድ ቁርበት ፋቂ ጋር በኢዮጴ ቆየ (ሐዋ. ሥራ 9፡ 43)፡፡ ከኢዮጴ 25 ማይል (40 ኪ.ሜ.) ርቀት ላይ በምትገኘው በቂሳሪያ ቆርኔሌዎስ የሚባል የሮም መቶ አለቃ ይኖር ነበር፡፡ እርሱና ቤተሰቡ እግዚአብሔርን ከልባቸው የሚያመልኩ ነበሩ፤ ወደ አይሁድነት ግን በይፋ አልገቡም - ማለትም ቆርኔሌዎስ ያልተገረዘ አህዛብ ነበር፡፡ ከእግዚአብሔር በተቀበለው ራዕይ መልዕክተኞችን ወደ ኢዮጴ ልኮ ጴጥሮስን ወደቤቱ እንዲጋብዝ ተነገረው (ሐዋ. ሥራ 10፡1-8)

ሐዋ. ሥራ 10፡9-16፣28፣34፣35ን ያንብቡ፡፡ ጴጥሮስ ምን ተመለከተ? እንዴትስ ተረጎመው?

---

---

የጴጥሮስ ራዕይ ስለ ምግብ ሳይሆን ስለ ሰዎች መሆኑን ማወቅ ጠቃሚ ነው፡ ፡ አዎን እኩለ ቀን ገደማ ነበር፤ ጴጥሮስም ርቦት ነበር፤ ያ ድምፅም የሚያያቸውን አርዶ እንዲበላ ነግሮታል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ይህንን ራዕይ የላከው በንፁህና ርኩስ ምግብ መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥፋት ሳይሆን ወንጌል ሁሉንም የሚያቅፍ መሆኑን ለጴጥሮስ ለማስተማር ነው፡፡

ራዕዩ ጴጥሮስ አህዛብን የማግለል ልማዱን እንዲያቆም በግልፅ የተቀመጠ ነበር፡፡ ጴጥሮስ የሚያስበው ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ገብቶ ከርሱ ጋር ካመለከ ራሱን እንደሚያረክስና በቤተ መቅደስ በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም የማይገባው እንደሚሆን ነበር፡፡ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን በይሁዳና አካባቢዋ የነበሩ አይሁዶች ካልተገረዙት አህዛብ ጋር አይቀላቀሉም ነበር፡፡

ችግሩ በጊዜው የነበረው ስነመለኮታዊ አስተምሮ ሲሆን አይሁዶችን ከአህዛብ ለይቶ እንደ ሀገር የመኖራቸውን ዋና ምክንያት ማለትም እውነተኛውን አምላክ ለዓለም ማሳወቅን እንዲዘነጉ አድርጎ አቅጣጫ አስቀይሯቸዋል፡፡

መገረዝ የአብርሐማዊው ቃልኪዳን ምልክት ስለነበር ያልተገረዙ አህዛብ በንቀት አይን እየታዩ ይገለሉ ነበር፡፡ ተገርዘው አይሁዳዊ ካልሆኑ በስተቀር የቃልኪዳኑ በረከቶች ተካፋይ እንደማይሆኑ ይታሰብ ነበር፡፡ ይህ ሐሳብ ቀደምት አማኞች በጊዜ ሂደት እያስተዋሉ እንደመጡት ከኢየሱስ ሞት ሁሉን አቀፍነት ጋር የማይሄድ ነበር፡፡

ቲቶ 2፡11ን ገላቲያ 3፡26-28ንና ኤፌሶን 2፡11-19ን ያንብቡ፡፡ እነዚህ ጥቅሶች የወንጌል መልዕክት ሁሉን አቀፍ ስለመሆኑ ምን ያስተምሩናል? ለክርስቲያኖች በዘር መከፋፈልና ጥላቻን መዝራት ስህተት ስለመሆኑ ምን ይነግሩናል?

| ማክሰኞ | ነሐሴ 1 |
|---|---|

## የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ

ሐዋ. ሥራ 10፡44-48 በቀደምቷ ቤተክርስቲያን ታሪክ ወሳኝ የሆነን ቅፅበት ይገልፅልናል፡፡ ከሐዋሪያቱ በአንዱ አማካኝነት ወንጌል ላልተገረዙ አህዛብ ሲሰበክ ይህ የመጀመሪያው ነበር፡፡ ከግሪክ ከመጡት አማኞች በተቃራኒ ሐዋሪያቱና ሌሎች አይሁድ አማኞች አህዛብን በቤተክርስቲያን ለመቀበል ዝግጁ አልነበሩም፡፡ ኢየሱስ እስራኤላዊ መሲህ ስለነበር ወንጌሉ በቅርብና በሩቅ ላሉት አይሁድ ብቻ መሰበክ አለበት ብለው ያምኑ ነበር፡፡ አህዛብ በእምነት ማህበሩ ተቀባይነት ለማግኘት በመጀመሪያ ወደ አይሁድነት ሊለወጡ ግድ ነበር፡፡ በሌላ አባባል አህዛብ ክርስቲያን ከመሆናቸው በፊት አይሁድ መሆን ነበረባቸው፡፡ በቀደሙት አይሁዶች ዘንድ ሊለወጥ የሚገባው አስተሳሰብ ያ ነበር፡፡

ለቆርኔሌዎስና ቤተሰቡ የልሳን ስጦታ መሰጠቱ ያ አስተምሮ ስህተት መሆኑን በግልፅና በሚታይ ሁኔታ የሚያስረዳ ምልክት ነበር፤ ከመዳን አንፃር እግዚአብሔር በአድሎ የሚያያቸው የሉም፤ አይሁድና አህዛብ በአንድ አይነት መልኩ ይዳኛሉ፡፡

ሐዋ.ሥራ 11፡1-18ን ያንብቡ፡፡ በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተክርስቲያን አባላት ጴጥሮስ በቄሳርያ ላጋጠመው ነገር ምን ምላሽ ሰጡ?

ለረጅም ዘመናት በቆየውና አይሁዶች በአሕዛብ ላይ ባላቸው የተሳሳተ አመለካከት ምክንያት በኢየሩሳሌም የነበሩት አማኞች ጴጥሮስ ካልተገረዙት ጋር በመብላቱ ወቀሱት፡፡ ከቆርኔሌዎስና ቤተሰቦቹ መዳን በላይ የአይሁድ ስርአቶች ተጠብቆ መቆየት የበለጠ ያሳሰባቸው ይመስላል፡፡ ቤተክርስቲያን ከአይሁድ ስርአቶች ጋር ከተቃረነች የእስራኤልን እምነት በመካዳቸው ምክንያት እግዚአብሔር የሚተዋቸው መስሏቸው ፈሩ፡፡ ሌሎች አይሁዶች በነርሱ ላይ በሚያቀርቡባቸው ክስና እስጢፋኖስ እንዲገደል ወደመሩት ወቀሳዎች መንገድ እንዳይሄዱ ፈሩ፡፡

"የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሙሉ ለሙሉ አዲስ ወደሆነ የስራ አቅጣጫ የምትገባበት ጊዜ መጣ፡፡ ብዙ ከአይሁድ የተመለሱ አማኞች በአህዛብ ላይ ዘግተውት የነበሩት በር በሰፊው የሚከፈትበት ጊዜ ደረሰ፡፡ ወንጌሉን የተቀበሉ አህዛብ መገረዝ ሳይኖርባቸው አይሁድ ከሆኑ ደቀመዛሙርት ጋር እኩል መታየት ቻሉ፡፡" Ellen white, The Acts of the Apostles, P.136

ልክ በጴንጤቆስጤ ቀን እንደሆነው ቀድሞ በማያውቁት ቋንቋ ተናገሩ፡፡ የአላማ ልዩነት ብቻ ነበር፡- ለሐዋሪያቱ ልሳን ሲሰጥ ለዓለም ወንጌሉን ለማዳረስ አላማ ሲሆን ለቆርኔሊዮስ ግን የእግዚአብሔር ፀጋ በአህዛብም እየሠራ እንደነበር ለማረጋገጥ ነበር የተሰጠው፡፡

**ረቡዕ ነሐሴ 2**

## የአንፆኪያዋ ቤተክርስቲያን

በቆርኔሌዎስ መለወጥ በመነሳሳት ሉቃስ የጴጥሮስን አገልግሎት ትረካ አቋርጦ ወንጌል በአህዛብ ወደፊት የሄደበትን ታሪክ ይነግረናል፡፡

ሐዋ. *ሥራ* 11፡19-26ን ያንብቡ፡፡ አንዳንድ ከኢየሩሳሌም የመጡ ስደተኞች ወደ አንፆኪያ ሲመጡ ምን ተፈጠረ?

---

---

የሐዋ. *ሥራ* 11 ይሄኛው ክፍል ጳውሎስ ያነሳሳውን (በምዕራፍ 8 የሚገኘውን) ስደት ታሪክ የሚያወሳ ነው፡፡ ስለዚህ ቀደም ብለን ያየናቸው መስፋፋቶች በይሁዳና በሌሎች ቦታዎች እየተካሄዱ ባሉበት ሰዓት ከኢየሩሳሌም እንዲወጡ ከተገደዱት ግሪካዊያን አማኞች መካከል አንዳንዶቹ ከይሁዳ ድንበር እጅግ ርቀው ወንጌልን እያዳረሱ ነበር፡፡

ሉቃስ በሶሪያ በምትገኘው አንፆኪያ በተባለችውና ስደተኛ የሆኑት አማኞች ለአይሁድ ጓደኞቻቸውና ለግሪካዊያን ወንጌልን መስበክና ብዙ አማኞችን ማግኘት በጀመሩባት ከተማ ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ በሐዋ. ሥራ 1፡8 ኢየሱስ የሰጠው ተልዕኮ ግሪክ በነበሩ አይሁድ ክርስቲያኖች ጥረት አማካኝነት መስተዋል ጀመረ፡፡

በአንፆኪያ በተገኘው ስኬት የተነሳ በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋሪያት ሁኔታውን እንዲገመግም በርናባስን ለመላክ ወሰኑ፡፡ እርሱም ለወንጌል ሥራ መስፋፋት ያለውን ታላቅ ዕድል በመመልከት እንዲረዳው ጳውሎስን ይዞ ወደ ተርሴስ ሄደ፡፡

በርናባስ ትክክል ነበር፡፡ እርሱና ጳውሎስ አብረው በሰሩበት ዓመት አብዛኛው አህዛብ የሆነበት ብዙ ሕዝብ ወንጌሉን መስማት ቻለ፡፡ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ይናገሩበት የነበረው ግለት አማኞቹ ለመጀመርያ ጊዜ «ክርስቲያኖች» ተብለው እንዲጠሩ አደረጋቸው (ሐዋ. ሥራ 11፡26)፡፡ ክርስቲያኖች «ተብለው ተጠሩ» የሚለው አባባል ከቤተክርስቲያን ውጭ ባሉ ሰዎች ምናልባትም ሊያሾፉባቸው የተሰጠ ስም መሆኑን ያሳያል፡፡ አማኞች ግን ራሳቸውን «ወንድሞች» (ሐዋ. ሥራ 1፡16)፣ ደቀመዛሙርት (ሐዋ.ሥራ 6፡1) ወይም «ቅዱሳን» (ሐዋ. ሥራ 9፡13) ብለው ይጠሩ ነበር፡፡ የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ በተፃፈበት ወቅት «ክርስትያን» የሚለው የተለመደ መጠሪያ ሆኖ ነበር (ሐዋ. ሥራ 26፡28) ሉቃስም ያንን እያረጋገጠ ይመስላል፡፡ «ክርስቲያን» ማለት የክርስቶስ ተከታይ ማለት ነው፡፡

ለእርስዎ «ክርስቲያን» ተብሎ መጠራት ምን አይነት ትርጉም ይሰጥዎታል? ታዲያ ህይወትዎ እውነትም ክርስቲያን ነው? ማለትም በጣም ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ክርስቲያን ካልሆኑት በተለየ እንዴት እየኖሩ ይሆን?

## ሐሙስ ነሐሴ 3

### የሔሮድስ ማሳደድ

ወደ ይሁዳ ስንመለስ ንጉስ ሔሮድስ የዮሐንስ ወንድም የሆነውንና የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብን ማስገደሉን እንመለከታለን (ማር. 1፡19)፡፡ በጴጥሮስም ላይ ተመሳሳዩን ማድረግ ፈልጎ ነበር፡፡

ሐዋ.12፡1-4ን ያንብቡ፡፡ ቀደምቷ ቤተክርስቲያን ስላጋጠማት ተጋድሎ ይህ ምን ያስተምራል?

---

---

በዚህ ቦታ የተጠቀሰው ሔሮድስ አግሪጳ የመጀመሪያው ሲሆን የታላቁ ሔሮድስ የልጅ ልጅ ነው (ማቴ. 2፡1)፡፡ በይሁዳ ከ40 እስከ 44 ዓ.ም እ.ኤ.አ ገዛ፡

፡ ለእምነቱ ያለው ፅናት በአይሁዳዊያን በተለይም በፈሪሳዊያን ዘንድ ታዋቂነትን አስገኝቶለታል፡፡ በአይሁዶች ለመወደድ ብሎ አንዳንድ ሐዋሪያትን ማሰቃየቱን ስንመለከት በሌላ ቦታ ስለርሱ ከተፃፈው ጋር ይገጥማል፡፡

ያዕቆብ በርሱ ትዕዛዝና አላማ መሠረት ስለተገደለ ጴጥሮስንም ሊያስገድል አቀደ። ጴጥሮስ ተያዘና በአራት ፈረቃ አራት አራት ወታደሮች እንዲጠብቁት አደረገ፡፡ ጴጥሮስ ከአራት ወታደሮች ጋር ይቆይ ነበር፤ሁለቱ ከእጁ ሠንሰለት ጋር ሲታሰሩ የቀሩት ሁለት ደግሞ በሩን ይጠብቃሉ፡፡ እንዲህ ጥብቅ የሆነ ጥበቃ የሚያስደርገው ቀደም ብሎ ጴጥሮስና ዮሐንስ ታስረው ሳሉ የተፈጠረው ነገር እንዳይደገም ለማድረግ ነበር (ሐዋ. ሥራ 5፡17-20)፡፡

ሐዋ. ሥራ 12፡5-18ን ያንብቡ፡፡ ወንድሞች ሲፀልዩ ምን መልስን አገኙ?

---

---

በማግስቱ አግሪጳ ጴጥሮስን ወደ ፍርድ አስወስዶ ለማስገደል አቅዶ በዚያ ለሊት ጴጥሮስ በድጋሚ ተአምራዊ በሆነ ሁኔታ በመልአክ አማካኝነት ከእስር ወጣ፡፡

በመቀጠል በቄሳሪያ የአግሪጳን መሞት ታሪክ እናገኛለን/ሐዋ. ሥራ 12፡20-23/፡፡ የሞተበትን ምክንያት ለመለየት የተለያዩ መላምቶች ቢሰጡም /ጨጓራ፣ መርዝ፣ የሆድ ህመም/ ሉቃስ ግን በግልፅ ንጉሱ የሞተው በመለኮታዊ ፍርድ ምክንያት እንደሆነ ተናግሯል፡፡

ያዕቆብ ተገደለ፣ ጴጥሮስ እንዲያመልጥ ተደረገና ሔሮድስ ደግሞ መለኮታዊ ቅጣት አገኘው፡፡ በአንዳንዶቹ ጉዳዮች ፍትህን ብናይም በሌሎቹ ደግሞ እንደዚያ አይመስልም፡፡ ላሉን ጥያቄዎች ሁሉ መልስ እንደሌለንና ባልተረዳናቸው ጉዳዮችም ቢሆን ለምን በእምነት መኖር እንዳለብን እነዚህ ጉዳዮች የሚያስተምሩን እንዴት ነው?

## ዓርብ | ነሐሴ 4

**ተጨማሪ ጥናት**፡- “በሐዋሪያት ሥራ 10 ላይ በሰማይ መላዕክት ተሳትፎ ቆርኔሌዎስና ቤተሰቡ የሚለወጡበትን ምሳሌ እናገኛለን፡፡ እነዚህ ምዕራፎች /8-10/ በትኩረት ይነበቡ፡፡ በነዚህ ውስጥ ነፍሳትን በማዳን ሥራ ከተጠመደ ክርስትያን ጋር ብዙዎች ከሚገምቱት በላይ ሰማይ በቅርበት እንደሚሠራ እንመለከታለን፡፡ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰብአዊ ዘር ግድ እንደሚለውና እያንዳንዳችንም ሌላውን የጌታን ሥራ በምድር ላይ ለመጨረስ እንደሚጠቅም የእግዚአብሐር መሣሪያ አድርገን መመልከትን መማር ይኖርብናል፡፡” *Ellen G White, The SDA Bible commentary, VOl.6, P. 1059*

“ቤተክርስቲያን ስትፀልይ የእግዚአብሔር አላማ ወደፊት ይራመድና ምንም እንኳን ስደትና ሞት ባይቀርም ሰይጣን ግን እየተሸነፈ ይሄዳል፡፡ ሉቃስ ስለ ወንጌል አሸናፊነት በእርግጠኝነት ሲናገር አገልጋዮቹ ቢሰቃዩና ቢታሰሩም የእግዚአብሔር ቃል ግን እንደማይታሰር ይገልፃል፡፡” I Howard Marshall, The Acts of the apostles (Grand Rapids: Eerdmans,1980), PP. 206-207

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ቆርኔሌዎስ “ከመላው ቤተሰቡ ጋር በመንፈሳዊ ነገር የተጋና እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ ለሰዎች እጅግ ምፅዋት የሚሰጥ፣ አዘውትሮ ወደ እግዚአብሔር የሚፀልይ ነበር፡፡” /ሐዋ. ሥራ 10፡2/ ቆርኔሌዎስ ጴጥሮስንም ከመገናኘቱ በፊት የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጡ ይሠራ እንደነበር ይህ ማስረጃ ነው፡፡ ያለው የአምልኮ ህይወት እግዚአብሔር ወንጌሉን እንዲያበራለት በር ከፍቶ ይሆን? በርሱ ታሪክ ውስጥ ትምህርት የሚሆነን ምን አለ?

2. ወደ ሰኞው ክፍል ይመለሱና ይህንን ጥያቄ በሰንበት ት/ት ክፍልዎ ይጠይቁ፡፡ እንደ ክርስቲያን መግባት በሌለብን የዘር ግጭት ውስጥ የሚያስገቡን ምን አይነት ባህላዊ፣ ማህበራዊና ፓለቲካዊ አውዶች ይሆኑ? በሌላ አባባል እንደ ክርስቲያን ከባህልና አመለካከት በላይ መሆን የምንችለው እንዴት ነው?

3. ምንም ጉዳት ቢደርስባቸውም ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ማሳደዱ መልካም ነገርን አምጥቷል፡፡ ወደ አንፆኪያ የመጡት ስደተኞች ለአይሁዶችና ለግሪካውያን መስበክ ጀመሩ፡፡ በክፍልዎ በግል ስላጋጠምዎና ቆይቶ ወደ በረከት ስለተቀየረ ህመምና ስቃይዎ ያካፍሉ፡፡

4. ያዕቆብ ለኢየሱስ ቅርብ ከነበሩት ደቀመዛሙርት አንዱ ነበር /ማር. 5፡37፣9፡2፣14፡33/፡፡ ሆኖም ከአስራ ሁለቱ የመጀመሪያው ሰማዕት ሆነ፡፡ ታማኝ የሆኑ ሰዎች የማይገባቸውን መከራ ሲቀበሉ የሚያሳዩ ሌሎች ምሳሌዎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጥቀሱ፡፡ ስለ ስቃይ ባለን ጥያቄ ላይ ከነዚህ ታሪኮች ምን ትምህርት መውሰድ እንችላለን?

# 7ኛ ትምህርት ከነሐሴ 5 - 11

## የጳውሎስ የመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ጉዞ

### ሰንበት ከሰዓት

*ለዚህ ሳምንት ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡- ሐዋ.13፣2ቆሮ.4፡7-10፣ሮሜ.10፡1-4፣ ሮሜ 3፡19፣ ሐዋ.ሥራ 14፡1-26፣ ሮሜ. ምዕ.9-11፡፡*

**መታሰቢያ ጥቅስ** ፡-"እንግዲህ ወንድሞች ሆይ የኃጢአት ይቅርታ የሚገኘው በኢየሱስ በኩል መሆኑ እንደ ተሰበከላችሁ ዕወቁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ በሙሴ ሕግ በኩል ማግኘት ያልቻለውን ጽድቅ ያገኛል፡፡" (ሐዋ. ሥራ 13፡38-39)"

የለ ጥርጥር ወንጌል ለአህዛብ ብሎም ለአይሁድ መዳረስ ነበረበት፡፡ ቀደምት አይሁዳውያን ክርስትያኖች ቀስ በቀስናበእርግጠኝነት መቀበል የጀመሩትይህንን መልእክት ነበር፡፡

አህዛብ በስፋት መቀላቀላቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ በግልፅ የሚነግረን ስለ አንጾኪያ የተነገረው ታሪክ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ጥቂት የማይባሉ የአይሁድ አማኞች የነበሩ ቢሆንም(ገላ. 2፡11-13) የመጀመሪያው የአህዛብ ቤተክርስቲያን የተመሰረተው በአንጾኪያ ነበር፡፡ መስራቾቹ ለወንጌል ካላቸው ቅናት የተነሳ በርናባስና ጳውሎስ እንደመጡ በተፈጠረው አዲስ ሃይል በመነሳሳት ቤተክርስትያን በፍጥነት አደገች፡፡ ይህችስፍራም ከይሁዳ ውጪ የመጀመሪያዋየክርስትያኖች ማዕከል ሆነች፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነማ በአንዳንድ ጉዳዮች በኢየሩሳሌም ከሚገኘው ቤተክርስትያንም ሳይቀርትልቃለች፡፡

ሐዋሪያት አሁንም ያሉት በእየሩሳሌም ቢሆንም አንጾኪያ የክርስትያን አገልግሎት ተልዕኮ የውልደት ስፍራ ሆነች፡፡ ጳውሎስ የተጓዘባቸውን ሦስት ሚሲዮናዊ ጉዞዎች በተቃና መንገድ እንዲያደርግ በመነሻነት እገዛ ያደረጉለት በዚህ ስፍራ ያሉ አማኞች ነበሩ፡፡ ክርስትና የሱስ እንዳቀደው አለማቀፋዊ ሃይማኖት የሆነው፣ ወንጌልም «ለህዝብ፤ ለነገድ ለቋንቋ ሁሉ»(ራዕይ 14፡6) እንዲስፋፋ የሆነውበነዚህ ሰዎች ቆራጥነት ምክንያት ነበር፡፡

የዚህን ሳምንት ትምህርት አጥንተው ለነሐሴ 12 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡

## እሑድ ነሐሴ 6

### ስልማና እና ጻፉ

ሐዋ. ሥራ 13 ላይ ሉቃስ በሁለት ሙሉ ምዕራፎች(ሐዋ. 13 እና 14) የሰፈረውን የጳውሎስን የመጀመሪያ ጉዞ ለመተረክ ሲል ትኩረቱን ወደ አንፆኪያ ይመልሳል፡፡ ከዚህ ጀምሮእስከ መጽሐፉማብቅያድረስትኩረቱን በጳውሎስ እና ለአህዛብ ባለው ተልዕኮ ላይ ያነጣጥራል፡፡

ይህ በሐዋሪያት ስራ መጽሐፍ የምናገኘው ቀዳሚው የወንጌል እንቅስቃሴ ሲሆን ይህ ጉዞ ደግሞ በቤተክርስትያኒቷ በጥንቃቄ ታቅዶ የተከናወነ ድርጊት ነበር፡፡ ቢሆንም ሉቃስ ይህ ጥረት የመነጨው ከአማኞች ከራሳቸው ሳይሆን ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ በአጽንኦት ይጠቅሳል፡፡ እዚህ ጋ የምናገኘው ወሳኙ ነጥብ እግዚአብሔር ሊሰራ የሚችለው እርሱ እንዲጠቀምብን በገዛ ራሳችን ፈቃድ ራሳችንን መስጠት ስንችል ነው፡፡

ሐዋ.13፡1-12ን ያንብቡ፡፡ በርናባስና ጳውሎስ በቆጵሮስ ስላደረጉት እንቅስቃሴ በተመለከተ ሉቃስ አጽንኦት ሰጥቶ ሊያስተላለፍ የፈለጋቸው ነጥቦችምንድናቸው?

____________________________________________________

____________________________________________________

ወንጌላውያኑ ተሰናብተው ከመሄዳቸው አስቀድሞ የምልጃ ጸሎትና ጾም ተደርጎ ነበር፡፡ በዚህ አውድ መሠረት እጅን ጭኖ የመጸለይ ተግባር ለስራው ብቁ ይሆኑ ዘንድ ለእግዚአብሄር ፀጋ አሳልፎ መስጠትንና መቀደስን ይወክላል(ሐዋ.14፡26)፡፡

የቆጵሮስ ደሴት ከአንጾኪያ እምብዛም ርቆ በማይገኘው ሰሜን ምስራቃዊ የሜዴትራንያን ባህር ጥግ የሚገኝ ስፍራ ነው፡፡ በርናባስ አስቀድሞ በቆጵሮስ ስለነበረብቻ ሳይሆን ወንጌልም በዚያ ደሴት ቀድሞ ደርሶ ስለነበር ጉዞውን ለመጀመር ምቹ ስፍራ ነበር፡፡ ነገር ግን በዚያ ቦታም ቢሆን እጅግ ብዙ መሰራት የሚገባው ሥራ ነበረ፡፡

በቆጵሮስ ውስጥ በርናባስ እና ጳውሎስ እንዲሁም የበርናባስ የአክስት ልጅ የሆነው ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ (ሐዋ.15፡39፤ቆላ.4፡10) በስልማና ምኩራቦች ይሰብኩ ነበር፡፡ ይህ የጳውሎስ የየእለት ተግባሩ ነበር፡፡ ወደ አህዛብ ፊቱን ከማዞሩ በፊት ቀድሞ በምኩራብ መስበክ ማለት ነው፡፡ የሱስ እስራኤላዊ የሆነ መሲህ ስለነበር ወንጌልን አስቀድሞ ለአይሁድ ማካፈል ትክክለኛና እጅግ አስፈላጊ ነበር፡፡

ከስልማና በኋላ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ እየተጓዙ (በሃሳባችን መሳል እንችላለን) ጳፋ ወደተባለችው ዋነኛ ከተማ እስኪደርሱ ድረስ በመንገድ ይሰብኩ ነበር፡፡ ከዚያም የመጽሐፉ ትረካ በሁለት ሰዎች ዙሪያ ያጠነጥናል፡፡እነሱም አይሁዳዊ ጠንቋይ የሆነው በርያሱስ ወይም ኤልማስ እና የሮም አገር ገዥ የነበረው ሰርግዮስ ጳውሎስ ናቸው፡ ፡ ታሪኩ ሲቀጥል በእንደዚህ ያለ ከባድ ምላሽ በሚሰጥበት ሁኔታ እንኳን ወንጌል እንዴት እንደተሰበከ ያትታል፡፡ በአንድ በኩል ግልጽ ተቃውሞ በሌላ በኩል ደግሞ ትልቅ ስፍራ ያላቸው የአህዛብ ሰዎች ወንጌልን አምነው ሲቀበሉ እናያለን፡፡ ሐዋ.13፡12 ላይ የምናገኘው ግልጽ ትረካ ስለ መለወጥ(ወንጌልን ስለ መቀበል) በደንብ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይነው፡፡

በዚህ ታሪክ አይሁድ የሆነው እውነትን ሲቃወም አህዛብ የሆነው ግን መቀበሉን ያሰላስሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ በሌላ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ክርስትያኖች ምንም እምነት ከሌላቸው ሰዎች ይልቅ «የወቅቱን እውነት» ለመቀበል ሲቸገሩ ስናይ ይህ ምን እንድንረዳ ያደርገናል?

| ሰኞ | ነሐሴ 7 |
|---|---|

## የጲስዲያዋ አንፆኪያ ክፍል 1

ጳውሎስና ጓደኞቹ ከቆጵሮስ ተነስተው በዛሬዋ ቱርክ ደቡብ ጫፍ በጵንፍሊያ ወደምትገኘው ጴርጌን ተጓዙ፡፡ ወደ ጲስዲያ ከመሄዳቸው አስቀድሞ ሉቃስ ሁለት የተከናወኑ ለውጦችን ይዘግብልናል፡፡ ጳውሎስ የመሪነቱን ሚና መያዙን (እስካሁን ድረስ በርናባስ ነበር ቀድሞ ይጠቀስ የነበረው) ሉቃስ የጳውሎስን አይሁዳዊ ስም («ሳውል») መጠቀም ያቆምና «ጳውሎስ» በሚለው ስም ብቻ መጠቀም ይጀምራል (ሐዋ.13፡9)፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ምናልባትም ጳውሎስን ከዚህ በኋላ በብዛት የምናገኘው በግሪክና ሮም ግዛት ውስጥ ስለሆነ ይሆናል፡፡

ሐዋ.13፡13 ላይ እንደተዘገበው ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ ወደ እየሩሳሌም ተመለሰ፡፡ ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ በምን ምክንያት ተለይቷቸው እንደሄደ የተገለፀልን ነገር የለም፡፡ ኤለን.ጂ.ኋይት ስትገልጽ ግን ከፊትለፊታቸው ሊገጥማቸው ያለው መከራን በመፍራትና ተስፋን በመቁረጥ «ማርቆስ ስለፈራናድፍረቱን ስላጣ አብሯቸው ወደ ሩቅ ስፍራ እንዳይሄድ እንቢ በማለት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ» ትለናለች፡፡ - The Acts of Apostles, P.170፡፡እግዚአብሔር ነገሮች ቀላል እንደሚሆኑ ቃል አልገባም፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ግን ጳውሎስ ከመጀመሪያውኑ የሱስን ሲያገለግል ስቃይና እንግልት እንደሚደርስበት አውቋል (ሐዋ.9፡16)፡፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር ሃይል ላይ ሙሉ በሙሉ መደገፍን ተማረ፤ ይህም የጥንካሬው ሚስጥር ሆነለት (2ቆሮ.4፡7-10)፡፡

ሐዋ.13፡38ን ያንብቡ፡፡ በጲስዲያ ምኩራብ ጳውሎስ ያስተላለፈው ወሳኝ መልእክት ምን ነበር?

---

---

ሐዋ.13፡16-41 በአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ የተቀመጠውን የጳውሎስን የመጀመርያ ስብከት ይገልጽልናል፡፡የተፃፈው ይህ ሆነ እንጂ የጳውሎስ የመጀመሪያው ስብከቱ እንዳልሆነ ሳንረሳ በአጭሩ ተጠቃሎ የቀረበ መሆኑም ሌላው ነጥብ ነው፡፡

ስብከቱ በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡፡ እግዚአብሄር እስራኤልንና የዳዊትን መንግስት ስለመምረጡ(ሐዋ.ሥራ 3፡17-23)፡፡ ይህ ክፍል ከአይሁድ አድማጮች ጋር መግባባትን ለመፍጠር የተናገረው ነው፡፡ ቀጥሎም ኢየሱስ የእግዚአብሄር የተስፋ ቃልፍጻሜበመሆንከዳዊት ዘር ግንድ ለእስራኤል ድነትን እንደሚያመጣ ተረከላቸው (ሐዋ. ሥራ 13፡24-37)፡፡ነገሩን ሲደመድም ደግሞ በየሱስ የተሰጠውን ድነት እምቢ ለሚሉ ማስጠንቀቂያን በመስጠት ነበር (ሐዋ. ሥራ 13፡38-41)፡፡

የስብከቱ ዋነኛ ጡዘት የሚገኘው በቁርጥ 38ና 39 ሲሆን ይህም የጳውሎስ መልእክት አንኳር ነጥብ ወደ ሆነው ፅድቅ ያተኩራል፡፡ ይቅርታና ጽድቅ የሚገኘው በሙሴ ህግ በኩል ሳይሆን በየሱስ ብቻ ነው፡፡ ይህ ክፍል ህጉ ተሽሯል አይለንም ነገር ግን አይሁዶች ጽድቅ ያመጣልናል ያሉት ህጉ ይህን ማድረግ እንደማይችል ፍንጭ ለመስጠት ነው (ሮሜ10፡1-4)፡፡ የዚህ ሁሉ ብቸኛ ባለመብት ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው (ገላ.2፡16)፡፡

ድነት በየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው? የእግዚአብሔርን የሞራል ህግ መጠበቅ አስፈጊነትና ህጉ ሊያፀድቀን ስላለመቻሉ በማሰብ ሁለቱን ሀሳቦች እንዴት ሊያስታርቋቸው ይችላሉ?

## ማክሰኞ ነሐሴ 8

### የጲስዲያዋ አንፆኪያ ክፍል 2

ሐዋ.13:38-39 የሚገልጽልን ህጉ ሊያፀድቀን እንደማይችል ሲሆን ይህ ደግሞ ወሳኝ አስተምህሮ ነው፡፡ የህጉ ባህሪ መልካም ቢሆንም ህጉ ሊያፀድቀን አይችልም፤ ምክንያቱም ለሚጠብቁት ሰዎች ፍጹም መታዘዝን አይሰጣቸውም (ሐዋ.15፡10፣ ሮሜ 8፡3)፡፡ ህጉ ፍጹም መታዘዝን እንድንለማመድ ቢያደርገን እንኳን ያለፈውን ኃጢያታችንን ሊያስተሰርይልን አይችልም(ሮሜ3፡19፣ ገላ.3፡10-11)፡፡ ለዚህ ነው ጽድቅን በከፊልም እንኳን ማግኘትየማይቻለው፡፡ ፅድቅን ልንቀበል የምንችለው

ሊያስተሰርይ ብቁ በሆነው በየሱስ ላይ ባለን እምነት ብቻ ነው፡፡ (ሮሜ 3፡28፤ ገላ.2፡ 16)፡፡ ይህ ስጦታ ደግሞ ፈጽሞ የማይገባን ነው፡፡ መታዘዝ ለክርስትና ህይወት ምንም ያህል አስፈላጊ ቢሆን ድነትን ግን ሊያመጣልን አይችልም፡፡

ሐዋ.13፡42-49ን ያንብቡ፡፡ በምኩራብ ያሉ ሰዎች የጳውሎስን መልእክት እንዴት ተቀበሉት?

ምንም እንኳን ጳውሎስ መልእክቱን የደመደመው ጠንከር ባለ መንገድ ቢሆንም በምኩራብ የነበሩት አብዛኛዎቹ ሰዎች የሰጡት ምላሽ ደስ የሚያሰኝ ነበር፡፡ በሚቀጥለው ሰንበት ግን ነገሮች በአስደናቂ ሁኔታ ተለወጡ፡፡ የወንጌሉን መልዕክት ሲቃወሙ የነበሩት «አይሁዳውያን»ምናልባትም ይሁዲነትን እንደተቋም የሚወክሉት የምኩራብ መሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡  ሉቃስም እጅግ ከመቅናታቸው የተነሳ በጭካኔአይን ጳውሎስን ይመለከቱት እንደነበር ገልጧል፡፡

በጥንቱ አለም የአይሁድ እምነት መገለጫ የነበሩት በአንድ አምላክ ማመን፣ የአኗኗር ዘይቤ እንዲሁም ሰንበት ከአይሁድ ውጪ የሆኑትን ሰዎች በከፍተኛ ሁኔታ ስለሳባቸው ብዙዎች የአይሁድን እምነት ተቀላቅለው ነበር፡፡ ግርዘት ግን ኋላቀር እና አፀያፊ አድርገው ስለወሰዱት ትልቅ እንቅፋት ሆኖባቸው ነበር፡፡ በዚህ የተነሳ ብዙ አህዛብወደ አይሁዳዊነት በይፋ ሳይቀየሩም እግዚአብሔርን ለማምለክ ወደ ምኩራብ ይመጡ ነበር፡፡ እነዚህም «እግዚአብሔርን የሚፈሩ» ተብለው ይጠሩ ነበር፡ ፡ በምኩራብ የሚገኙ የአይሁድ እምነት ተከታዮች ተብሎም ተጠርተዋል (ሐዋ.13፡ 16፤43)፡፡በህዝቡ መካከል የጳውሎስ መልእክት እንዲሰራጭያደረጉትናበብዛትም ይመጡ የነበሩት «እግዚአብሔርን የሚፈሩ» የተባሉትና ወደ አይሁድነት በይፋ የተቀላቀሉት  እንደሆኑ ይገመታል፡፡ በቅድሚያ የአይሁድ እምነት ተከታይ ሳይኮን ድነትን መለማመድ መቻሉ ያለጥርጥር ለብዙዎች ማራኪና ሳቢ ነበር፡፡

የአይሁድ መሪዎች ስላደረባቸው ቅናት ምክንያት ለመግለፅ ይህ ይረዳ ይሆናል፡፡ በዚህም አለ በዛ ወንጌልን በመቃወማቸው ከእግዚአብሔር ድነት ራሳቸውን እያገለሉ ብቻ ሳያሆን ጳውሎስና በርናባስንም ነፃ ሆነው በድነት እቅድ ውስጥ ያካተታቸውን አምላክ በማመስገን ወደተደሰቱት አህዛብ ሙሉ ትኩረታቸውን እንዲያደርጉ አደረጓቸው፡፡

ረቡዕ ነሐሴ 9

## ኢቆንዮን

በአይሁድ መሪዎች አነሳሽነት የአካባቢው ባለስልጣናት የተቃውሞ ቅስቀሳን አነሳስተው ጳውሎስንና በርናባስን ከከተማ አስወጧቸው(ሐዋ.13፡50)፡፡ ደቀመዛሙርቱ ግን በደስታና በመንፈስቅዱስ ይበልጥ ተሞሉ (ሐዋ.13፡52)፡፡ወንጌላውያኑም ወደ ኢቆንዮን ከተማ አቀኑ፡፡

ሐዋ. ሥራ 14፡1-7ን ያንብቡ፡፡የጳውሎስና የበርናባስ እንቅስቃሴ በኢቆንዮን ምን ውጤት አመጣ?

___

___

በኢቆንዮንም ጳውሎስና በርናባስ ፊታቸውን ወደ አህዛብ ከማዞራቸው አስቀድሞ አይሁዶችን ለመድረስ ሞከሩ፡፡ በጲስድያዋ አንፆኪያ የነበረው የጳውሎስ ስብከት (ሐዋ.13፡16-41) በአገልግሎቱ ለአይሁድ ቅድሚያ የሰጠበትን ዋነኛ ምክንያት ያም ስለ እስራኤል መመረጥ መመረጡም ስለያዛቸው በረከቶች (ሮሜ3፡2፣ 9፡4-5) እንዲሁም ከዳዊት የዘር ግንድ አዳኝ የመምጣቱ ተስፋ ቃል ስለተፈፀመ ነበር፡፡ አያሌ አይሁዳውያን ወንጌልን መቃወማቸው እውነት ቢሆንም ጳውሎስ ግን ስለአይሁድ መለወጥ ፈጽሞ ተስፋ አልቆረጠም፡፡

ሮሜ 9-11 ላይ ጳውሎስ ግልጽ አድርጎ እንደሚያስቀምጥልን «ከእስራኤል የተወለደ ሁሉ እስራኤላዊ አይደለም» (ሮሜ9፡6)፤አንዳንድ አይሁዳውያንም ሊያምኑ የቻሉትበእግዚአብሔር ምህረት የተነሳ ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር ህዝቡን አልተወምነገር ግን «በአሁን ጊዜም እንደዚሁ በጸጋ የተመረጡ ትሩፋን አሉ»(ሮሜ 11፡5)፡፡አንድ ቀን አይሁዶች በእምነት ወደ የሱስ እንደሚመጡ ቢያምንም ጳውሎስ ወንጌልን ለአህዛብ መስበኩን ቀጠለ፡፡

«ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 9-11 ላይ ባቀረበው የመከራከሪያ ነጥብ በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ስለተከተለው የተልዕኮስትራቴጂ የበለጠ የገለጸ ሲሆን በየትውልዱ ያሉ ክርስትያኖች ላላመኑ አይሁዶች መመስከር እንዳለባቸውያሳየበትን ወሳኝ የስነ መለኮት ትምህርት የምናገኝበት ነው፡፡» David G. Peterson, The Acts of the Apostles (Grand Rapids: Eerdmans, 2009),P.401::

ጉዳዩ በጲስዲያዋ አንፆኪያ ከሆነው እምብዛም አይለይም፡፡ በቅድሚያ ለጳውሎስ መልእክት አይሁድም ይሁኑ አህዛብ የሰጡት ምላሽ ቀና ነበር፡፡ ግን አሁንም በድጋሚ አማኝ ያልሆኑ አይሁዳውያን ምናልባትም የአይሁድ ማህበረሰብ መሪዎች አህዛብ የሆኑትበወንጌላውያኑ (በእነ ጳውሎስ) ላይ ተቃውሞ እንዲያነሳሱባቸው አዕምሮአቸውን መረዙባቸው፡፡ ይህም በህዝቡ መካከል ከባድ መከፋፈልን ፈጠረ፡ ፡ ተቃዋሚዎቹም ጳውሎስ እና በርናባስን ለማጥቃትና ለመግደል ሲያሴሩ ሁለቱም ወንጌላውያን ከተማውን ለቀው ወደ ቀጣዩ ስፍራ ለመሄድ ወሰኑ፡፡

አይሁዶች ወንጌልን ከመስማት ባለፈ የየሱስን ስም የሚጠሩ ሰዎች በህይወታቸው ሲያሳዩት መመልከት ይፈልጋሉ፡፡ እርስዎ አይሁዳዊ የሆነ ጓደኛ ካለዎት ምን አይነት ምስክርነትን ነው እየሰጡት ያሉት?

## ሐሙስ ነሐሴ 10

### ልስጥራና ደርቤ

ቀጥሎ ጳውሎስና በርናባስ የጎበኙት ስፍራ ልስጥራ ሲሆን ከኢቆንዮን በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ አስራ ስምንት ማይል (29 ኪ.ሜ አካባቢ) ርቆ የሚገኝ አነስተኛ መንደር ነው፡፡ በዚያ ጥቂት ጊዜ ቢያሳልፉም (ሐዋ. ሥራ 14፡6-7፣15) ሉቃስ የዘገበልን ግን አንዱን ታሪክ ብቻ ነው፤ይኸውም ከመወለዱ ጀምሮ ሲሰቃይ ስለኖረው ምናልባትም ለማኝ ስለነበረው ሽባው ሰው መፈወስነበር፡፡

ሐዋ.14፡5-19ን ያንብቡ፡፡ ለጳውሎስ የመለሱለት ምላሽ ሕዝቦቹ ምን ያህል ማስተዋላቸውየወረደእንደሆነ እንዴት ያሳያል?

---

---

ሕዝቦች በተአምሩ እጅጉን ስለተደመሙ ጳውሎስና በርናባስ አማልክት እንደሆኑ በማመን ስም አወጡላቸው፡፡ በርናባስን «ድያ(ዜውስ)» ብለው ሲጠሩት እርሱም የግሪክ አማልክት የበላይ አምላክ ሲሆን ጳውሎስን ደግሞ «ሄርሜን» ብለው ጠሩት እርሱም «የድያ» አፈቀላጤ ነው፡፡እንደእውነቱ ከሆነሰዎቹ መስዋዕትም ጭምር ሊያቀርቡላቸው ፈልገው ነበር፡፡

የላቲን ገጣሚ የሆነው ኦቪድ (43 ከክ.ል. በፊት -17 ከክ. ል በኋላ የኖረው) ሁለት አማልክት በሰዎች ተመስለው ተመሳሳዩን አካባቢ ("የጵርግያን ከፍታዎችን") ሲጎበኙና ለማረፍ የሚበጃቸውን ስፍራ ሲፈልጉ የሚተርክን አፈ ታሪክ ቀደም ብሎፅፎ ነበር፡፡ እንደ አፈ-ታሪኩ ከሆነ ትሁትና በእድሜ የገፉ ጥንዶች እነዚህን እንግዶች ተቀብለው

ተንከባከቧቸው፤ ሌሎቹ ግን ቸልተኞች ነበሩ፡፡ለእነዚህ የማይታወቁ እንግዶች መልካምነትንና ርህራሄን ስላሳዩዋቸው የእነዚህ ጥንዶች ቤት ወደ ቤተ መቅደስነት ሲለወጥ እነርሱም ካህናት ሆኑ፡፡ የቀረው ከተማ ግን ሙሉ በሙሉ ጠፋ (Meth-amorphoses 611-724)::

በዚህ አካባቢ ይህ ታሪክ በመዳረሱ ለጳውሎስ ተአምር ህዝቡ የሰጠው ምላሽ እምብዛም ላያስደንቅ ይችላል፡፡ ታሪኩ ህዝቡ እነዚህ የፈውስ አማልክት ብለው የሚጠሩትን አስክሌፒየስ ናቸው ከማለት ይልቅወንጌላውያኑ ሁለቱ አማልክት ናቸው ስላሉበት ምክንያት ይህ ታሪክ በደንብ ይገልፅልናል፡፡ ጳውሎስና በርናባስ ግን የሐሰት አምልኮዋቸውንእንዲያቆሙ ከለከሏቸው፡፡ በስተመጨረሻ ከጲስዲያና ከኢቆንያን የመጡ አንዳንድ ተቃዋሚዎች ጉዳዩን እንዳልነበረ ገለባብጠው ጳውሎስን በድንጋይ ወግረው ወደሞት እንዲቃረብ አደረጉት፡፡

ሐዋ.14፡20-26ን ያንብቡ፡፡ ጳውሎስና በርናባስ ጉዟቸውን ያጠናቀቁት በየትኛው ስፍራ ነበር? ከመንገዳቸው ሲመለሱስ ምን አደረጉ?

---

---

ጳውሎስ « ወደ እግዚአብሄር መንግስት ለመግባት በብዙ መከራ ማለፍ አለብን» (ሮሜ 14፡22) ሲል ምን ማለቱ ነው? እዚህ ጋ እየተናገረ ያለውን እርስዎእንዴት ተለማምደውታል? ከምንም በላይ ምንም አይነት ከባድ «መከራ» ቢደርስብን በእምነት ማደግን እንዴት ልንማር እንችላለን?

## ዓርብ | ነሐሴ 11

**ተጨማሪ ጥናት፥-** ክርስቶስ በዚህ ምድር በነበረበት ጊዜ አይሁዶችንራሳቸውን ከሌሎች ህዝቦች ከመለየት ሊያወጣቸው ተጋ፡፡ የመቶ አለቃው መለወጥ እና የከንአናዊትዋ ሴት ታሪክ ከእስራኤል ህዝብ ውጪ የሱስ በቀጥታ የሰራባቸው ምሳሌዎችነበሩ፡፡ አሁን ጊዜው በአህዛብ መካከል ንቁና ቀጣይነት ያለው ስራ የሚሰራበት ሆነ፡፡ ሁሉም ማህበረሰብ ወንጌልን በደስታ ለመቀበል ስለበራላቸው የእምነት ብርሃን እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ ጊዜው ደረሰ፡፡የአይሁዳውያን አለማመንና ተንኮልየእግዚአብሄርን አላማ አላከሸፈም፤ ምክንያቱም አዲሶቹ እስራኤሎች በወይራ ዛፉውስጥ ገብተዋል፡፡ምኩራቦች ለደቀመዛሙርቱ ዝግ ሁኑባቸው ነገር ግን በተቃራኒው የግልቤቶችና የአህዛብ የነበሩ የህዝብ ህንጻዎች የእግዚአብሄር ቃል ይሰበከባቸው ዘንድ ክፍት ሆኑ፡፡» Ellen G, white, Sketches from the life of paul, P. 51::

“በሚሲዮናዊ ጥረታቸው ሁሉ ጳውሎስና በርናባስ የክርስቶስን ምሳሌ በመከተል መስዋዕት በመሆን ታማኝና ለነፍሳት የሚተጉ ሰራተኞች ለመሆን ፈቃደኛ ነበሩ፡ ፡ በከፍተኛ ንቃትና፣በጉጉት ሳይታክቱና፣ ወደራሳቸው ጉዳይ ፈጽመው ሳያዘነብሉ በጸሎት እየተጉ የእውነትን ዘር ለመዝራት ሳያቋርጡ ሰሩ፡፡ ዘሩን እየዘሩ ደቀመዛሙርቱ ለወንጌል ብለው የነሱን አቋም ለሚወስዱ ሰዎች ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር፡፡ ተግባራዊ የሚሆን መመሪያን በመስጠት የማይነገር ዋጋ ያለውን ነገር አስተባበሩ፡፡ ይህ ቅን የሆነ መንፈሳቸውና እግዚአብሔርን ማክበራቸው አዲስ በመጡት ደቀመዛመርቱ ልብ ውስጥ ስለ ወንጌል መልእክት ወሳኝነት ከፍተኛ ተጽእኖ መፍጠር ቻለ፡፡” Ellen G. white, The Acts of the Apostle, s P. 186

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ትኩረትዎን ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ ነገሮች ከባድሲሆኑ ሸሽቶአቸው በነበረው ታሪክ ላይ ያድርጉ፡፡ ስለ ማርቆስ ጉዳይ ጳውሎስና በርናባስ ክርክር ገጠሙ፡፡ በርናባስ አብሮአቸው እንዲሄድ ሲፈልግ ጳውሎስ ግን እንቢ አለ (ሐዋ.15፡37ን ተመልከቱ)፡፡ ከአመታት በኋላ ግን ጳውሎስ ሲጽፍ «ማርቆስ በአገልግሎቴ ስለሚረዳኝ ከአንተ ጋር ይዘኸውና» (2ጢሞ.4፡11) አለ፡፡ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ለጥሪያቸው ታማኝነታቸውን ማሳየት ላልቻሉ ሰዎችምን ማድረግ እንዳለብን ምን እንማራለን?

2. ጳውሎስንና በርናባስን የልስጥራ ሰዎች አምላክ አድርገው ሲቆጥሯቸው የመለሱላቸውን ምላሽ እስቲ ተመልሰው ይቃኙ (ሐዋ.14፡14-18)፡፡ እግዚአብሔር ለኛ ህይወት ላደረገው ነገር ስፍራውን ለራሳችን ለመውሰድ ስንፈተን እንዴት መመለስ አለብን?

3. ሐዋ.14፡21-23ን ያንብቡ፡፡ ጳውሎስና በርናባስን እንደመነሻነት በመውሰድአዲስ የተለወጡ ሰዎች እምነታቸው እንዲዳብርና እንዲያድግ በግል ብሎም በቤተክርስትያን ደረጃ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?

4. ሰዎች የፈጠሩዋቸው ባህሎችም ሆኑ ለረጅም ጊዜ የቆዩ እምነቶች ልክ የሃይማኖት መሪዎች ጳውሎስን እንደተቃወሙት በእውነት መንገድ ላይ ጣልቃ ስላለመግባታቸው እንዴት እርግጠኞች መሆን እንችላለን?

# ፬ኛ ትምህርት ከነሐሴ 12 - 18

## የኢየሩሳሌም ጉባኤ

*ለዚህ ሳምንት ትምህርት የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቡ:- ሐዋ.15፣ገላ.2፡11-13፣ ዘዳ.12፡43-49 ሮሜ 3፡30፤ ዘሌ.3፡30፤ ዘሌ.18፡30፤ ራዕይ2፡14-20፡፡*

**<u>መታሰቢያ ጥቅስ</u>** :-<<እኛም የዳንነው ልክ እንዲነርሱ በጌታ በኢየሱስ ፀጋ መሆኑን እናምናለን>>(ሐዋ፡15፡11)፡፡

ከሁለት አመታት ቆይታ በኋላ ጳውሎስ እና በርናባስ ወደ አንፆኪያ ወረዱ፡፡ እንደ ወንጌል መልዕክተኛ(ሚሲዮናዊ) እነርሱንሲልኳቸው መላው የቤተክርስትያን አባላት ስለተሳተፉለቤተክርስትያን የደረሰቡበትን ሁኔታ ሪፖርት ማድረግ የሚጠበቅ ነው፡፡ ሪፖርቱ ትኩረት ያደረገው እነርሱ ባሳኩት ጉዳይ ላይ ሳይሆን እግዚአብሔር በእነርሱ በኩል ባከናወነውላይ ነበር፡፡

የሪፖርቱ ፍሬ ነገር ብዙ አይሁዶች ወደ ማመን መጥተው የነበረ ቢሆንምበዋናነት በአህዛብ መካከል ተልእኮው ስላመጣው ስኬት መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ቆርኔሌዎስ ወደ ትዕይንቱ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ያልተገረዙ አህዛብ የመዳን ጉዳይ ትልቅ መነጋገሪያ ሆነ (ሐዋ. ሥራ 11፡1-18)፡፡ ነገር ግን እያሌ ቁጥር ያላቸው አህዛብ ወደ ቤተክርስትያን አባልነት እንዲቀላቀሉ ሲፈቀድነገሮችተወሳሰቡ፡፡ በኢየሩሳሌም ያሉ ብዙ ምዕመናን ጉዳዩ አላስደሰታቸውም፡፡እንደነርሱ ኃሳብ አህዛብ ከእግዚአብሔር ህዝብ ጋር ለመቀላቀልበቅድሚያ መገረዝናአይሁዳዊ መሆን ይገባቸዋል፡፡

ሐዋ. ሥራ 15 በሙሉ የሚያወራው የአህዛብ ችግር አሳሳቢ ደረጃ ላይ ስለ መድረሱና ቤተክርስቲያን መፍትሄ ለማምጣት በህብረት ስለ ሰራችውሥራ ነው፡፡ የኢየሩሳሌም ጉባኤ የሐዋሪያት ቤተክርስቲያን ለመላው አለም ካላት ተልእኮ ጋር በተያያዘ ወሳኝ የታሪክ አቅጣጫ የተቀየረበት ክስተት ነበር፡፡

የዚህን ሳምንት ትምህርት አጥንተው ለነሐሴ 19 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡

## እሁድ ነሐሴ 13

### የጉዳዩ ይዘት

ከጅማሬው አንስቶ በአንጾኪያ የነበረችው ቤተክርስቲያን በሰላምናበህብረት ይኖሩ የነበሩ አይሁዳውያንንና ያልተገረዙ አህዛብንየያዘች ነበረች (ሐዋ.11፡19-21፣ ገላ.3፡11-13)። ይህ ህብረት ግን ከኢየሩሳሌም በመጡ የተወሰኑ አማኝ ቡድኖች ተበጠበጠ፡፡

ሐዋ.15፡1-15ን ያንብቡ፡፡ ቤተክርስቲያን እየተጋፈጠች የነበረችው ችግር ምን ነበር?

---

---

ከይሁዳ የመጡት በተለምዶ አክራሪ ይሁዳውያን(ጁዳይዘርስ)የተባሉት ቁጥር 5 ላይየተጠቀሱትአማኝ ፈሪሳውያን እንደሆኑ ይታመናል፡፡ በዚህ ቤተክርስቲያን የፈሪሳውያን መገኘት እምብዛም አይደንቅም ምክንያቱም ጳውሎስ ራሱ ከመለወጡ በፊት ፈሪሳዊ ነበርና (ፊሊ.3፡5)፡፡ እነዚህ ቡድኖች በራሳቸው ተነሳሽነት ወደ አንጾኪያ የመጡ ይመስላሉ (ሐዋ.15፡24)፡፡ሆኖም በሌላ ክፍል ላይ በአንጾኪያ በተከናወነ ክስተት ያልተገረዙ አህዛብ በቤተክርስቲያን መገኘታቸውሐዋሪያትን ጨምሮ ብዙ አይሁዳውያንን ምቾት ነስቷቸው እንደነበር ተፅፏል(ገላ.2፡11-13)፡፡

ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክት ላይ ይሁዳውያን ስለሆኑ ሰዎች የተነገረው በበጎ ጎኑ ሳይሆን እንደውም ችግር ፈጣሪዎች ስለመሆናቸው ነበር (ገላ.1፡7፣ 5፡10)፤ «ሐሰተኛ ወንድሞች»ም ብሎ ይጠራቸዋል(ገላ.2፡4)፡፡ ውስጣዊ መሻታቸውም በወንጌል ያገኘነውን መንፈሳዊ ነፃነት ማጣጣልና የተለወጡ አህዛብን የህጋዊነትባሪያ ማድረግ ነው፡፡

ኃሳባቸው ለማስተዋል በጣም ቀላልነበር፤ አህዛብ ካልተገረዙና የአይሁድን ሜዳዊ ህግ ካልታዘዙ መዳን አይችሉም የሚል ነበር፡፡ ድነት እነርሱ እንደሚያምኑት የተሰጠው እግዚአብሔር ቃል ኪዳን በገባላቸው ህዝቦችውስጥ ብቻ ነው፤ስለዚህ በብሉይ ኪዳን መሰረት የእግዚአብሔር የተመረጠ ህዝብ የመሆኛው መንገድ መገረዝ ብቻ እንጂ ሌላ መንገድ የለም (ዘፍ.17፡9-14፣ ዘዳ.12፡48)፡፡ በአጭሩ አህዛብ መዳን የሚችሉት በቅድሚያ የአይሁድ ተከታይና ወገን ሲሆኑ ብቻ ነው፡፡

ጳውሎስ እና በርናባስ የቀረበው መስፈርት (ቅድመ ሁኔታ) ከወንጌል ባህሪ እና አላማ ጋር የሚፃረር እንደሆነ ስላወቁ አልተስማሙም፡፡ ከይሁዳ የመጡት አክራሪዎች

ያቀረቡበት ጠብ አጫሪ አቀራረብበሐዋ.15፡2 ላይ እንደምናነበው ክርክርን«የከረረ» ግጭትንና ጠብን አስከተለ፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ብቻ የሚፈታ ቀላል ጉዳይ አልነበረም፡፡ የቤተክርስትያን ህብረት ጉዳይ አደጋ ውስጥ ገባ፡፡በአንጾኪያ የነበሩ ወንድሞችም የተወሰኑ ሰዎችን ወክለው በመምረጥ ጳውሎስንና በርናባስን በመጨመር መፍትሄ እንዲያመጡ ወደ ኢየሩሳሌም ላኳቸው፡፡

በአክራሪ አይሁዳውያን ቦታ ራስዎንያስቀምጡ፡፡ ለዚህ ጉዳይ የሚያስቀምጧቸው የመከራከሪያ ነጥቦች ምን ሊሆኑይችላሉ?

## ሰኞ ነሐሴ 14

## ግዝረት

በዚህ ክርክርላይ ታላቁ የግጭት መንስኤ ግዝረት ነበር፡፡ ይህ ሰብአዊ ዘር ያቋቋመው አይደለም (ማቴ.15፡2፣9 ጋር ያነፃፅሩ) ፡፡ ይልቁንም እግዚአብሔር ራሱ ለአብርሃም እና ለዘሩ ቃልኪዳን የገባለትን የራሱ የተመረጠ ህዝብ ስለመሆኑ የሰጠው ምልክት ነበር (ዘፍ.17፡9-14)፡፡

ዘፀ.12፡43-49ን ያንብቡ፡፡ እስራኤላዊ ሆኖ ከተወለደ ሰው በተጨማሪ ሌላ መገረዝ ያለበት ሰው ማን ነበር?

---

---

የቃል ኪዳን በረከት ተወስኖ የተሰጠው እስራኤላዊ ተወላጅ ለሆኑግለሰቦች ብቻ አልነበረም፡፡ ማንኛውም ባርያ ለነበረ ወይንም እንግዳ (መጻተኛ) ሆኖ ይኖር ለነበረና ይህንን አብሮ ለመካፈል ብሎም ለመገረዝ ፈቃደኛ ለሆነ ሰው ሁሉ ነበር፡፡ ከግዝረት በኋላ እንግዳ (መፃተኛ) የነበረው ሰው በእግዚአብሄር አይን እንደ እስራኤል ተወላጅ ይታያል፡«ከዛም እንደ ተወላጅ ይቆጠራል» (ዘፀ. 12፡48)፡፡

ስለዚህ ግዝረት(ለወንዶች) የእግዚአብሔር የቃልኪዳን ህዝቦች ይሆኑ ዘንድ የሚያስችል አስፈላጊ ስርአት ነበር፡፡ ስለዚህ የሱስ የእስራኤል መሲህ ሆኖ ስለመጣ አህዛብ ከዚህ ድነት ተጠቃሚ ለመሆን አስቀድመው አይሁድ መሆን ይገባቸዋል ብለውአክራሪ አይሁዳውያኑ ማሰባቸው የሚጠበቅ ነው፡፡

ሮሜ3፡30፣ 1ቆሮ.7፡18፣ ገላ.3፡28፣5፡6ን ያንብቡ፡፡ ስለግዝረት ጳውሎስ የነበረው መረዳት ምን ነበር?

---

---

አይሁዶችን ሳይቀላቀል ማንም አህዛብ መዳን አይችልም በማለታቸው እነዚህ ግለሰቦች ሁለት የተለያዩ እሳቤዎችን እየደበላለቁ ነበር፤ቃልኪዳንንና ድነትን፡፡ የእግዚአብሔር የቃልኪዳኑ ህዝብ አባል መሆን ብቻውን ድነታችንን አያረጋግጥልንም (ኤር.4፡4፣ 9፡25)፡፡ በተጨማሪም አብርሃም ራሱየዳነው(የፀደቀው) በእምነት ነበር፤ ያ ደግሞ የሆነው ከመገረዙም አስቀድሞ ነው እንጂ ስለተገረዘ አልነበረም (ሮሜ4፡9-13)፡፡ ድነት ሁልጊዜም የሚሆነው በእምነት ነው ቃልኪዳን ደግሞ እግዚአብሔር ራሱንና የድነት እቅዱን በጸጋውአማካኝነት ለመላው አለም የሚያሳውቅበት መንገድ ነው፡፡ እስራኤል የተመረጠውም ለዚሁ አላማ ሲባል ነበር (ዘፍ.12፡1-3)፡፡

ችግሩ ግን ቃልኪዳኑንና ድነትን በቅርበት የዚህን ያህል ማስተሳሰር አማኞች ግዝረትን እንደ ወሳኝና ዋነኛ ተግባር እንዲወስዱትአድርጓቸዋል፡፡ የእግዚአብሄር የማዳን ፀጋ ግን የሰው ስራ በሚከናወንበትአይሠራም፡፡ስለዚህ ግዝረትን እንደ መዳንመንገድ አማኝ በሆኑ አህዛብ ላይ መጫንየወንጌልን ትክክለኛ አቅጣጫ የሚያፋልስ ነበር (ገላ.1፡7፣ 2፡3-5)፡፡ የእግዚአብሔርንም ጸጋ ዋጋ ያሳጣል(ገላ.2፡21)፤ የሱስም አይጠቅመንም ማለት ነው(ገላ.5፡2)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የድነትን አለማቀፋዊ ባህሪ የሚክድ ሆነ ማለት ነው (ቆላ.3፡11፣ ቲቶ2፡11)፡፡ጳውሎስ ፈጽሞ ከእንደዚህ አይነት አስተሳሰብ ጋርአይስማማም፡፡

ድነት የሚገኘው የትክክለኛይቱ ቤተክርስቲያን አባል በመሆን ብቻ ነው የሚለው አስተሳሰብ አደገኛነት ምን ላይ ነው?

ማክሰኞ ነሐሴ 15

## ክርክሩ

ሐዋ.15፡7-11ን ያንብቡ፡፡ በኢየሩሳሌም ለነበረው ክርክር ጴጥሮስያበረከተውአስተዋጽኦ ምን ነበር?

በርግጥም ሉቃስ በስብሰባው ላይ ስለተከናወኑጉዳዮች ሙሉ ዝርዝር አላቀረበልንም፡ ፡የአክራሪ አይሁዳውያኑን መከራከሪያ ነጥቦች (ሐዋ.15፡5) እንዲሁምጳውሎስና በርናባስ የሰጡትን ምላሽ ማወቅ የሚጠቅም ነው(ሐዋ.15፡12)፡፡ የጴጥሮስና የያዕቆብ ንግግር ብቻ መፃፉእነዚህ ሰዎች ከደቀመዛሙርት መካከል ምን ያክል ከፍ ያለ ቦታ እንደነበራቸው የሚያሳይ ነው፡፡

ጴጥሮስ ለሐዋሪያትና ሽማግሌዎች ባደረገው ንግግር ከአመታት በፊት ከቆርኔሌዎስ ጋር ስላጋጠመው ልምምድ በማውሳት ተናገረ፡፡ በዚህ ስፍራም ቀድሞ በኢየሩሳሌም ወገኖች መካከል ያቀረበውን መከራከሪያ የሚመስል ኃሳብ ነበር ያቀረበው (ሐዋ.11፡ 4-17)፡፡ እግዚአብሔር ራሱ የቆርኔሌዎስን መለወጥ መቀበሉን በጴንጤቆስጤ ቀን ለሐዋሪያቱ እንደሆነው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለርሱና ለቤተሰቡ በመስጠት አረጋግጧል (ምንም እንኳን እርሱ ያልተገረዘ አህዛብ ቢሆንም)፡፡

በመለኮታዊ እቅዱ የተነሳ እግዚአብሔር ድነትን በተመለከተ በአይሁድ እና በአህዛብ መካከል ምንም ልዩነት እንደሌለ ለማስረዳት ጴጥሮስን ተጠቀመ፡፡ ምንም እንኳን ከብሉይ ኪዳን ህግና ደንብ የመንጻት ጥቅምን ባያገኙም ያልነፁ አይባሉም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ራሱ ልባቸውን ስላነፃው ነው፡፡ የጴጥሮስ የመጨረሻ ንግግር ከጳውሎስ ከምንጠብቀው ንግግር ጋር ተመሳሳይ ነው፡- ‹‹እኛም የዳንነው ልክ እንደነርሱ በጌታ በኢየሱስ ፀጋ መሆኑን እናምናለን፡፡›› (ሐዋ.15፡11)፡፡

ሐዋ.15፡13-21ን ያንብቡ፡፡ ለአህዛብ ችግር ያዕቆብ ያቀረበው የመፍትሄ ሀሳብ ምን ነበር?

---

---

የያዕቆብ ንግግር በአመራር ላይ እንደነበርየሚያሳይ ነው (ከሐዋ. ሥራ 12፡17፣ 21፡18፣ ገላ.2፡9-12 ጋርያነጻጽሩ)፡፡ስለ ዳዊት ቤት እንደገና መጠገንበአሞጽ ትንቢት(አሞፅ 9፡ 11-12) የዳዊት ዙፋን ስለመመለሱ የተነገረውን ትንቢት የተረዳበትን መንገድ ባናውቅም የያዕቆብ ዋነኛ አላማ እግዚአብሔር አህዛብ እንዲቀላቀሉአስቀድሞ እድል እንደሰጠና ዳግም ‹‹የእግዚአብሔር ህዝብ›› በመሆናቸው ከእስራኤላውያን ጋር ስለመቀላቀላቸው ለመግለጽ ነው፡፡

በዚህ የተነሳ የርሱ ውሳኔ በተለወጡ አህዛብ ላይ በእስራኤል ምድር መኖር የሚሹ መፃተኞች ከሚጠበቅባቸው ውጪ ምንም አይነት ገደብ እንዳይጫንባቸው ነበር፡፡

## ረቡዕ ነሐሴ 16

### የሐዋሪያት ድንጋጌ

ሐዋ.15፡28-29ን ያንብቡ፡፡ ጉባኤው በተለወጡ አህዛብ ላይ ያስተላለፈው አራት ድንጋጌ ምን ነበር?

---

---

ጉባኤው ለተሰበሰበበት ዋነኛ አጀንዳ በቂ በሚባል ደረጃ መፍትሄ ሰጠ፡፡ ድነት በፀጋ ከመሆኑ የተነሳ አህዛብ ወደ ቤተክርስቲያን ለመቀላቀል የግድ መገረዝ እንደሌለባቸው ተወሰነ፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ አራት ነገሮች መራቅ ግድ ይላቸዋል፡፡

**1ኛ .** ለጣኦት ከተሰዋ በኋላ ለግብዣወይም ለገበያ ሽያጭ የቀረበን ሥጋ ከመብላት

**2ኛ .** ደም ከመብላት 3ኛ.ታንቆ የሞተ እንስሳን ሥጋ ማለትም ደሙ በስጋው ውስጥ እያለ ከመመገብና4ኛ. ከተለያየ አይነት የዝሙት እርኩሰት መራቅ ነበር፡፡

አያሌ ክርስትያኖች ዛሬ ላይ እነዚህን የምግብ ድንጋጌዎች (ከ1-3 ያሉትን ድንጋጌዎች) ለዚያ ጊዜ ብቻ እንደነበሩ ይቆጥራሉ፡፡ እነዚህ ነገሮች ለአይሁድ ማህበረሰብ አፀያፊ ስለነበሩ ይህ ድንጋጌ በአይሁድና በአህዛብ አማኞች መካከል የነበረውን ክፍተት ለማጥበብ ብቻ የታቀዱ ናቸው ብለው ይሞግታሉ፡፡ ሌሎቹ የብሉይ ኪዳን ህግጋት ማለትም በዘሌዋውያን ላይ የሚገኘውየአመጋገብ ህግ (ዘሌ.11) እና የሰንበትትእዛዝ (ዘፀ.20፡8-11)በዚህ ዝርዝር ውስጥ ስላልተካተቱ ክርስትያኖችም ሊጠብቋቸው አይገባም ብለው ያስባሉ፡፡

የሐዋሪያት ድንጋጌ ተብሎ የተጠራው ግን ጊዜያዊ ወይንም ለክርስትያኖች ግብረገብ አዲስ ትእዛዝን በማምጣት ከብሉይ ኪዳን ጋር የተያያዙ ነገሮችን ሁሉ ያስወገደ ሂደት አልነበረም፡፡ እንደውም በመንፈስ ቅዱስ ምሪት አማካኝነት (ሐዋ.15፡28) ሐዋሪያት እና የቤተክርስትያን ሽማግሌዎች ከእስራኤል ጋር ለሚኖሩ መፃተኞች የተነገረውን የዘሌዋውያን 17-18ንመመሪያ አስቀጥለውታል፡፡

ከዘሌዋውያን አውድ አንጻር እነዚህ ድንጋጌዎች አረማዊነትን ስለመተው ይናገራሉ፡፡ ማንኛውም መፃተኛ በእስራኤል መኖር ከፈለገ በእግዚአብሄር የማያምኑ ሰዎችየሚያደርጉትን ያደገበትንድርጊት መተው አለበት (ዘሌ.18፡30)፡፡ ልክ እንደዚሁአምኖቤተክርስቲያንን መቀላቀል የፈለገ አህዛብ ሁሉ አረማዊ የሆነ ተግባርን ላለመፈጸም ቁርጥ አቋም ማሳየት ነበረበት፡፡

ሆኖም ይህ የመጀመርያው ደረጃ ብቻ ነበር፡፡ ይህን ካደረገ በኋላ እርሱ/እርሷ አለማቀፋዊ የሆነውን ትእዛዝ በመጠበቅ የእግዚአብሄር ፈቃድ ይፈጽሙ ዘንድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ይህም የሜዳዊ ህግ ያልሆኑትን(ከሙሴ ህግ በፊት የነበሩትን) ለምሳሌ ሰንበትን (ዘፍ.2፡1-3)መጠበቅ እና ንጹህ የሆነውንና ያልሆነውን መለየት ይገባቸዋል(ዘፍ.7፡2)፡፡

ድንጋጌዎቹጊዜያዊ ብቻ አለመሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ ለምሳሌ ራእይ2፡14፣20 ላይ የመጀመሪያው እና የመጨረሻው ድንጋጌ ተደጋግሞ ተጽፏል፤በውስጠ ታዋቂነት ሌሎች ሁለቱ ህጎች መኖራቸውም ግልጽ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የታሪክ ማስረጃዎች የሚያሳዩን ድንጋጌዎቹ ከአዲስ ኪዳን ዘመን በኋላም ቆይተው ለኖሩ ክርስትያኖች ይሰሩ እንደነበረ ነው፡፡

ግጭቶች በሚነሱበት ጊዜ አብረን ለመቀመጥ፣እርስ በርስ ለመስማማትና በጉዳዩ ላይ ለመወያየት በአክብሮትና በትህትና መንፈስ ለማውራት እንዴት መማር እንችላለን?

**ሐሙስ ነሐሴ 17**

## ደብዳቤ ከኢየሩሳሌም

ሐዋ.15፡22-29ን ያንብቡ፡፡ የጉባኤውን ውሳኔ በተመለከተ የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ምን ተጨማሪ እርምጃን ወሰደች?

---

---

የመጀመሪያ እርምጃ የነበረው ለአህዛብ አማኞች ምን እንደተወሰነ የሚገልጽ ደብዳቤ ጽፎ ማሳወቅ ነበር፡፡ኢየሩሳሌም በነበሩሐዋሪያትና ሽማግሌዎች ስም የተጻፈው ደብዳቤ የኢየሩሳሌም ቤተክርስትያንን የሥልጣን ተዋረድ የሚያንጸባርቅ ይፋዊ ሰነድ ሲሆን ይህም የሐዋሪያት አመራር በሌሎች የክርስቲያን ማህበረሰብ ላይ ስለነበር ነው፡ ፡ የተጻፈውበ49ዓ.ም ሲሆን ምናልባትም ጉባኤው የተቀመጠበት ቀን ነው፡፡ ይህ ደብዳቤ ከቀደምት ክርስትያን ሰነዶች አንዱ ነው፡፡

የኢየሩሳሌምቤተክርስትያንም ሁለት ልኡካንን ማለትም ይሁዳና ሲላስ ጳውሎስን አጅበው ወደ አንጾኪያ እንዲወርዱ መደቡ፡፡ ተግባራቸውም ደብዳቤን ማድረስ እና ስለ ደብዳቤው ይዘት አረጋግጦ መናገር ነበር፡፡

ሐዋ.15፡30-33ን ያንብቡ፡፡ በአንጾኪያ ያለችው ቤተክርስቲያን ለደብዳቤው የሰጠችው ምላሽ ምን ይመስል ነበር?

---

---

ደብዳቤው በሚነበብበት ጊዜ ከማበረታቻ መልእክቱ የተነሳ ቤተክርስትያኒቱ በከፍተኛ ደስታ ተዋጠች፡- ለተለወጡ አህዛብ ግዝረት የግድ የሚያስፈልግ መስፈርት አልነበረም፡፡ እንዲያደርጉ ደብዳቤው የጠየቃቸውን ድንጋጌም አልተቃመውም (አራቱ ድንጋጌዎችን)፡፡በቀዳሚዋ ቤተክርስቲያን ተነስቶ የነበረው አሳሳቢ መከፋፈል ቢያንስ በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ ተፈታ፡፡

በጉባኤው ማገባደጃ ላይ የጳውሎስ ወንጌል በኢየሩሳሌም በሚገኙ የቤተክርስቲያን መሪዎች ዘንድ ሙሉ ተቀባይነትን ስላገኘለጳውሎስና በርናባስ አመኔታቸውን ለማሳየት የትብብር ቀኝ እጃቸውን ሰጧቸው (ገላ.2፡9)፡፡ ነገር ግን አይሁዳዊ የሆኑ ክርስትያኖች በአይሁድ ህግ መኖራቸውን ሲቀጥሉ የመንፃት ስርዓት ካልፈፀሙት አህዛብ ጋር በማእድ መቀመጥ አስቸጋሪ ሆኖባቸው ነበር፡፡

ይህ ጉዳይ ለአብነት ያህል ጴጥሮስ በገላ.2፡11-14 ታሪክ ላይ ያደረገውን ይነግረናል፡ ፡ኤለን ኋይት ስትናገር «ደቀመዛሙርቱ እንኳን የጉባኤውን ውሳኔ በፈቃደኝነት ለመቀበል ልባቸውን አላዘጋጁም፡፡» The Acts of the Apostles, P.197፡፡

እስቲ ለራስዎ ሀቀኛ ይሁኑና ከሌላ ዘር ፤ባህል ብሎም የኑሮ ደረጃ ከመጡ ሰዎች ጋር ለመቀላቀልና ህብረት ለማድረግ ምን ያህል ያስቸግሮታል? ለወንጌል ፀር የሆነውን ይህንን ጉዳይበመከላከል ማስወገድ የምንችለው እንዴት ነው?

## ዓርብ | ነሐሴ 18

**ተጨማሪ ጥናት፡** «የተለወጡ አይሁዳውያን እግዚአብሔር አቅዶ በከፈተው መንገድ በፍጥነት መሄድ አልቻሉም፡፡ በአህዛብ መካከል ሐዋሪያት በሰሩት የስራ ውጤት የተነሳ ቆይተው የተለወጡ ሰዎች ብዛት ከተለወጡ አይሁዳውያን ቁጥር ይልቃል፡ ፡ አይሁዳውያን የፈሩት የህጋቸው ደንቦችና ስርአቶች አህዛብ የቤተክርስቲያን አባል እንዲሆኑ እንደቅድመ ሁኔታ ካልተቀመጡ ለዘመናት ከሌሎች የተለዩ ህዝቦች ሆነው እንዲቆዩ ያደረጋቸው ብሔራዊ መታወቂያ የወንጌልን መልእክት በሚቀበሉት ዘንድ እንዳይጠፋ ነው፡፡»-Ellen G white, The Acts of the Apostles, P.189፡፡

<<በቤተክርስቲያን እይታ ውስጥ ያሉ የአይሁድ ክርስቲያኖች የአይሁድ መመረጥና የተለየ ህዝብ መሆን ወደ ነበረበት ተመልሶ እንዲመጣ ፈልገዋል ፡፡ የክርስትያን ቤተክርስቲያን ከአይሁድ ስርአት እና ባህል እየራቀ መሄዱን ያዩት ለአይሁድ ተሰጥቶ የነበረው ቅዱስና የተለየ የነበረው ይህ ስርአት አዲስ በመጣው የእምነት ብርሃን አማካኝነት ጠፋ፡፡ በዚህ ውስጥ ትልቁን ሚና በተጫወተው ጳውሎስ ላይ ብዙዎች ተበሳጩበት፡፡ ደቀመዛሙርቱ እንኳን የጉባኤውን ውሳኔ ለመቀበል ሙሉ በሙሉ ዝግጁዎች አልነበሩም፡፡ አንዳንዶች ለስርአታቸው ቀናኢ ስለነበሩ ጳውሎስን ጠሉት ምክንያቱም የአይሁድን ህግ በተመለከተ የእርሱ መርህ ልል እና ግድየለሽነትን የሚያንፀባርቅ ነው ብለው አስበዋልና፡፡»- page 197.

# የመወያያ ጥያቄዎች

1. በክፍልዎ ውስጥ ወደ ሰኞ ክፍል የመጨረሻ ጥያቄ ተመልሰው ይወያዩ፡ ፡ «የትክክለኛዋ » ቤተክርስቲያን አባል መሆናችን ብቻ ድነታችንን እንደማያረጋግጥልን የምናስተውለው እንዴት ነው? ለምሳሌ ጥንታዊ እስራኤላውያን በርግጥም «ትክክለኛ ቤተክርትያን» ውስጥ ነበሩ ያ ማለት ግን ሁሉም ይድናሉ ማለት አይደለም፡፡ በትክክለኛው ቤተክርስቲያን ውስጥ መሆን ብቻ ድነታችንን አያረጋግጥም ታዲያ የቤተክርስቲያኒቱ አካል የመሆን ጥቅሙ ምንድነው?

2. ያልተገረዙ አህዛብን ወደ እምነት ማህበር በመቀበል የቀደመችው ቤተክርስቲያን የተጋፈጠችው አንዱና ዋነኛው የአስተዳደራዊ ጉዳይ ነበር፡፡ ከዚህ ጋር የሚነፃፀር ዛሬ በቤተ ክርስትያናችን ያለ ምን ጉዳይ አለ? የሐዋ.15 ምሳሌ ጉዳያችንን እንዴት መፍታት እንዳለብን ምን ያስተምረናል?

3. በክፍልዎ ውስጥ የተወሰኑ ሰዎችን መድቡና አህዛቦች ቤተክርስቲያንን ከመቀበላቸው በፊት የአይሁድ ተከታይ መሆን አለባቸው ምክንያቱም ቃልኪዳኑ ለእስራኤል ነው የተሰጠው ብለው እንደሚከራከሩበት አይሁዳውያን ይሁኑ፡፡ የመከራከሪያ ነጥባቸው ምንድነው እናንተስ ለዚህ ያላችሁ ምላሽ ምንድነው? እንደዚህ አይነት ክርክሮች አሁን ላይ ግልጽ የሆኑ ቢሆንም በተለያየ ጊዜ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደነበሩ እንዴት እንረዳለን?

# ፱ኛ ትምህርት ከነሐሴ 19 - 25

## የጳውሎስ ሁለተኛ ሚስዮናዊ ጉዞ

**ሰንበት ከሰዓት**

ለዚህ ሳምንት ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቡ፡- ሐዋ. ሥራ 16፤ ሮሜ 3፡ 28፤ ገላ. 2፡16፤ሐዋ፣ ሥራ 17፤ 1ኛቆሮ.1፡23፤ ሐዋ18፡1-10፡፡

**<u>መታሰቢያ ጥቅስ</u>** ፡-<<አትፍራ ተናገር ዝምም አትበል እኔ ከአንተ ጋር ነኝና ማንም በአንተ ላይ ተነስቶ ሊጎዳህ አይችልም፡፡ በዚህ ከተማ ብዙ ሰዎች አሉኝና ፡፡>>

(ሐዋ. ሥራ 18፡9 - 10)

ወደ አንጾኪያ ስንመለስ ጳውሎስና በርናባስ ቤተክርስትያንን በቃሉ እያበረታቱና የበለጠ ወንጌልን እየሰበኩ እናገኛቸዋለን፡፡ ከፍተኛ የሆነ አለመስማማት ወደ መለያየት ሲመራቸው ላየ ይህ በአብሮነት የሰሩበት የመጨረሻ ጊዜያቸው ይመስለዋል፡ ፡ የጳውሎስና በርናባስ አለመስማማት ምክንያቱ ማርቆስ ነበር፤ እርሱም የበርናባስ የወንድሙ ልጅ ነበር፡፡ (ቆላ.4፡10) ጳውሎስ ቀድሞ በወንጌል ወደ ደረሱበት ስፍራ በርናባስ እንዲመጣ ሲጋብዘው በርናባስ ግን የወንድሙን ልጅ አብሮት ሊወስደው ፈለገ፡፡ ነገር ግን ጳውሎስ ማርቆስ በፊት የሠራውን ስህተት በማንሳት ሃሳቡን ተቃወመው (ሐዋ.ሥራ 13፡13)፡፡ የጳውሎስና በርናባስ መለያየት ግን ወደ ባርኮት ተለወጠ፡፡ ምክንያቱም በመለየየታቸው የተነሳ አስቀድመው ካቀዱት በላይ ሰፊ የሆነ ስፍራን ማካለል ችለዋልና፡፡ በርናባስ ማርቆስን ይዞ ወደቆጵሮስ ተመለሰ፤ ይህም ስፍራ በርናባስ ያደገበት ስፍራ ነበር (ሐዋ. ሥራ4፡36)፡፡ በዚህ ጊዜም ጳውሎስ ሲላስን ወደርሱ እንዲመጣ ጠራውና ወደ ቂሳርያ እና ወደ ኪልቂያ ሄደ በዛም ቤተክርስትያንን አጠናከረ፡፡ ጳውሎስ ወደ አንጾኪያ ለመጀመርያ ጊዜ ከመምጣቱ በፊት በጠርሴስ ለአያሌ አመታት ቆይቷል (ሐዋ. ሥራ9፡30፣11፡25-26)፡፡ አሁን ደግሞ የመሰረተውን ህብረት ዳግም የመጎብኘት እድል አገኘ፡፡ ያም ቢሆን ግን የእግዚአብሔር እቅድ ጳውሎስ አስቀድሞ ካቀደው እቅድ እጅጉን የላቀ ነበር ፡፡

የዚህን ሳምንት ትምህርት አንብበው ለ ነሐሴ 26 ሰንበት ይዘጋጁ።

## እሑድ ነሐሴ 20

# ወደክስጥራ መመከስ

ሉቃስ መርጦ ከፃፋቸው ክስተቶች መካከል የጳውሎስ ወደ ልስጥራና ደርቤ የመመለስ ታሪክ ነው፡፡ ስለ ሶርያ እና ኪልቅያ የነገረን ነገር ቢኖር ጳውሎስ በእነዚህ ስፍራዎች ሲያልፍ ቤተክርስትያንን ያበረታታ እንደነበር ብቻ ነው (ሐዋ. ሥራ 15፡41)፡፡

ሐዋ. ሥራ 16፡1-13 ያንብቡ፡፡ ሌሎችን ለመድረስ ጳውሎስ ያለው ግለት ለኛ ምን ትምህርት ይሰጠናል?

---

---

የጢሞቴዎስ አባት አህዛብ ቢሆንም እናቱ ግን አይሁዳዊ ሆና በጌታ ያመነች ነበረች፤ ስሟም ኢዩኒስ ነበር፡፡ ጢሞቴዎስ ምንም እንኳን ቢገረዝም ከልጅነቱ ጀምሮ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ያውቃል (2ኛጢሞ. 3፡15) ሃይማኖተኛ ሰውም ነበር፡፡ እንደ ክርስትያንነቱ በአካባቢው ያሉ አማኞች የሚያከብሩትና የሚያደንቁት ነበር፡፡

አይሁዶች በእናቱ በኩል አይሁዳዊ ስለሆነ አይሁዳዊ አድርገው ቆጠሩት፡፡ ስለዚህ ጢሞቴዎስ አይሁዳዊ ነው፡፡ በተወለደ በስምንተኛው ቀን ግን አልተገረዘም፡፡ አባቱ ግሪካዊ ስለነበር ግርዘት ኋላ ቀር ስርአት ነው ብሎ አስቦ ነበር፡፡

ጳውሎስጢሞቴዎስ የስራ አጋሩ እንዲሆን ቢፈልግም ያልተገረዘ አይሁዳዊ በመሆኑ በምኩራብ ህግ መሠረት ወደ ምኩራብ መግባት ስለማይፈቀድለትእንዲገረዝ አደረገው፡፡ ጳውሎስ ይህንን ያደረገበት መነሻ ሃሳቡ ተግባራዊ መሆን ያለበት እንጂ ከሚሰብከው የወንጌል ስብከት ተቃራኒ እንደ ሆነ ሊታሰብ አይገባም፡፡

ጳውሎስ በመጀመርያ ጉዞው ያያቸውን ስፍራዎች ደግሞ ሲጎበኝ ሳለበደቡብ ምእራብ አቅጣጫ ወደሚገኘውና የእስያ አውራጃ ክፍል ወደሆነው ስፍራ ለመሄድ ወሰነ፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ይህንን እንዳያደርግ ከለከለው፡፡ ስለዚህም ወደ ሰሜን ተጓዘና ወደቢታንያ ለመድረስ ሞከረ፡፡ ነገር ግን አሁንም ግልጽ ባልሆነ መንገድ ወደዛ ስፍራ እንዳይሄዱ መንፈስ ቅዱስ ከለከላቸው፡፡ በሚስያ እያለፈ ባለበት ሰዓት የጳውሎስ ብቸኛ አማራጭ የነበረው ወደ ምዕራብ አቅጣጫ የመርከብ ወደብ ወደ ሆነቸው ወደ ጢሮአዳ መሄድ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳትም ወደ ብዙ አቅጣጫዎች መሄድ ይችላል፡፡

በሌሊት ራዕይ ግን እግዚአብሄር ባህሩን አቋርጦ ወደ መቄዶንያ እንዲሄድ አሳየው፡፡ ስለ ራእዩ አብረውት ያሉ ሰዎች ሲወያዩ የደረሱበት ድምዳሜ እግዚአብሄር ወንጌልን ለመቄዶንያ ሰዎች እንዲያካፍል እንደጠራው ነው፡፡

ጳውሎስ ለምን ጢሞቴዎስን እንደገረዘው እስቲ ያስቡ፡፡ እኛ የማንስማማባቸውን አንዳንድ ነገሮች ወይም አስፈላጊ አይደሉም የምንላቸውን ነገሮች በማድረግ ትልቅ ተጽእኖ ሊያመጡ የሚችሉ ነገሮችን መፍጠር እንደምንችል ይህ እንዴት ያስተምረናል?

## ሰኞ ነሐሴ 21

### ፊሊጵስዮስ

ጳውሎስና አጋሮቹ መቄዶንያ ሲደርሱ በአውሮፓ የመጀመርያውን የክርስትያን ህብረት ወደ መሰረቱበት ወደ ፊሊጵስዮስ ተጓዙ፡፡

ሐዋ.ሥራ 16፡11-24ን ያንብቡ፡፡ እነዚህ ሚሽነሪዎች በሰንበቱ ቀን ወዴት ሄዱ? ለምን? በዛ ስፍራስ ምን ሆነ?

____________________________________________

____________________________________________

ጳውሎስ ወደ ከተማ በደረሰ ቁጥር ልምዱ በአካባቢው የሚገኘውን ምኩራብ በሰንበት ቀን በመጎብኘት ለአይሁዶች መመስከር ነበር (ሐዋ. ሥራ13፡14፤42-44፤17፡1-2፤18፡4)፡፡ በፊሊጲስዮስ እርሱና የእርሱ ቡድኖች(አይሁድና አህዛብ ከሆኑ ሴቶች ጋር) ለመፀለይ ወደ ወንዝ ዳርቻ ሄዱ፡፡ ምናልባትም በከተማው ምኩራብ የለም ይሆናል፡፡ የዚህ ኃሳብ አስፈላጊነት ጳውሎስ በሰንበት ቀን ወደ አይሁድ ምኩራብ የሚሄደው በወንጌል አላማ ብቻ ሳይሆን ቀኑ የአምልኮ ቀን ስለሆነ ለማምለክ ጭምር ነበር፡፡

ሐዋ. ሥራ16፡25-34ን ያንብቡ፡፡ ስለ ወህኒ ቤቱ ጠባቂ መለወጥ እያሰላሰሉ፤ ለመዳን ምን ማድረግ ይጠበቅበት እንደነበር ያስቡ?

____________________________________________

____________________________________________

ለወህኒ ቤቱ ጠባቂ ጳውሎስና ሲላስ የመለሱት ምላሽ ከወንጌል ኃሳብ ጋር ሙሉ በሙሉ የተጣጣመ ነው፡፡ ምክንያቱም መዳን የሚገኘው ሙሉ በሙሉ በክርስቶስ በማመን ነውና (ሮሜ 3፡28፤ገላ.2፡16)፡፡ ከዚህ ክፍል በመነሳት መደምደም የማንችለው ነገር ቢኖር ለመጠመቅ ሌሎቹን መሠረታዊ አስተምህሮዎችና ተግባር ተኮር መመሪያዎች ትቶ በየሱስ ማመን ብቻ አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡

ስለ ወህኒ ቤቱ አለቃ ምን የምናውቀው ነገር አለ? አይሁዳዊ ነው ወይስ ከአይሁድነት የተቀየረ? የትኛውንም ቢሆን የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር ኢየሱስን ጌታና አዳኝ አድርጎ ማመን ነው፡፡ አህዛብ ሆኖ ልክ እንደ ቆርኔሌዎስ፣ ሊዲያና ሌሎች እግዚአብሔርን የሚያውቅና የሚያመልክ የነበረስ ቢሆን? ቀደም ብሎ በከተማው ውስጥ ጳውሎስ ያስተማረባቸው ስብሰባዎች ላይ ተገኝቶ የነበረስ ቢሆን? እርሱ ማንም ቢሆን ስለርሱ የተፃፈው ነገር ማጠሩ በደንብ ሳይማሩ በአጭር ጊዜ ለመጠመቅ ሰበብ ሊሆን አይገባውም፡፡

ሐዋ16፡31-34ን ያንብቡ፡፡ ይህ ክፍል የክርስቶስ መስዋዕትነት ምን ያህል የተሟላ እንደሆነ ምን ያስተምረናል? ቀን በቀን እንዴት አድርገን ነው የክርስቶስን ጸጋ እኛን የመሸፈኑ ተስፋ ላይ ብቻ እርግጠኛ ሆነን ልባችን ሊያርፍ የሚችለው?

## ማክሰኞ ነሐሴ 22

### ተሰሎንቄ እና ቤርያ

ጳውሎስና ሲላስ ከእስር ቤት ሲለቀቁ ከፊሊጵስዮስ ለቀው ሄዱ (ሐዋ. ሥራ16፡35-40)። ጳውሎስና አጋሮቹ ከፊሊጵሲዮስ ተነስተው የመቄዶንያ ዋና ከተማ ወደ ሆነቻው ወደ ተሰሎንቄ አቀኑ፡፡

ሐዋ. ሥራ 17፡1-9ን ያንብቡ፡፡ በተሰሎንቄ የሚገኙ አይሁዶች ጳውሎስ በአህዛብ መካከል የሰበከውን ፍሬያማ ስብከት እንዴት ተቀበሉት?

---

---

አሁንም ጳውሎስ ወንጌልን የሚያካፍልበትን ምኩራብ ሲፈልግ እናገኘዋለን፡፡ ቁጥራቸው አያሌ የሆነ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ግሪኮች እና የማይናቅ ቁጥር ያላቸው እውቅ ሴቶች በጳውሎስ መልእክት አመኑ፡፡ እነዚህ የተለወጡ ሰዎች ከጳውሎስና ሲላስ ጋር ተባበሩ»(ሐዋ.17፡4)፡፡ የተለየ ቡድን መስርተው ከምኩራብ ውጪ በኢያሶን ቤት ይሰበሰቡ ነበር፡፡

የነርሱ ተቃዋሚዎችም በቅናት ተነሳስተው አመጽ ቀሰቀሱ፡፡ ፍላጎታቸውም ጳውሎስንና ሲላስን (ጢሞቲዎስ አልተጠቀሰም) በከተማው ባለስልጣናት ፊት በማቅረብ ለመክሰስ ነበር፡፡ ሚሽነሪዎቹን ግን ማግኘት ባለመቻላቸው ኢያሶንና ጥቂት በቅርቡ ያመኑ ሰዎችን ወደአካባቢው ባለስልጣናት ፊት አቅርበው የፖለቲካ አመጽ ያስነሱ ሰዎችን አስጠልለዋል በሚል ሰበብ አቆሟቸው፡፡

ሐዋ. ሥራ 17፡10-15ን ያንብቡ፡፡ በቤሪያ የሚገኙ አይሁዶች በተሰሎንቄ ከሚገኙት ይልቅ በተቃራኒው ምን አይነት ምላሽ ሰጡ?

---

---

ኢዮጂንስ 'eugenēs' 'የሚለው ቃል (ሐዋ. 17፡11) ስርወቃሉ «በመልካም ሁኔታ መወለድ» ወይም «የመሳፍንት ውልደት» ማለት ሲሆን ነገር ግን በዚህ ስፍራ የሚያመላክተን «ተገቢ የሆነ አስተሳሰብ» ወይም አመለካከት ያላቸው እንደሆነ ነው፡፡ በቤሪያ ያሉ አይሁዳውያን የሚመስገኑት ከጳውሎስና ሲላስ ጋር በመስማማታቸው ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በራሳቸው ፍላጎት በየቀኑ መጽሐፍትን በመመርመር ሚሽነሪዎቹ ትክክል መሆን አለመሆናቸውን ለማወቅ በመጣራቸው ነው፡፡ ለወንጌል ያለን ጉጉት በእውቀት ላይ ካልታነፀ እምነታችን ጥራዝ ነጠቅና ረጅም እድሜ የሌለው ይሆናል፡፡ ብዙም ሳይቆይ ግን በቤሪያ ስደት ስለተነሳ በጳውሎስ የወንጌል አገልግሎት ፍሬያማነት ላይ እክል ገጠመው፡፡ በዚህም የተነሳ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ወደ አቴና መሄድ ግድ አለው፡፡

እርስዎ አንዳንድ ነገሮች እንደተባሉት መሆናቸውን ለማረጋገጥ መጽሐፍ ቅዱስዎን በትጋት የመረመሩበት ቅርብ ጊዜ መቼ ነበር?

**ረቡዕ ነሐሴ 23**

## ጳውሎስ በአቴና

የጥንታዊቷ ግሪክ የጥበብ ማዕከል የነበረችው አቴና በጣኦታት የተሞላች ነበረች፡፡ በሁሉም ቦታ በተለይም የከተማ ህይወት ማዕከል በነበረው በአጎራ መግቢያ(የህዝብ አደባባይ) በእብነበረድ የተሠሩ ሀውልቶችና ጣዖታት ነበሩ፡፡ ጳውሎስ በበዛው የጣዖት አምልኮ ስለተረበሸ ሁሌ እንደሚያደርገው ቀድሞ ወደ አይሁድ ምኩራብ መሄዱን ትቶ ሁለት ተግባራትን በተመሳሳይ ወቅት ማከናወን ፈለገ፤ በየሳምንቱ ከአይሁዳውያንና እግዚአብሔርን ከሚፈሩ አህዛብ ጋር ሲያሳልፍ በየቀኑ ደግሞ በህዝብ አደባባይ ከግሪካውያን ጋር ይወያይ ነበር (ሐዋ. ሥራ 17፡15-22)፡፡

የአቴና ሰዎች አዲስን ነገር ለመስማት ሁልጊዜ ዝግጁዎች ስለነበሩ አንዳንድ ፈላስፎች ለጳውሎስ ትምህርት ፍላጎት አሳይተው አርዮስፋጎስ ወደተባለ የከተማዋ ከፍተኛ የመማክርት ጉባኤ ጋበዙት፡፡ ጳውሎስ ንግግሩን ሲያደርግ ከአይሁድ ጋር እንደሚያደርገው ከመፅሐፍ ቅዱስ ወይም ከእስራኤል ታሪክ አልጠቀሰም(ከሐዋ. 13፡16-41 ጋር ያነፃፅሩ)፡፡ እንደዚያ አይነት አቀራረብ ለዚህኛው ጉባኤ ጥቅም

አይኖረውም፡፡ በምትኩ እነዚያ አረማውያን ሊያስተውሉት በሚችሉት መልኩ ወሳኝ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን ገለፀላቸው፡፡

ሐዋ. ሥራ 17፡22-31ን ያንብቡ፡፡ በአርዮስፋጎስ ባደረገው ንግግር ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ መዳን፣ ስለ ታሪክና ስለ ሰብዓዊ ዘር ምን አይነት ታላላቅ እውነቶችን ሰበከ?

---

---

አብዛኛዎቹ የጳውሎስ ቃላት ስለ ሐይማኖትና ስለ እግዚአብሔር የተዛባ አመለካከት ለነበራቸው አረማውያን አድማጮቹ የሚያስቁ ነበሩ፡፡ እግዚአብሔር በዓለም ላይ ስለሚፈርደው ፍርድ ሲናገር(ሐዋ. ሥራ 17፡31) ወዲያው ያቋረጡት ስለሚመስል መልዕክቱን እንዴት ሊደመድም እንዳሰበ አናውቅም፡፡ ይህ ትምህርቱ ከቀጣዮቹ የግሪክ አስተምህሮዎች ማለትም 1. እግዚአብሔር እጅግ ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ በምድር ላይ ባሉ ጉዳዮች ለየትኞቹም ግድ አይለውም ጣልቃም አይገባም እና 2. ሰው ከሞተ አይነሳም ከሚሉት ጋር የሚጋጭ ነበር፡፡ ይህ ወንጌል ለግሪካውያኑ ሞኝነት(1 ቆሮ. 1፡ 23) የሆነበትንና በአቴና የአማኞች ቁጥር ያነሰበትን ምክንያት ይገልፃል፡፡

ሆኖም አማኝ ከሆኑት መካከል የአርዮስፋጎስ ምክር ቤት አባል የነበሩና በአቴናውያን ማህበረሰብ ውስጥ እጅግ ተፅዕኖ ያሳድሩ የነበሩ እንደ ዲዮናስዮስ ያሉ ሰዎች ነበሩ፡ ፡ በተጨማሪም ስሟ በመጠቀሱ የምክር ቤቱ አባል ባትሆን እንኳን ከፍ ያለ ቦታ የነበራት ደማሪስም ከአማኞቹ መካከል ነበረች(ሐዋ. ሥራ 17፡34)፡፡

ጳውሎስ በአርዮስፋጎስ ያቀረበበት ለየት ያለ አቀራረብ ስለ ማህበራዊና ባህላዊ ልዩነቶች ግንዛቤ እንደነበረው ያሳያል፡፡ እንደውም መልዕክቱን ግልፅ ለማድረግ ከአረማዊ ግጥም ስንኞችን ጠቅሷል(ሐዋ. ሥራ 17፡28)፡፡ ይህ የተለያዩ ሰዎችን ለመድረስ የተለያዩ መንገዶችን እንዴት መጠቀም እንዳለብን ምን ይነግረናል?

## ሐሙስ ነሐሴ 24

### ጳውሎስ በቆሮንቶስ

በሐዋ. ሥራ 18፡1-11 ላይ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ስላጋጠመው ነገርና በዚያም አንድ ዓመት ተኩል ስለመቀመጡ ይነግረናል፡፡ አቂላና ጵርስቅላ የጳውሎስ የዕድሜ ዘመን ወዳጆቹ ይሆናሉ(ሮሜ 16፡3፤ 2 ጢሞ. 4፡19)፡፡ ከታሪኩ እንደምንረዳው ምናልባትም በንጉስ ክላውዲየስ አማካኝነት ከይሁዳውያን ከሮም ተባረው ወደ ቆሮንቶስ ከመምጣታቸው በፊትም ክርስትያኖች ነበሩ፡፡

ሮማዊው የታሪክ ፀሐፊ ሱቶኒዮስ እንደጠቀሰው ለቀው እንዲወጡ የተደረገበት ምክንያት በአካባቢው ያሉ የአይሁድ አማኞች ወንጌልን በመስበካቸው «ክርስቶስ» በሚለው ስም አማካኝነት በአይሁድ ማህበረሰብ መካከል ግጭት ስለተነሳ (Claudius 25.4) ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ አቂላና ጵርስቅላም በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ ሆነው ይሆናል፡፡ ያም ሆነ ይህ ጳውሎስና አዳዲስ ወዳጆቹ ተመሳሳይ እምነትና አይሁዳዊ መሰረትን ከመጋራት ባለፈ ተመሳሳይ መተዳደሪያንም ይጋራሉ፡፡

ሐዋ.18፡4-17ን ያንብቡ፡፡ የጳውሎስ የሚሲዮናዊ እንቅስቃሴ በቆሮንቶስ ምን ውጤትን አመጣ?

---

---

ሲላስና ጢሞቴዎስ መቄዶንያ እንደደረሱ በዛ ከምትገኘዋ ቤተክርስቲያን የገንዘብ ድጋፍ ይዘው ነበር የመጡት(2ኛቆሮ.11፡8-9)፡፡ ይህም ጳውሎስ ሙሉ በሙሉ በስብከቱ ብቻ እንዲጠመድ አደረገው፡፡ «ወንጌልን የሚሰብኩ ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ከወንጌል እንዲቀበሉ» (1 ቆሮ.9፡14) ቢያስተምርም የጳውሎስ(የራሱ) መመሪያ ግን ለወንጌል አገልግሎት የሚያወጣውን ወጪ በሙሉ በራሱ መሸፈን ነበር፡፡

ምንም እንኳን የጳውሎስን መልእክት አይሁዶች በብርቱ ቢቃወሙም አንዳንድ አይሁዳውያንና አህዛብ ግን አምነው ነበር፡፡ አምነው ከተለወጡት መካከል የምኩራብ አለቃ የነበረው ቀርስጶስ ከመላ ቤተሰቡ ጋር ይገኝበታል፡፡ አያሌ የቆሮንቶስ ሰዎች አምነው ተጠምቀዋል፡፡ የሚቀጥለው ክፍል የሚነግረን ግን በአይሁዶች በኩል ያለው ሁኔታ የበለጠ እየከረረ መሄዱን ነው (ሐዋ.18፡12-17)፡፡ ጳውሎስም በቶሎ ቆሮንቶስን ለቆ ለመሄድ አስቦ ነገር ግን በሌሊት ራዕይ በዚያ ስፍራ እንዲቆይ የመለኮት ማበረታቻን አገኘ (ሐዋ.18፡9-11)፡፡

ወደ አንጾኪያ በሚመለስበት ጊዜ ጳውሎስ አቂላና ጵርስቅላን ወስዶ ጉዞውን ከመቀጠሉ በፊት ጥቂት ቀናት በቆየበት በኤፌሶን ተዋቸው፡፡ በዛ ቆይታውም በአካባቢው ባለው ምኩራብ ውስጥ የመስበክን እድል አገኘ፡፡ የሰዎቹን መልካም የሆነ ምላሽ እግዚአብሔር ከፈቀደ ዳግም ተመልሶ እንደሚመጣ ቃል እንዲገባ አስገደደው (ሐዋ.18፡18-21)፡፡ ይህ የሆነው በቀጣይ ጉዞው ውስጥ ነበር፡፡

ጥሩ ምላሽ ባለማግኘቱ ተስፋ የቆረጠው ጳውሎስ በዛ ስላሉት የነፍሳት መዳን ሁኔታ ከጌታ ማበረታቻን ማግኘት አስፈለገው፡፡ የጌታ ቃል ምን ነበር ያለው (ሐዋ.18፡10)? ከጳውሎስ ጋር ተመሳሳይ ነገር ሲገጥመን ጌታ እኛን ምን ይለናል?

## ዓርብ | ነሐሴ 25

**ተጨማሪ ጥናት፡-**”ዛሬ ገናና ያልሆነውን እውነት የሚያስተምሩ የሚቀበላቸው ሰው ባለመግኘታቸው፣ ክርስትያን ነን የሚሉ ሰዎች ሳይቀር ባይቀበሏቸው ተስፋ ሊቆርጡ አይገባም። ጳውሎስና የስራ አጋሮቹ በሚያገለግሏቸው ሰዎች መሃል ሆነው ከዚህ በላይ ደርሶባቸዋልና፡፡ የመስቀሉ መልእክተኞች ነቅቶ በመፀለይ፣ በእምነትና በድፍረት ወደፊት በመንቀሳቀስ በየሱስ ስም ሁልጊዜ ለመስራት መታጠቅ አለባቸው።“ Ellen G. White, The Acts of the Apostles, P.230

“በምድር ታሪክ ማጠቃለያ ላይ እውነቱ የሚሰበክላቸው የቤርያን ሰዎች ፈለግ በመከተል ቃሉን በየቀኑ የሚመረምሩና እና የእግዚብሔርን ቃል ከቀረበላቸው መልእክት ጋር የሚያነፃፅሩቢሆኑ ኖሮ በንጽጽር አሁን ካሉት ጥቂት የእግዚአብሔር ህግ ታማኞች ይልቅ ብዙዎች ይገኙ ነበር፡፡”

“ሁሉም የሚፈረድባቸው በተቀበሉት ብርሃን ልክ ነው፡፡ ጌታ አምባሳደሮቹን የድነት መልእክቱን አስታጥቆ ልኳቸዋል፤ የሚሰሙትም የአገልጋዮቹን ቃል በተቀበሉበት ልክ ሃላፊነቱን ይወስዳሉ፡፡ በቅንነት እውነትን የሚሹ ሁሉ የቀረበላቸውን አስተምህሮ በተገለጠላቸው የእግዚአብሔር ቃል ብርሀን በጥንቃቄ ሊመረምሩ ይገባቸዋል፡፡” Page 232

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በሰኞ ጥናታችን የመጨረሻው አንቀጽ ባጠናነው አውድ መሰረት የሚከተለው አባባል የሚያመላክተውን ነገር እስቲ በክፍሎቻችሁ ውስጥ ተወያዩ፡፡ “ለጥምቀት የሚዘጋጁ እጩዎች ከልብ የሆነ ዝግጅት ማድረግ አለባቸው... የክርስትያን ህይወት መርህ ወደ እውነቱ በቅርቡ ለተቀላቀሉ ሰዎች ግልጽ መሆን ይገባዋል፡፡” Ellen G. White, Testimonies for the Church, vol. 6, pp. 91, 92::

2. በረቡዕ የመጨረሻ ጥያቄ ላይ ትኩረትዎን ያድርጉ፡፡ ልክ ጳውሎስ የባህል ልዩነቶችንእንዳስተዋለውእኛምእንደቤተክርስቲያንልዩነታችንንአስተውለን ወንጌሉንና የሃይማኖት አቋማችንን ድርድር ውስጥ ሳናስገባሰዎችን ባሉበት ስፍራ መድረስ የሚቻለን እንዴት ነው?

3. ሐዋ. 17፡32-34ን ያንብቡ። ጳውሎስ በአቴና ላቀረበው መልእክት ከተሰጡት ሶስት ምላሾች ምን እንማራለን?“1) አንዳንዶቹ አሾፉበት፡፡ እንግዳ በሆነውና የተነቃቃ ስሜት በነበረው አይሁድ ተዝናኑ፡፡ በህይወት ላይ ማፌዝ ይቻላል፤ ነገር ግን ይህን በሚያደርጉ ሰዎች በቀልድ የተጀመረው ነገር በሀዘን ይጠናቀቃል፡፡ 2) አንዳንዶች መወሰን አልፈለጉም፡፡ ከሁሉም አደገኛው ቀን አንድ ሰው ስለነገ ማውራት ምን ያህል ቀላል እንደሆነ የሚያስተውልበት ዕለት ነው ፡፡ 3) አንዳንዶች አመኑ። ጠቢብ የሆኑ ሰዎች ሞኞች ብቻ የእግዚአብሔርን ስጦታ እንቢ እንደሚሉ ያውቃሉ፡፡”William Barclay, The Acts of the Apostles, rev. ed. (Philadelphia: Westminster, 1976), p. 133

4. ጳውሎስ ለአቴናውያን መልእክቱን ለማጉላት ከአረማዊ ፀሐፊ ጠቅሶ (ሐዋ.17፡28) ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ እንደዚህ ያሉ ምንጮችን መጥቀስ ያለውን ጥቅም እድንማር ይህ እንዴት ያግዘናል? ይህን ማድረጉ ምን አይነት አደጋስ ሊኖረው ይችላል?

# 10ኛ ትምህርት ከነሐሴ 26 - ጳጉሜ 2

## ሦስተኛው ሚስዮናዊ ጉዞ

ሰንበት ከስዓት

*ለዚህ ሳምንት ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ የሐዋ. ሥራ 18፡24-28፤ ሐዋ. ሥራ 19፤የሐዋ. 20፡ 7-12፣15-27፤ 2 ቆሮ. 4፡8-14፤ የሐዋ. ሥራ 21፡1-15፡፡*

**<u>መታሰቢያ ጥቅስ</u> ፡-"ይሁን እንጂ ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን ሩጫዬንና የእግዚአብሔርን የጸጋ ወንጌል የመመስከር አገልግሎቴን ብፈጽም፣ ለእኔ ሕይወቴ ከምንም እንደማይቈጠር እንደ ከንቱ ነገር ናት።"**

(የሐዋ. ሥራ 20፡ 24)

ሉቃስ የጳውሎስን ሦስተኛ ጉዞ እንደ ጻፈው ጉዞው የቀጠለው ሁለተኛውን ጉዞ ወዲያውኑ ተከትሎ ነበር፡፡ ጽሑፉ እንደሚለው የጳውሎስ የአገልግሎት ማዕከል በሆነችው በአንጾኪያ የተወሰነ ጊዜ ካሳለፈ በኋላ ሐዋሪያው ሌላ ጉዞ አድርጓል። አከታትሎ "በገላትያናበፍርግያአገሮችከቦታቦታበመዘዋወርደቀመዛሙርትንሁሉአበረታታ"ሐዋ. 18፡23፡፡በመሆኑም የመጀመሪያዎቹ 2414 ኪሎ ሜትሮች(1,500 ማይሎች) ጉዞ የተጠቃለለው በአንድ አረፍተ ነገር ነው።

ይህም የሆነበት ምክንያት የጉዞው መዳረሻ ኤፌሶን ስለነበረች ነው፤ ጳውሎስ በጉዞው ላይ በሌሎች ከተሞች ሲያልፍ ከነበረው የቆይታ ጊዜ ይልቅ በዚህች ከተማ ረዘም ያለ ጊዜ አሳልፏል፡፡ ከወንጌል አገልግሎት አንጻር በኤፌሶን የነበረው አገልገሎት ፍሬያማ ነበር፤የጳውሎስም የስብከት ተፅዕኖ በእስያ አውራጃዎች ሁሉ ላይ ተዳርሶ ነበር(የሐዋ. ሥራ 19፡10፣26)፡፡ ምናልባትም የቆላስያስ፣የኢያራ እና የሎዶቅያ አብያተ ክርስቲያናት ምናልባትም በኤጳፍራ አማካኝነት የተመሰረቱት በዚህ ወቅት ሳይሆን አይቀርም(ቆላ. 4፡12፣13)፡፡ ይህም ሰው ከጳውሎስ ጋር ከሰሩት ሰዎች መካከል አንዱ ነው(ቆላ. 1፡7፤ ፊሊሞ. 23)፡፡

ስለዚህ ጉዞ የሚያስገርመው ነገር በሐዋርያት ሥራ ከተመዘገቡት የጳውሎስ ጉዞዎች የመጨረሻ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ጳውሎስ ነጻ ሰው ሆኖ ከተጓዛቸው ጉዞዎች ማለታችን እንጂ ከዚህ ጉዞ በኋላም ሉቃስ እራሱ ወደ ሮም ያደረገውን ጉዞ መዝግቦት እናገኛለን፤ ነገር ግን ያን ጉዞ ያደረገው እንደ እስረኛ ነበር፡፡

*የዚህን ሳምንት ትምህርት በማጥናት ለጳጉሜ 3 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡

**እሑድ ነሐሴ 27**

## ኤፌሶን፡ ክፍል አንድ

በሐዋርያት *ሥራ* 18፡24-28 እንደ ተመዘገበው ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን በጉዞ ላይ እያለ አጵሎስ የተባለ አይሁዳዊ ወደ ኤፌሶን መጣ፡፡ ይህም ሰው አንደበተ ርቱዕና የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ያስተዋለ ሰው ነበር፡፡ ሉቃስ እርሱን የገለጸበት መንገድ በትክክልም አጵሎስ የኢየሱስ ተከታይ እንደ ነበር ያስረዳል።"ይህሰው፣የጌታንመንገድየተማረ፣ስለኢየሱስምበትክክልየሚናገርናበመንፈስእየተቃጠለ የሚያስተምርነበር፡፡" (የሐዋ. *ሥራ* 18፡25)፡፡ነገር ግን እርሱ ያውቅ የነበረው የዮሐንስን ጥምቀት ብቻ ነበር፡፡ አጵሎስ በዮሐንስ መጥመቁ ከተጠመቀ በኋላ ኢየሱስ ከነበረው ምድራዊ የአገልግሎት ሕይወት ጋር የሚተዋወቅ ሲሆን፤ ነገር ግን በዚያ አካባቢ ብዙም ሳይቆይ እርቆ ሳይሄድ አልቀረም፤ምን አልባትም ከሕማማቱ/ከበዓለ ሃምሳ ትዕይንቶች/ በፊት ወደ አሌክሳንድሪያ ተመልሶ ሊሆን ይችላል፡፡

ለዚህም ነበር አቂላና ጵርስቅላ ተጨማሪ ግንዛቤን ሲሰጡት የነበረው፡፡ እናም ከቅዱሳት መጽሐፍት ኢየሱስ እርሱ የእስራኤል መሲህ እንደነበር አሳዩት (ሐዋ 18፡28)፤አጵሎስ ከክርስቶስ ኢየሱስ አገልገሎት ጀምሮ የነበረውን ተጨማሪ የክርስትና እድገት መስማት ነበረበት፡፡ ሆኖም ግን አቂላና ጵርስቅላ ለአጵሎስ ከዚህ የሚበልጥም ነገር ነው ያደረጉለት፤ በኤፌሶን ከሚገኙ ሌሎች አማኞች ጋር በመሆን በአካያ ወደሚገኙ አብያተ ክርስትያናት የድጋፍ ደብዳቤ አስይዘው በመላክ (ሐዋ. 18፡27) በቆሮንቶስ ውጤታማ አገልግሎት እንዲኖረው አድርገዋል (1 ቆሮ. 3፡4-6፤ 4፡6፤ 16፡12)፡፡

የሐዋ. 19፡1-7 ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ ኤፌሶን በደረሰ ጊዜ ያጋጠመው ምን ነበር?

---

---

የአጵሎስ ታሪክ ጳውሎስ ኤፌሶን በደረሰ ጊዜ ካገኛቸው አስራ ሁለት ሰዎች ጋር ተያያዥነት ያለው ነው፤ ምክንያቱም ሁኔታቸው ተመሳሳይ ነበረ፡፡ ሰዎቹ የተሰጣቸው መገለጫ "ደቀመዛሙርት" (የሐዋ. 19፡1) የሚል ሲሆን ጳውሎስም ለእነርሱ ያቀረበው ጥያቄም (የሐዋ. 19፡2) በግልጽ የሚያሳየው በኢየሱስ ያመኑ ሰዎች እንደነበሩ ነው፡፡

በተመሳሳይም ለጳውሎስ የሰጡት መልስ የሚያሳየው እንደ አጵሎስ ሁሉ በመጀመሪያ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀመዛሙርት የነበሩና የበዓለ ሃምሳው ልምምድ የሌላቸው የኢየሱስ ተከታዮች መሆናቸውን ነው፡፡ ከጌታ ጋር በሚኖረው የጠለቀ ትስስር የሚገኘውን ደስታ የማግኘት እድል ሊኖራቸው የተገባ ሰዎች ነበሩ፡፡

“ጳውሎስ ኤፌሶን በደረሰ ጊዜ አስራ ሁለት የሚሆኑ ወንድሞችን አገኘ፤ ልክ እንደ አጵሎስ ሁሉ እነርሱም የመጥመቁ ዮሐንስ ደቀመዛሙርት የነበሩ እና እንደ እርሱ ሁሉ ስለ ክርስቶስ ተልዕኮ የተወሰነ ግንዛቤ ነበራቸው፡፡ የአጵሎስ አይነት ችሎታ ባይኖራቸውም በተመሳሳይ ቅንነትና ታማኝነት የተቀበሉትን እውነት ለሌላው ለማድረስ የሚወዱ ሰዎች ነበሩ፡፡” —Ellen G. White, The Acts of the Apostles, p. 282.

እንደአዲስ መጠመቃቸውን ማየት ያለብን ሁኔታው ልዩ ከመሆኑ አንፃር ሊሆን ይገባል፡፡ እነዚህ ሰዎች ከሌላ የክርስትና ቤተ እምነት አልመጡም፤ወይም የነበራቸውን የሕይወት ልምምድ የቀየሩም አይደሉም፤ ነገር ግን እራሳቸውን ከዋናው የክርስትና ልምምድ ጋር እያዋሃዱ ነበር፡፡ እናም መንፈስ ቅዱስን በመቀበል በሌሎች ቋንቋዎች(ልሳኖች) መናገር ጀመሩ። ይህም ማለት ምናልባትም ክርስትያን ሚስዮናውያንሳይሆኑ አይቀሩም፤ እንደ አጵሎስ ሁሉ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ በሚወጡበት ሁሉ ለመመስከር የሚያስችላቸውን ሃይል በሙላት አግኝተዋል፡፡

| ሰኞ | ነሐሴ 28 |
|---|---|

## ኤፌሶን፡ ክፍል ሁለት

በኤፌሶን፤ ጳውሎስ በመጀመሪያ የሰበከው በምኩራብ ውስጥ ነበር፡፡ ተቃውሞ በተነሳ ጊዜ ግን እርሱና አዲስ አማኞቹ በጢራኖስ ወደሚገኘው የትምህርት መስጫ አዳራሽ መሰብሰቢያቸውን ቀየሩ። በእዚያም ጳውሎስ ለሁለት አመታት በየእለቱ ቃሉን ይናገር ነበር (የሐዋ. ሥራ 19፡8-10)፡፡የሉቃስ ማጠቃለያ በኤፌሶን የነበረውን የጳውሎስ አገልግሎት የሚያስቀምጠው በሁሉም አውራጃዎች (ግዛቶች) ወንጌል በስፋት ተዳርሶ እንደነበር ነው (የሐዋ. ሥራ 19፡10፣26)፡፡

የሐዋርያት ሥራ 19፡11-20 ላይ አስማትና ሌሎች የአጉል ልማድ እምነቶች የተለመዱ በሆኑበት ከተማ ውስጥ የእግዚአብሔርን ሃይል አሸናፊነት የሚያሳዩና ተአምራትን የያዙ ታሪኮችን ሉቃስ በጽሁፉ ውስጥ አካቷል፡፡

ጥያቄ ውስጥ የማይገባው ነገር እግዚአብሔር ጳውሎስን በመጠቀም መፈወሱ ሲሆን በሐዋሪያው የተነኩ መሀረቦችና ሽርጦች ሳይቀሩ የመፈወስ ኃይል ነበራቸው(የሐዋ. 19፡12)። ይህ ለአንዳንዶች እንግዳ ነገር ሊመስል ይችላል፤ ፈውሱ ግን ኢየሱስ ደም ሲፈሳት የነበረቻውን ሴት ከፈወሰበት ፈውስ ጋር ተመሳሳይነት አለው (ሉቃ 8፡44)፡ ፡ የኤፌሶን ሰዎች የልማድ እምነቶች እግዚአብሔር "ለየት ያለ" ተዓምርን እንዲፈጽም ምክንያት ሆነዋል ይላል ሉቃስ (ሐዋ. 19፡11)፡፡ ይህም እግዚአብሔር የሰዎችን ፍላጎት በማስተዋላቸው ልክ (ደረጃ) እንደሚያሟላ ምሳሌ ይሰጠናል፡፡

በኤፌሶን በነበረው የተልዕኮ ውጤታማነት የረካው ጳውሎስ ወደ እየሩሳሌም ለመሔድ ወሰነ፡፡ ሉቃስ ለዚህ ጉዞ ምክንያትን አልሰጠም፤ነገር ግን ከራሱ ከጳውሎስ ጽሁፎች እንደምንረዳው በእየሩሳሌም በምትገኘው ቤተክርስቲያን ላይ የተፈጠረውን ድህነት በተወሰነ መልኩ ለመቅረፍ የሰበሰበውን እርዳታ ለማድረስ ምኞቱ እንደ ነበር ነው (ሮሜ 15፡25-27፣ 1 ቆሮ. 16፡1-3)፡፡ በመጀመሪያዎቹ ዓመታትየሽቀጦች መሰብሰብና እና በቀላውዲዎስ ዘመን የተነሳው አስከፊ ረሃብ የአይሁድ አማኞችን አደህይቶ ነበር። እናም ጳውሎስም ለእርዳታ ያቀረቡትን ተማጽኖ ሲያይ(ገላ. 2፡ 10) ምንም እንኳን ወደ እየሩሳሌም በመውጣቱ የሚገጥመውን ችግር ቢያውቅም አጋጣሚውን በሐዋሪያነቱ ላይ ያላቸውን አመኔታና የተለያየ የባሕል ስብጥር ያላትን ቤተክርስትያን ህብረት ለማጠናከር ለመጠቀም አሰበ (የሐዋ. 20፡22፣23፤ ሮሜ 15፡ 31)፡፡

ሐዋ. ሥራ 19፡23-41ን ያንብቡ፡፡ በኤፌሶን ቆይታው መጨረሻ አካባቢ በጳውሎስ ላይ ተነስቶ የነበረው ተቃውሞ ትክክለኛ ምክንያት ምን ነበር?

---

---

ተቃውሞው ከአረማውያን አምልኮ ጋር የተያያዘ ሲሆን ይህም በጳውሎስ አገልግሎት ምክንያት አምልኮው የከፋ ኪሳራ ገጥሞት ስለነበር ነው፡፡ የዲሜጥሮስ ትክክለኛ እሳቤ ከገንዘብ ጋር የተቆራኘ ቢሆንም ነገሩን ወደ ሃይማኖታዊ ጉዳይ ቀይሮት ነበር፤ ምክንያቱም አርጤምስ (ዲያና) ቤተመቅድስ ይገኝ የነበረው በኤፌሶን ስለነበር ነው። ይህም ቤተመቅድስ ጥንታዊ ሆነው አስደናቂ ታሪክ ካለቸው ሰባቱ ቅርሶች አንዱ ሆኖ ተመዘገቧል፡፡

ሐዋ. ሥራ 19፡27ን ያንብቡ፡፡ ዲሚጥሮስ የገንዘብ ምንጩ እንዳይቋረጥ ጥበብ በተሞላበት መልኩ ሃይማኖታዊ ተቆርቋሪነትን እንዴት እንዳነሳሳ ይመልከቱ፡ ፡ እኛም እንደ ክርስትያን እምነታችንን ወይም ለእምነታችን ተቆርቋሪ በመምሰል በተመሳሳይ መልኩላለመጠቀም ልንጠነቀቅ የሚገባን ለምንድን ነው?

## ማክሰኞ ነሐሴ 29

# ጢሮአዳ

ከሁከቱ በኋላ (ሐዋ. ሥራ 19፡23-41) ጳውሎስ ኤፌሶንን ለቆ ለመውጣት ወሰነ፡፡ ነገር ግን ወደ ኢየሩሳሌም የሚወስደውን ቀጥተኛ መንገድ አልነበረም የተጠቀመው፡፡ ቀጥተኛውን መንገድ ትቶ በመቄዶንያና በአካይ በኩል አለፈ(የሐዋ. 20፡1-3)፡፡ በጉዞም ላይ የአህዛብ ቤተክርስቲያናትን የሚወክሉ የተወሰኑ ሰዎች አብረውት ነበሩ (የሐዋ. 20፡4)፡፡

ሐዋ. 20፡1-7 ያንብቡ፡፡ እነዚህ ጥቅሶች የሰንበት ቀን ወደ እሁድ እንደተለወጠእንደ ማረጋገጫነት ይቀርባሉ። የዚህ ሃሳብ ስህተቱ ምንድን ነው?

________________________________________________

________________________________________________

ጳውሎስ ጉዞውን ገታ በማድረግ በጢሮአዳ ቆይታ አደረገ። ይህም ቆይታው የተጠናቀቀው "በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን"(የሐዋ. 20፡7) በቤተክርስቲያን ስብሰባ ነበር፡፡ በህብረት የነበሩት "እንጀራን ለመቁረስ" ነበር። ምናልባትም የጌታ እራት ሊሆን ይችላል፡፡ በቀደመው ጊዜ ከነበረች የእየሩሳሌም ቤተክርስትያን ጀምሮ ማዕድን አብሮ የመቁረስ ጊዜ የጌታ እራትን ተከትሎ ይከናወን ነበር (ሐዋ. 2፡42፤46)። በዚህ ጊዜ ግን በህብረት መመገቡ አብሮ ተከናውኖ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡ በዚህ ስፍራ ስለ ጽዋ ወይም ስለጸሎት አለመጠቀሱ ግምቱን ዋጋቢስ አያደርገውም፡፡ ዋናው ሃሳብ ግን ይህ ክፍል ብዙ ጊዜ በጳውሎስ ዘመን የነበሩ ቢያንስ ደግሞ የአህዛብ አብያተ ክርሰትያናት ሰንበትን በእሁድ የአምልኮ ቀን ተክተውት ነበር ለማለት በማስረጃነት ይቀርባል፡፡

ነገር ግን እንዲህ ብለን ከመደምደማችን በፊት ይህ ስብሰባ የተከናወነበትን ትክክለኛ ቀን እንዲሁም የስብሰባውን አይነት ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ የጳውሎስ መልዕክት እስከ እኩለ ሌሊት ከመቀጠሉ ጋር ተያይዞ፤ መብራቶችን እንደተጠቀሙ መገለጹ (ሐዋ. 20፡7-8) ደግሞም እስከ ንጋትም የቀጠለ መሆኑን እንጂ (የሐዋ. 20፡11) የአውጤኪስን ከባድ እንቅልፍም መጥቀስ አስፈላጊ ባልሆነ ነበር (ሐዋ. 20፡9)። ይህም የምሽት ስብሰባ መሆኑን ያረጋግጥልናል፡፡

ጥያቄው ከእሁድ ማለዳ በፊት የነበረው ምሽት ነው ወይስ ከእሁድ በኋላ የነበረው ምሽት የሚለው ነው። መልሱ የሚወሰነው ሉቃስ በተጠቀመው የጊዜ አቆጣጠር ዘዴ ይሆናል፤ ይህም የአይሁድን የጊዜ አቆጣጠር ተጠቅሞ ከሆነ ከፀሐይ ግባት እስከ ፀሐይ ግባት ወይም የሮማውያን የጊዜ አቆጣጠር ከሆነ ደግሞ ከእኩለ ሌሊት እስከ እኩለ ሌሊት ይሆናል። የቀደመውን የጊዜ አቆጣጠር ተጠቅሞ ከሆነ ቀኑ ቅዳሜ ምሽት ነበር፤ የኋለኛውን ተጠቅሞ ከሆነ ቀኑ እሁድ ምሽት ነበር።

በሁለቱም መንገድ የሐዋሪያት ሥራ 20፡7-12 አውድ የሚነግረን፤ ስብሰባው እሁድ ምሽት ተከናውኖ ከነበር እንኳን ስብሰባው መደበኛ የቤተክርስትያን ጉባኤ እንዳልነበረ ነው። ነገር ግን ጳውሎስ በሚቀጥለው ማለዳ ጉዞ ለማድረግ በማሰቡ የተደረገ ልዩ ስብስባ ነበር። እናም ይህ የተለየና የማይገናኝ ክፍል እሁድን ለመጠበቅ እንደ ድጋፍ ማረጋገጫ ተደርጎ ሊቀርብ መቻሉ በራሱ የሚከብድ ነው። እውነታው ደግሞ አለመሆኑ ነው።

ሰባተኛውን ቀን ሰንበትን መጠበቅ ትክክል እንደሆነ የሚያስረዱ ምክንያቶች ላይ ቆይታ ያድረጉ። እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ክርስትያንነታችንና የሦስቱን መላእክት መልዕክት ለዓለም ለማድረስ ከተሰጠን ጥሪ አንጻር ስለ ስንበት የተሰጡ ጠንካራ የመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፎች (ማረጋገጫዎች) ስለ ማንነታችን ምን ያህል ያስገነዝቡናል?

**ረቡዕ** **ነሐሴ 30**

## ሚሊጢን

ጳውሎስ ወደ እየሩሳሌም በጉዞ ላይ እያለ በሚሊጢን ሌላ ቆይታ አድርጎ ነበር። በዚህ ቆይታው ነበር ከኤፌሶን ለመጡ የቤተክሰርስቲያን መሪዎች የስንብት ንግግር የማድረግን እድል ያገኘው።

ሐዋርያት ሥራ 20፡15-27 ያንብቡ። ጳውሎስ በንግግሩ መግቢያ ላይ አፅንእት የሰጠው ምን ነበር?

________________________________________

________________________________________

ሮምና እስፔንን የሚያጠቃልል ሌላ ጉዞ እቅዱ ውስጥ ስለነበር (ሮሜ 15፡22-29) ጳውሎስ ከዚህ በኋላ ወደ እስያ እንደማይመለስ ተረድቷል። እናም ንግግሩን በመቀጠል በኤፌሶን ባሳለፋቸው አመታት የነበረውን ቆይታ በዝርዝር አቀረበ።

የዚህ አይነቱ ገለጻ ዋና አላማው ስላለፈው ማውሳት ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ከፊቱ ባለው ጊዜ በእየሩሳሌም ምን እንደሚያጋጥመው ስለሚያስፈራው ነበር፡፡

የጳውሎስ ፍርሃት ያለምክንያት አልነበረም፡፡ በኢየሩሳሌም የሚገኙ አማኞች በጠላትነት ሳይሆን ባለፈው የአሳድጅነት ሕይወቱና ከግዝረት ነጻ በሆነው የወንጌል ስበከቱ ምክንያት እርሱን የሚያዩት በጥረጣሬ ነበር (ሐዋ. 21፡20-26)፡፡ በአይሁድ መሪዎች ዘንድ ከኃዲና መናፍቅ ነበር (ሐዋ. 23፡1፥2)፡፡ በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ላይ በተለይም ደግሞ የሮም አገዛዝ የተበላሸ በሆነበት ጊዜ ይሁዳም አብዮታዊ እና ብሔራዊ በሆኑ ጉዳዮች ተጨንቃ ነበር፡፡ ይህም ሁኔታ ቤተክርስትያንን ጨምሮ በሁሉም የአይሁድ ማህበረሰብ ላይ ተጽዕኖ ነበረው፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ የቀድሞው ፈሪሳዊ በአህዛብ መካከል ያከናወናቸው ሥራዎቹ እንደ ስም አጉዳፊ እንዲፈረጅ አድርገውታል (ሐዋ 21፡27-36)፡፡

ጳውሎስ ሌላ ተጨማሪ ጭንቀት ነበረበት፡፡ ሐዋርያት ሥራ 20፡28-31 ላይ ጳውሎስ በኤፌሶን የሚገኙ የቤተክርስቲያን መሪዎች የሀሰተኛ መምህራንን ጉዳይ እንዴት መፍታት እንዳባለቸው ትኩረት ሰጥቷል፡፡ እነዚህን ሃሰተኛ መምህራን ጳውሎስ የመስላቸው  በጎችን ከመንገዳቸው ለማሳትና ለማስቀየር እንደሚሞክሩ ነጣቂ ተኩላዎች አድጎር ነበር፡፡ እናም በቀድሞው ዘመን፣ በቤተክርስትያን ውስጥ እንኳን ሳይቀር ሀሰተኛ መምህራን ነበሩ፡፡ ሰሎሞን በራሱ ዘመንና በሌላ አውድ እንደተናገረው “ከፀሐይበታችምንምአዲስነገርየለም።”(መክ1፡9አ.መ.ት)፡፡ የቤተክርስትያን ታሪክ እንደሚገልጽልን ሃሰተኛ መምህራን በቤተክርስትያን ላይ የከፋ ጉዳት አስከትለው እንደነበር ነው፡፡ይህ ችግር ደግሞ እስከ ፍጻሜ ድረስ ይኖራል (2ኛ ጢሞ 4፡3)፡፡

ጳውሎስ በአእምሮው ውስጥ የበዙ ጉዳዮችና ጭንቀቶች እነደነበሩ ምንም ጥያቄ የለውም፤ ቢሆንም ግን የእርሱ ታማኝነትና ትጋት በጭራሽ አልተለወጠም ነበር፡፡

2ኛ ቆሮ. 4፡8-14 ያንብቡ፡፡ በተለይ ፈተና ሲመጣለራሳችን ልንተገብረው ስለሚገባ ነገር ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ምን እያለ ነው? ጳውሎስ የመጨረሻ ተስፋውን ማን ላይ አደረገ?

## ሐሙስ ጳጉሜ 1

### ጢሮስ እና ቂሳሪያ

ከሚሊጢን በኋላ ሉቃስ የጳውሎስን ጉዞ በዝርዝር አስፍሮታል፡፡ ወደ እየሩሳሌም በሚያደርገው ጉዞ ላይ፣መርከቧ ጭነቷን ባራገፈችበት በፊንቄያራውያን የባህር ዳርቻ፣በጢሮስ አንድ ሳምንት አሳለፈ (ሐዋ. 21፡1-6)፡፡ በዚህ ስፍራ እያለ ግን በዚያ የሚኖሩ አማኞች ወደ እየሩሳሌም ሊወጣ እንደማይገባ ሞገቱት። እነዚህ አማኞች በመንፈስ ተመርተው ጳውሎስን ወደ እየሩሳሌም እንዳይሄድ ማሳሰባቸው አስቀድሞ ለሐዋርያው ከተሰጠው ምሪት ጋር በእርግጥም አይጣረስም፡፡ ሐዋርያት ሥራ 19፡21 ላይ ያለው ክፍል ግሪኩ ሲያስቀምጠው etheto en tò pneumati (ኤትዮንቱ ኤነቱ ፒትማነቲ) ይለዋል። ሊተረጎም የሚገባውም “በመንፈስ ወሰነ/አሰበ” (1962 እትም) በሚል እንጂ ጳውሎስ ሁሉን ለማድረግ በራሱ እንደወሰነ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም፡፡ ዋናው ሃሳብ መንፈስ በጢሮስ ለሚገኙ ክርስትያኖች ጳውሎስ ሊገጥመው ስላለው አደጋ ማሳየቱ ሲሆን፤እናም ከዚህ በመነሳት እንደ ሰው በመጨነቅ የጉዞ ዕቅዱን እንዲቀይር ሃሳብን ማቅረባቸው ነው፡፡ ጳውሎስ እራሱ በእየሩሳሌም በእርሱ ላይ ምን ሊሆን እንደሚችል እርግጠኛ አልነበረም (ሐዋ. 20፡22፣23)፡፡ መለኮታዊ ምሪት ሁሉንም ነገር ሁሌ ግልጽ ላያደርግ ይችላል፤እንደ ጳውሎስ ላለ ሰው እንኳን ቢሆን፡፡

ሐዋ. 21፡10-14 ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ ወደ እየሩሳሌም ስለሚያደርገው ጉዞ በቂሳሪያ ምን አይነት ለየት ያለ ክስተትተከናወነ?

---

---

አጋቦስ ከእየሩሳሌም የሆነ ነብይ ሲሆን ስለ እርሱም በሐዋርያት ሥራ 11፡27-30 ስለ ረሀብ በሚናገረው ክፍል ላይ ቀድሞ ተነግሯል፡፡ ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን አንዳንድ ትንቢቶች (ለምሳሌ ኢሳ. 20፡1-6፣ ኤር. 13፡1-10) መልእክቱ ድርጊታዊ ነበር። በጳውሎስ ላይ እየሩሳሌም ሲደርስ ሊሆን ያለውን ስዕላዊ በሆነ መልኩ በግልጽ ያሳየና ጠላቶቹ እንዴት አድርገው ለአህዛብ (ለሮማውያን) አሳልፈው እንደሚሰጡት ያስቀመጠ ነበር፡፡

ከጳውሎስ ጋር የነበሩት ሰዎች የአጋቦስን መልዕክት እንደ ትንቢት ሳይሆን በግልጽ እንደተሰጠ ማስጠንቀቂያ በመውሰድ እና የማሳመኛ መንገዶችን ሁሉ በመጠቀም ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይወጣ በብርቱ ጥረው ነበር፡፡ ጳውሎስም ለእርሱ ያላቸውን አሳቢነት በጥልቀት ያስተዋለ ቢሆንም ተልዕኮውን ለመፈጸም ወስኖ ነበር። ሕይወቱን የሚያስከፍለው ቢሆንም እንኳን፤ ለእርሱ የወንጌል መዳረስና የቤተክርስትያን አንድነት ከራሱ የግል ደህንነት ወይም ፍላጎት ይልቅ ይበልጥ አስፈላጊዎች ነበሩ፡፡

"ሐዋርያው እየሩሳሌምን እንዲህ በሐዘን በተሞላ ልብ ቀርቧት አያውቅም፡ ፡ ጥቂት ወዳጆችና የበዙ ጠላቶች እንደሚገጥሙት ያውቃል፡፡ የእግዚአብሔርን ልጅ ወዳልተቀበለችውና ወደ ገደለችው ደግሞም የመለኮትን ማስጠንቀቂያ ወደ ገፋችውከተማ እየተጠጋ ነበር፡፡"(Ellen G. White, The Acts of the Apostles, pp. 397, 398.)

ጳውሎስን፡- ብዙዎች በተሳሳተ መልኩ ተረድተውታል። ግፍ ተሰርቶበታል፣ ተንገላቷል፣ ነቀፋም ደርሶበታል ነገር ግን በእምነቱ ጸና፡፡ እኛም ተስፋ አስቆራጭ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ማለፍን እንዴት ልንማር እንችላለን?

## ዓርብ | ጳጉሜ 2

**ተጨማሪ ጥናት**:"ወንጌል በመሰበኩ ምክንያት የመጣው ስኬት የአይሁድን ቁጣ እንደ አዲስ ቀስቅሶታል፡፡ አዲሱ አስተምህሮ በሁሉም ሥፍራ መዳረሱ ከየአቅጣጫው እየተሰማ ነው። በዚህም አስተምሮ ነው አይሁድ ይጠብቁት ከነበረው የሜዳዊ ሕግ ስርዓቶች ነጻየሆኑት፤ አህዛብም ከአይሁድ እኩል የአብርሃም ልጅነትን መብት አምነው የተቀበሉት.... እርሱ(ጳውሎስ) እርግጠኛ በሆነ ንግግሩ" ግሪክ ወይም አይሁዳዊ፣የተገረዘ ወይም ያልተገረዘ፣..."(ቆላ. 3፡ 11) በማለቱ ምክንያት ይህ ንግግሩ በጠላቶቹ ዘንድ እንደ የድፍረት ስድብ ተፈርጆ ነበር። እናም ድምጹ ጸጥ ማለት እንዳለበት ወስነው ነበር፡፡"—Ellen G. White, The Acts of the Apostles, p. 390.

“እናም በእምነት ወንድሞቹ ከሆኑት በሚቀርብለት ርህራሄ እና ድጋፍ ላይ እንኳን አመኔታ አልነበረውም፡፡ ያልተለወጡት አይሁድ በሚጓዝበት ሁሉ በመከተል ከእርሱ የተቃረኑ ሃሳቦችን (ሪፖርት)፤ ስለ እርሱም ይሁን ስለ ሥራው፤ በደብዳቤም ይሁን በአካል በመገኘት በእየሩሳሌም ለመዝራት የዘገዩ አልነበሩም። እናም ደግሞ አንዳንድ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች እንኳን ሳይቀሩ እነዚህን ተራ ወሬዎች እንደ እውነት በመቀበል እነዚህን ሰዎች ለመቃረንም ሆነ ከእነርሱ ጋር ህብረት ላለማድረግ ፍላጎት አላሳዩም ነበር፡፡”—Page 398.

# የመወያያ ጥያቄዎች፡

1. ጳውሎስ በኤፌሶን ያገኛቸው አስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት ቀደም ሲል የመጥምቁ ዮሐንስ ተከታዮች የነበሩ በኋላ ደግሞ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት የሆኑ ነበሩ (ሐዋ 19፡1-7)፡፡ ይህን ክፍል በጥልቀት ተጠምቀው የነበሩ፣ከሌላ ቤተ-እምነት የመጡና የአድቬንቲስትን እምነት የተቀላቀሉ ክርስትያኖች እንደገና መጠመቅ እንዳለባቸው ለማስረዳት መጠቀማችን ትክክል የሆነው ለምን ይመስሎታል? አጽሎስ እንደገና ባለመጠመቁ ውስጥስ የምናስተውለው እውነታ ይኖር ይሆን?

2. ጳውሎስ ስለነበረበት ሁኔታ ያስቡ፡፡ በኢየሱስ በማያምኑ በራሱ ወገኖች ተቀባይነት አጣ፤ በኢየሱስ የሚያምኑ ብዙ አይሁድ እንኳን “ዋና መለያዎችን” ለውጧል በሚል ምክንያት ጳውሎስን የሚመለከቱት በትልቅ ጥርጣሬና ባለማመን ነበር፡፡ብዙ አረማውያን እርሱ በሚናገረው ወንጌል ላይ ጥላቻ ነበራቸው፡፡ ግን ይህ ሁሉ ለምን? በዚህ ሁሉ ተቃውሞ ውስጥ ግን ጳውሎስ በጽናት የቀጠለው ለምንድን ነው?

3. የሰንበት ቀን ወደ እሁድ ስለመቀየሩ ወይም ከዚህ በኋላ አስፈላጊ እንዳልሆነ በሰዎች ስለሚነሱ መከራከሪያዎች ያስቡ። ለእነዚህ የመከራከሪያ ሀሳቦች ሰንበትን መታዘዝ በእምነት ከሆነና የመዳናችን ብቸኛ ተስፋ ያረፈበትን በማስተዋል ከሆነ ሌሎቹን ዘጠኙን ትዕዛዛት ከመታዘዝ ተለይቶ ህጋዊነት ሊያስብለው እንደማይችል መልስ ለመስጠት የምንችለው እንዴት ነው?

# 11ኛ ትምህርት ከጳጉሜ 3 - መስከረም 4

## በኢየሩሳሌም መታሰር

*ሰንበት ከሰአት*

*ለዚህ ሳምንት ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡- ሐዋ.21፣ ሮሜ 2፡28-29፣ ገላ.5፡6፣ ሐዋ.22፣ ሐዋ. 23፡1-30፣ ማቴ. 22፡23-32፡፡*

**መታሰቢያ ጥቅስ** ፡- "በሚቀጥለውም ሌሊት ጌታ በአጠገቡ ቆሞ። <<ጳውሎስ ሆይ አይዞህ በኢየሩሳሌም እንደመሰከርህልኝ በሮምም ደግሞ ልትመሰክርልኝ ይገባሃል>> አለው።" (ሐዋ. ሥራ 23፡11)

ከጳውሎስ የመጀመርያ ሚሲዮናዊ ጉዞ በኋላ በቤተክርስትያን ውስጥ አህዛብ እንዴት ወደ እምነቱ መቀላቀል እንደሚገባቸው በተመለከተ መሰረታዊ የሆነ አለመግባባት መፈጠሩ ግልጽ ሆነ (ሐዋ.15፡1-5)። ግጭቱ እያየለ ቢመጣም ጳውሎስ ግን በቤተክርስትያን ውስጥ አንድነት የሚመጣበትን መንገድ ያቅድ ነበር። የመማክርት ጉባኤው ድሆችን እንዲያስብ ስላሳሰቡት(ገላ. 2፡10) የአህዛብ ቤተክርስትያናት በይሁዳ ለሚገኙ ወንድሞች «ቅዱሳን ቤተሰቦች» (1ኛ ቆሮ.16፡1) የገንዘብ እገዛ እንዲያደርጉ ጋበዛቸው፤ ምናልባትም በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለውን ልዩነት ለማፍረስ እንደ ድልድይ ይሆናል ብሎ ተስፋ አደረገ፡፡

አደገኛ ሊሆን እንደሚችል ቢያውቅም ጳውሎስ በሦስተኛው ጉዞ መጨረሻ ላይ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ወሰነ። በአንድ በኩል ወገኖቹ ለሆኑት አይሁዳውያን ያለውን እውነተኛ ፍቅር ለማሳየት ሲሆን (ሮሜ 9፡1-5) በሌላ በኩል ደግሞ አንድ የሆነ ቤተክርስትያን እንዲኖር ይናፍቅ ስለነበር(ገላ. 3፡28፤5፡6) ነው። አይሁዳውያንም ይሁኑ አህዛብ ህግን በመጠበቅ ሳይሆን በእምነት እኩል ስለዳኑ (ሮሜ 3፡28-30) አብሮ ላለመሆን የህግ ቅድመ ሁኔታዎችን መደርደር ሁሉን የሚያካትተውን የወንጌልን ባህሪ የሚጣረስ ሃሳብ ነው (ኤፌ. 2፡11-22)። በህይወቱ አዲስ ምዕራፍንና ተልእኮን አንግቦ የሚሄደውን ጳውሎስ እስቲ እንከተለው፡፡

የዚህን ሳምንት ጥናት አንብበው ለ ሰንበት ይዘጋጁ፡፡

## እሑድ ጳጉሜ 4

### የእየሩሳሌም መሪዎችን ማግኘት

ጳውሎስ ልክ እየሩሳሌም እንደደረሰ ምዕመናን ምናሶን ቤት እንዲቆይ በማድረግ ሞቅ ያለ አቀባበል አደረጉለት (ሐዋ. 21፡16-17)።

በሐዋ.21፡18-22 ላይ ያዕቆብና የእየሩሳሌም ሽማግሌዎች ጳውሎስ በአካባቢው በሚገኙና ለሙሴ ህግ ቅናት በነበራቸው አይሁዳውያን ዘንድ ስለሚኖረው ተቀባይነትተጨነቁ፡ ፡ ለአይሁዳውያኑ የተነገራቸው እርሱ በውጪ የሚገኙ አይሁዳውያን የሙሴን ህግ እንዲተው «ልጆቻቸውም እንዳይገረዙ ልማዳቸውንም እንዲተው»እንደሚያስተምር ነው፡፡ (ሐዋ. 21፡21)

ነገር ግን ይህ ፈጽሞ ትክክል አልነበረም፡፡ ጳውሎስ እያስተማረ የነበረው ድነትን ለማግኘት መገረዝም ሆነ አለመገረዝ ምንም አይጠቅምም ምክንያቱም አይሁድም ይሁኑ አህዛብ በየሱስ ላይ ባላቸው እምነት እኩል ድነዋል(ሮሜ 2፡28-29፣ ገላ. 5፡ 6፣ ቆላ. 3፡11)፡፡ ይህ አይሁዳውያንን በግልጽ ህጉንና መስፈርቱን ፈጽመው እንዲረሱ ከማስተማር ፈፅሞ የተለየ ነው፡፡ መታዘዝ ብዙ ጊዜ የሚተረጎመው ህግ በመጠበቅ መዳን «Legalism» ተብሎ ቢሆንም ትክክለኛ ትርጉሙ ግን ያ ብቻ አይደለም፡፡

ሐዋ. 21፡ 23-26ን ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ እንዴት አድርጎ ነው አሁንም ታማኝ አይሁዳዊ መሆኑን ያሳየው?

__________________________________________________________

__________________________________________________________

ጳውሎስ አሳማኝ በሆነ መልኩ እንዲራመድ(ግጭትን የሚያነሳሳ ነገር እንዳይናገር) ተመክሮ ነበር፡፡ የሚወራበት አሉባልታ ሐሰት መሆኑን ለማረጋገጥ የግድ አይሁዶች የሚያደርጉትን ነገር አድርጎ እንዲያሳይ ተመከረ፡፡ ይህም ለተወሰኑ ስለት ላለባቸው ሰዎች ራሳቸውን ናዝራዊ እንዲያደርጉ ወጪያቸውን በመሸፈን ይገለጣል፡፡ ይህ ስለት ደግሞ አንድ አይሁድ ራሱን ለእግዚአብሔር በተለየ መንገድ የሚያስረክብበት ሐይማኖታዊ ስነስርአት ነበር፡፡

የሚያሳዝነው ግን ጳውሎስ እጁን ሰጠ(ይህንን ምክር ሰማ)፡፡ ጀግና የምንላቸው ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ጨምሮ የራሳቸው የሆነ ጉድለት ነበራቸው። ለምሳሌ የአብርሃምን፣ የሙሴን፣ የጴጥሮስ እና የሌሎችንም ህይወት እንደምንመለከተው ማለት ነው፡፡ ጳውሎስ ይህንን ያደረገው ከአይሁዳውያን ጋር እንደ አይሁዳውያን

ሆንኩ ያለውን የራሱን መርህ ለመከተል ይሆናል(1 ቆሮ. 9፡19-23) ወይንም የስለቱ ይዘት ግልፅ ባይሆንም እንኳን ጳውሎስ እራሱ ጥቂት ቀደም ብሎ ስለት ስለተሳለም ሊሆን ይችላል(ሐዋ. 18፡18) ብለን የመከራከሪያ ነጥቦችን ልናስቀምጥ እንችላለን። በዚህ ጊዜ ግን ያደረገው ከምክሩ በስተጀርባ ያለውን ህግን ወይንም ስርአትን ፈፅሞ መዳንን በሚደግፍ መልኩ ሀሳቡን ድርድር ውስጥ እንዲገባ አደረገ(አመቻመቸ)። ይህ ጳውሎስ በብርቱ ይቃወመው የነበረውን የሁለት ወንጌል አመለካከት ያንፀባርቃል። ይህም ሁለት ወንጌል አንዱ ለአህዛብ መዳን በእምነት ለአይሁድ ደግሞ መዳን በስራ ነው የሚለው ነበር፡፡ «ጳውሎስእነርሱ የጠየቁትን ነገረ ሁሉ ለመስጠት ከእግዚአብሔር ዘንድ ስልጣን አልተሰጠውም» Ellen G. white, The Acts of the Apostlees, P 405

ትክክል(ጠቃሚ) ለመሆን በምናደርገው ጥረት ውሰጥ እንዲህ አይነት ተመሳሳይ ስህተትን ከመስራት ልንጠነቀቅ የምንችለው እንዴት ነው?

ሰኞ ጳጉሜ 5

## አመጽ በቤተ መቅደስ

የቤተክርስትያን መሪዎች ያቀረቡትን ሀሳብ ጳውሎስ ስለተቀበለ የሰዎቹ ስለት እንዲጠናቀቅ ለማገዝ የሰባት ቀን የመንጻት ስርአት መፈፀም ነበረበት(ዘዳ.19፡ 11-13)፡፡ በአይሁድ ባህል ከአህዛብ መንደር የመጣ ማንኛውም ሰው እርኩስ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ወደ ቤተመቅደስ መግባት አይችልም ነበር፡፡ ጳውሎስ ለካህናት ከናዝራውያኑ መንፃት ስርዓት ጋር በተያያዘ ስለ መንፃቱ ከማሳወቁ በፊት ራሱን ማንፃት የተገባው ለዚህ ነበር(ሐዋ. 21፡26)።

ሐዋ.21፡27-36ን ያንብቡ፡፡ ከሰባቱ ቀን መንፃት በኋላ ጳውሎስምን ገጠመው?

---

---

አመፅ ተቀሰቀሰ። በጳውሎስ ላይ አመጽ እንዲነሳ ያደረጉት ሰዎች የአይሁድን ሃይማኖት በተለይም የተቀደሰውን የቤተመቅደስ ስርአት ያራክሳል በማለት ክስ አቀረቡበት። ከጳውሎስ ጋር አብሮ የተጓዘው የኤፌሶን ሰው ጥሮፊሞስ አማኝ አህዛብ ስለነበር (ሐዋ21፡ 29) አይሁዳውያን ብቻ በሚገቡበት ቤተመቅደስ ውስጥ ጳውሎስ ይዞት የገባ መሰላቸው፡፡ ያንን አድርጎ ቢሆን ኖሮ ጳውሎስ ከባድ ጥፋትን ያጠፋ ነበር፡፡ ውጫዊውንና ውስጣዊውን ጉባኤ በሚለየው ግንብ ላይ በግሪክና በላቲን ቋንቋ የተፃፈ አህዛብ ጎብኚዎች መግባት እንደማይችሉ የሚያስጠነቅቁ ምልክቶች ነበሩ፡፡ ከገቡ ግን ለሚከተላቸው ሞት ራሳቸው ሃላፊነቱን ይወስዳሉ፡፡

«በአይሁዶች ህግ መሰረት ያልተገረዘ ሰው ወደ ተቀደሰው ስፍራ ውስጠኛ ክፍል ከገባ የወንጀል ቅጣቱ ሞት ነው። ጳውሎስ ከኤፌሶን ሰው ጥሮፊሞስ ጋር በከተማው ውስጥ ስለታየ ወደ ቤተመቅደስ አስገብቶት ይሆናል ተብሎ ተገመተ፡፡ ያንን አላደረገም፤ እርሱ ራሱ ደግሞ አይሁዳዊ ስለነበር ወደ ቤተመቅደስ መግባቱ ህግን አንደጣሰ አያስቆጥረውም፡፡ ምንም እንኳን ክሱ ሙሉ በሙሉ የሐሰት ቢሆንም ቀድሞ ይታማበት በነበረው ነገር ጥፋተኛ እንዲባል ግን ሰዎችን አነሳስቷል፡፡ የከተማው ጩኸት በርክቶ ከቤተመቅደሱ ደጃፍ አልፎ ስፍራው ወደ ሁከትና ረብሻ ቦታነት ተለወጠ፡፡»Ellen G white, The Acts of the Apostles, P. 407።

የአመጽ ወሬው ወደ ሮም ጦር ሰፈር ሲደርስ የጦር አዛዡ ቀላውዲዮስ ሉስዮስ (ሐዋ. 21፡31-32፤23፡26) ከጦር መኮንኖቹና ሠራዊቶቹ ጋር ደርሶ ህዝቡ ጳውሎስን ሳይገድሉት አተረፈው፡፡

የጥቃቱ አላማ የሆነው ጳውሎስ እንደመሆኑ መጠን በሰንሰለት ታሰረ፤ የጦር አዛዡም ስለተፈጠረው ነገር መመርመር ጀመረ፡፡ በህዝቡ ሁከት መካከል ጳውሎስ ወደ ጦር ምሽጉ እንዲወሰድ ትዕዛዝ ሰጠ፡፡

ይህ አመጽ እንዲቀሰቀስ የሆነው በሐሰት አሉባልታ ምክንያት ነበር፡፡ ጆሮ ስለምንሰጣቸው ሲብስም ስለምናስተላልፋቸው የአሉባልታ አይነቶች መጠንቀቅ ያለብን እንዴት ነው?

**ማክሰኞ** **መስከረም 1**

## በህዝቡ ፊት

ሐዋ. ሥራ21፡37-40 ቀጥሎ ምን እደተከናወነ ይነግረናል። ጳውሎስ ወደ ሮም የጦር ሰፈር ለምርመራ እየተወሰደ እያለ እንዲሞት እየወተወተ ላለውህዝብ ንግግር ማድረግ እንዲችል አዛዡን ፈቃድ ጠየቀ፡፡

ከአዛዡ ጋር በግሪክ ቋንቋ በሚነጋገርበት ጊዜ አዣዡም ከሦስት አመት በፊት በእየሩሳሌም ሮማውያንን ተቃውመው ሰዎች አመፅ እንዲያነሳሱ ያደረገው የግብፅ አይሁዳዊ እሱ መሰለው፡፡ አመፁም በሮማውያን ሃይል አማካኝነት በቁጥጥር ስር ሲውል በዚህ አመጽ ላይ የተሳተፉ ብዙዎች ሲሞቱና ሲታሰሩ ግብፃዊው ሰው ደግሞ አምልጦ ነበር፡፡

ጳውሎስእርሱ የመጣው ከግብጽ ሳይሆን ከጠርሴስ እንደሆነ ሲያረጋገጥ እንዲናገር ተፈቀደለት፡፡ በንግግሩም ላይ የቀረበበትን ክስ ለማስተባበል ዝርዝር

ምላሽ አላቀረበም (ሐዋ. 21፡28)። ነገር ግን እንዴት እደተለወጠ፣ለአይሁድ ስርአት ያለውን መሰጠትና ቅንነት በዚያም ምክንያትበየሱስ የሚያምኑትን አማኞች ያሳድድ እንደነበር ነገራቸው፡፡ ነገር ግን ጌታ በተለያዩ ራእዮች ከተገናኘው ጀምሮ እርሱን ከመከተል ውጪ ሌላ አማራጭ እንዳልነበረው ይህም ሙሉ በሙሉ የህይወቱን አቅጣጫ እንደቀየረውና ለአህዛብም ይሰብክ ዘንድ እንደተጠራ ነገራቸው፡፡ ከእነርሱ ጋር ስነ መለኮታዊ የሆነ ውይይት ውስጥ ከመግባት ይልቅ የራሱን የሕይወት ልምምድ በማካፈል እያደረገ ያለውን ነገር ለምን እንዳደረገ አስረዳቸው፡፡

ሐዋ.22፡22-29ን ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ ለአህዛብ ሐዋሪያ ሆኖ እንደተጠራ ሲናገር ህዝቡ ምን አይነት ምላሽ ሰጡ?

---

---

ጳውሎስ እንዲናገር እድል መስጠቱ ምንም ለውጥ አላመጣም፡፡ እንደውም ለአህዛብ ያለውን መሰጠት ስለጠቀሰ በርሱ ላይ ክስን ላቀረቡ ሰዎች እውነት መሆናቸውን አረጋገጠላቸው (ሐዋ. 21፡28)። ስለዚህ ህዝቡ ደግሞ አመፃቸውን አፋፋሙ፡፡

የሮሙ አዛዥ ጳውሎስ የተናገረውን ነገር በሙሉ ማስተዋል ስላልቻለ እየተገረፈ ምርመራ እንዲደረግበት ወሰነ፡፡ ጳውሎስ ንፁህ የአይሁድ ደም

ያለው ግለሰብ ቢሆንም (ፊሊ. 3፡5) የሮም ዜግነትም ነበረው፡፡ ይህን በሚናገርበት ጊዜ አዛዡ ትዕዛዙን ማስቆም ነበረበት። ጳውሎስ እንደ ሮም ዜጋ ይህ አይነት ግርፋት ሊደርስበት ፈፅሞ አይገባም።

የጳውሎስን ንግግር እሰቲ ያንብቡ(ሐዋ. 22፡1-21)። ጳውሎስ ራሱን ከመከላከል ባለፈ ለአይሁድ ወገኖቹ ይሰብክ እንደነበር የሚያሳይ ምን ማስረጃ ተመለከታችሁ? የርሱን የመለወጥ ታሪክ የነገራቸው ለምንድነው? የሰዎች የመለወጥ ታሪኮች ከፍተኛ ሃይል ያላቸው እንዴት ነው?

**ረቡዕ** **መስከረም 2**

## በሸንጎው ፊት

የሮሙ አዛዥ ጳውሎስ የሮምን መንግስት ለአደጋ እንደማይዳርገውና ጉዳዩ የአይሁድ ህዝብ የውስጥ አለመስማማት መሆኑንሲረዳ የአይሁድ መማክርት ሸንጎ ጉዳዩን እንዲይዝ ጠየቀ (ሐዋ. 22፡30፤ 23፡29)።

ሐዋ.23፡1-5ን ያንብቡ፡፡ በሸንጎ ፊት ጳውሎስ በምን አይነት መንገድ ነበር ራሱን የተከላከለው?

---

---

የጳውሎስ የመግቢያ ንግግር እንደእስረኛ የእግዚአብሔርን ስም እንደተሳደበ ተቆጥሮ ወዲያው አፉ ላይ ተመታ። ይህ ሲሆን ወዲያው ያሳየው ባህሪ የጳውሎስን ቁጡነት በጨረፍታ አሳይቶናል፡፡ ሊቀ ካህናቱን «በኖራ የተለሰንክ ግድግዳ» (ሐዋ.23፡2) ብሎ ሲናገረው የሱስ ግብዝ የሆኑ ፈሪሳውያንን የኮነነበትን መንገድ እያስተጋባ ነበር (ማቴ.23፡27)፡፡ ነገር ግን ጳውሎስ ይህንን ያለው ሊቀ ካህናቱን መሆኑን አለማወቁን መግለጡ የአይን ችግር ስለነበረበት ይሆናል የሚለውን ግምት ሙሉ ለሙሉ ባዶ አያደርገውም።

ሐዋ.23፡6-10ን ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ በምን አይነት ብልሃት ነበር የፍርድ ሂደቱ እዲረበሽ ያደረገው?

---

---

ሸንጎው የተመሰረተው በሰዱቃውያንና በፈሪሳውያን ሲሆን ሁለቱ ጎራዎች ደግሞ ቀኖናን ጨምሮ በብዙ ጉዳዮች ፈጽመው የማይስማሙ ነበሩ። ሰዱቃውያን ለምሳሌ የሃይማኖት መጽሐፎቻቸው የያዙት አምስቱን የሙሴን መጽሐፍት (ፔንታቱክ) ሲሆን በሙታን ትንሣኤም አያምኑም (ማቴ. 22፡23-32) ነበር።

የጳውሎስ ንግግር (ሐዋ. 23፡6) ግን የሸንጎውን ትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር የበለጠ ጠንካራ ስልት ነበር፡፡ በደማስቆ መንገድ ላይ ከሞት የተነሳውን የሱስን በማግኘቱ ስለተለወጠና ወደ ሐዋሪያዊ አገልግሎቱ ስለገባ የተከሰሰበት ዋና ጉዳይ በትንሳኤው ማመኑ ነበር (ሐዋ. 24፡20-21፤26፡6-8)። ቀድሞ ከነበረው ቅንአት አሁን ያለበትን ሁኔታ ሌላ ምንም ሊገልፅ አይችልም፡፡ የሱስ ከሞት ካልተነሳ አገልግሎቱ ሁሉ ከንቱ ይሆን ነበር። እርሱም ይህንን ጠንቅቆ ያውቅ ነበር (1 ቆሮ.15፡14-17)።

በዛ ምሽት ጳውሎስ በጦር ሰፈር ውስጥ በነበረበት ጊዜ ጌታ በሚያበረታታ ቃል ተገናኘው፡- «ጳውሎስ ሆይ አይዞህ! በኢየሩሳሌም እንደመሰከርክልኝ በሮምም ደግሞ ልትመሰክርልኝ ይገባሃል» አለው (ሐዋ.23፡11)። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለ ይህ የተስፋ ቃል መነገሩ ለጳውሎስ ትልቅ ትርጉም ይሰጠዋል፡፡ በሮም ለመስበክ የነበረው ከፍተኛ ጉጉት (ሐዋ. 19፡21፤ሮሜ1፡13-15፤15፡22-29) እውን ሊሆን ነበረ፡፡

ሐሙስ መስከረም 3

## ወደ ቂሳርያ መተለለፍ

በህጋዊ መንገድ ጳውሎስን ማስወገድ ባለመቻላቸው ስለተበሳጩ በራሳቸው መንገድ በቡድን ጳውሎስን በማጥቃት ለመግደል አሴሩ።

ሐዋ.23፡12-17ን ያንብቡ። ሴራቸው ምን ነበር? እንዴትስ ሆኖ ነበር የተጨናገፈው? ቅንአት ያላቸው ሰዎች ለትልቅ ጥፋት መንስኤ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይህ ታሪክ ምን ያስተምረናል?

---

---

ከአርባ በላይ የሆኑ አይሁዳውያን በጳውሎስ ላይ በማሴር እርሱን ለመግደል መሃላ መግባታቸው ሐዋሪያው በእየሩሳሌም ምን ያክል ጥላቻን እንዳነሳሳ የሚያሳይ ነው፡፡ ሉቃስ ስለነዚህ ሰዎች ማንነት በግልጽ አይጠቅስልንም፤ ነገር ግን የአይሁድን እምነት አሉ ከተባሉ ከሃዲዎችና ባለንጣዎች ለመከላከል ማንኛውንም መስዋዕት ለመክፈል የተዘጋጁ አክራሪ አይሁዳውያን ናቸው፡፡ በመጀመርያው ከፍለ ዘመን በይሁዳና አካባቢዋ እንዲህ ያለ የሃይማኖት ጽንፈኝነት ከፍተኛ ነውጥ ካለው የጋለ ብሔራዊ ስሜት ጋር ሲጣመር መመልከት የተለመደ ነበር፡፡

ነገር ግን እግዚአብሔር ሲያዘጋጅ የሴራው ወሬ የጳውሎስእህት ልጅ ጆሮ ደረሰ። ስለ ጳውሎስ የቤተሰብ ሁኔታ ምንም ማወቅ ባለመቻላችን ትንሽ ቢያሳዝነንም እርሱና እህቱ ግን ያደጉት በእየሩሳሌም ነበር(ሐዋ. 22፡3)። ከዛም አግብታ ቢያንስ አንድ ወንድ ልጅ እንዳላት እናውቃለን፡ለማንኛውም የጳውሎስ እህት ልጅ የሆነው ትንሽ ልጅ (ሐዋ.23፡18፥22) «እጁን ይዞ» ስለሚል(ሐዋ.23፡19) ልጁ በአስራዎቹ የእድሜ ክልል በመገኘቱ ወደ ጦር ሰፈር ሄዶ ለመነብኘትና የተፈጠረውን ለመናገርም እድል እንዲያገኝ አድርጎታል፡፡

ሐዋ.23፡26-30ን ያንብቡ፡፡ የጦር አዛዥ የሆነው ሉስዮስ ለአገረ ገዥ ፊሊክስ ያስተላለፈው መልእከት ምን ነበር?

---

---

ደብዳቤው ስለተፈጠረው ጉዳይ ሚዛናዊ የሆነ ሪፖርትን ይዞ ለፊልክስ ደረሰው። ከዚያም በተጨማሪ ጳውሎስየሮም ዜጋ ስለሆነ ያገኘውን ጥቅም ያትታል፡፡ የሮማውያን ህግ መብት ያላቸውን የራሱን ዜጎች ለምሳሌ በህጋዊ ሁኔታ እንዲዳኙ፣ በዚያም ራሳቸውን የመከላከል መብት እንዲያገኙ (ሐዋ. 25፡16) እንዲሁም ያልተገባ የፍርድ ሂደት ቢኖር እንኳን ለአገረ ገዥው አቤቱታቸውን እንዲያቀርቡ መብት ይሰጣቸዋል(ሐዋ. 25፡10-11)።

ፊልክስም ግላዊ ክብሩን ለማሳየት ሳይሞክር ጳውሎስን ትክክለኛውን የህግ መንገድ ተከትሎ በተገቢ መንገድ አስተናገደው። ቃሉን ከጠየቀ በኋላ ከሳሾቹ እስኪመጡ ድረስ እንዲጠበቅ አዘዘ፡፡

እስቲ በጳውሎስ ህይወት ላይ የእግዚአብሔር ነገሮችን ማመቻቸት ምን እንደሚመስል ያስቡ፡፡ በምንም ያክል ከባድ ፈተናና መከራ ብናልፍ እግዚአብሔር ላደረገልን ነገር ምን ያክል በትህትና ምላሽ ሰጥተናል?

**ዓርብ** | ነሐሴ **18**

**ተጨማሪ ጥናት፡** «በዚህ ወቅት ጳውሎስና አጋሮቹ በእየሩሳሌም መሪዎች ወደሆኑት ሰዎች ቀርበው የአህዛብ ቤተክርስትያናት ለተቸገሩ አይሁድ ወንድሞቻቸው የላኩትን አመጡ፡፡...

«በራሳቸው ፍላጎት ያደረጉት ይህ ስጦታ አህዛብ ሆነው የተለወጡ ሰዎች በአለምአቀፍ ደረጃ ተደራጅቶ ላለው የእግዚአብሔር ስራ ታማኝነታቸውንማሳያ ሲሆን ይህ ደግሞ በሁሉም ዘንድ መልካም የሆነ ተቀባይነት ማግኘት እንደሚገባው ያሳያል፡፡ ነገር ግን ለጳውሎስና አጋሮቹ ግልጽ በሆነ መንገድ አንዳንዶች ለወንድሞች ያላቸውን ፍቅር ስጦታ በመስጠት የገለጹትበን የወንድማማች መንፈስ ማድነቅ ተሳናቸው፡፡» Ellen G. white, The acts of the Aposttles, pp.399-400

«በቤተክርስትያን ያሉ መሪዎች እንደ ተጠራ ጌታም ወደ አህዛብ እንዲደርስ እንደላከው ለማመን ፈቃደኛ ቢሆኑ ኖሮ  እግዚአብሔር ጳውሎስን ለነርሱ ያቆይላቸው ነበር። የጳውሎስን ስራ በአጭሩ እንዲጠናቀቅ ፈልጎ አልቀባውም፤ በእየሩሳሌም ያሉ የቤተክርስትያን መሪዎች ተነስተውበት ብዙ ነገር ሲያደርጉበትም ያንን ለመቋቋም እግዚአብሔር ተዓምርም አላደረገም፡፡

«ተመሳሳይ የሆነ መንፈስ አሁንም ድረስ ተመሳሳይ ውጤትን ያመጣል፡፡ የመለኮት የፀጋ ስጦታን ለማድነቅና ለማሳደግ ችላ ማለታችን ቤተክርስትያን ልታገኝ የሚገባትን ብዙ በረከት እንዲቀርባት አድርጓል፡፡ እግዚአብሔር ስራው ተቀባይነት ቢያገኝ

ኖሮ የአንዳንድ ታማኝ አገልጋዮችን አገልግሎት ምን ያክል ያረዝመው ይሆን፡፡ ቤተክርስትያን ግን ማስተዋላችንን የነፍሳት ጠላት እንዲነጥቅና የክርስቶስ አገልጋዮች የሚሉትንና የሚያደርጉትን ነገር በተሳሳተ መንገድ እንዲተረጎምና እንዲቀርብ የምትፈቅድ ከሆነ፣ በርሱ መንገድ በመቆም ለስራው እንቅፋት የሚሆኑ ከሆነ ጌታም የሰጣቸውን ባርኮት ይነጥቃቸዋል። . . .

‹‹እጆች ህይወት አልባ በሆኑ ደረቶች ላይ ሲያርፉ፣ የማስጠንቀቂያና የማበረታቻ ድምጽ ፀጥ ሲል ያኔ እምቢተኞች የነበሩት እነርሱ ያካፈሉትን በረከት አይተው ይቀበሉ ይሆናል፡፡ በህይወታቸው ቆይታ ማሳካት ያልቻሉትን በሞታቸው ያሳኩ ይሆናል፡፡” ገፅ 417, 418

# የመወያያ ጥያቄዎች

1. ወደእየሩሳሌም ሲመጣ በመልካም ሁኔታ እንደማይቀበሉት ጳውሎስ ቢያውቅም ከግላዊ ጥቅሙ በላይ ለቤተክርቲያን ጥቅም የቆመ ነበር፡፡ የእርሱን ፈለግ መከተል ያለብን እስከምን ድረስ ነው?

2. በኢየሩሳሌም ጳውሎስ እንዲደራደር ካደረገው ሁኔታ ምን የምንማረው ነገር አለ? መርሆቻችንን ሳንጥስ እንዴት አድርገን ነው ከአካባቢው ጋር መስማማት የምንችለው? ግን ይህን ማድረግስ ይቻለናል?

3. የቤተክርስትያን ህብረት ሁልጊዜም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ምንም እንኳን ለነገሮች ያለን አመለካከት የተለያየ ቢሆንም እንዴት አድርገን ነው አብረን በመስራት አንድ መሆን መቻልን የምንማረው?

# 12ኛ ትምህርት ከመስከረም 5 - 11

## በቄሳርያ መታሰር

ሰንበት ከሰአት

*ለዚህን ሳምንት ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡- ሐዋ. ሥራ 24፣ ሐዋ. ሥራ 25፣ ሐዋ.ሥራ 26፣ 1 ቆሮ. 1፡23፡፡*

**መታሰቢያ ጥቅስ** ፡- "በቀላሉም ሆነ በብዙ አንተ ብቻ ሳትሆን ዛሬ የሚሰሙኝ ሁሉ ከዚህ ከታሰርኩበት ሰንሰለት በስተቀር እንደ እኔ ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔርን እለምናለሁ" (ሐዋ. ሥራ 26፡29)

ጳውሎስ ወደ ቂሳርያ ሲዘዋወር በከተማይቱ (ሐዋ. 24፡27) በተለይም በሄሮድስ ግቢ ውስጥ በእስር የሁለት አመታት ቆይታው ተጀመረ፡፡ ይህ ስፍራ ደግሞ የሮም አመራሮች መኖሪያ ነበር(ሐዋ. 23፡35)፡፡ በነዚህ አመታት ውስጥ በሁለቱ የሮም ገዥዎች (ፊሊክስና ፊስጦስ) እና በንጉሱ (አግሪፓ 2ኛ) ፊት ቀርቧል፤ በዚህም እግዚአብሔር የሰጠውን የወንጌል አደራ መፈፀም ቻለ(ሐዋ. 9፡15)፡፡

በዚህ ሁሉ ምርመራ እርሱን ጥፋተኛ የሚያስብል ምንም አይነት ማስረጃም ሆነ ምስክር ስላልተገኘ ጳውሎስ ሁልጊዜም ንጹህ ሰው መሆኑን ያስረዳ ነበር፡፡ እንደውም ትረካው ፍንትው አድርጎ የሚያሳየን ጳውሎስ ለመታሰር የሚያበቃው ምንም ነገር እንደሌለና ለቄሳር ይግባኝ ባይል ኖሮ ሊለቀቅ እንደሚችል ነበር(ሐዋ. 26፡32)፡፡ እነዚህ ምርመራዎች ጳውሎስ ስለየሱስና በትንሳኤ ላይ ስላረፈው ታላቁ የተስፋ ቃል ለሌሎች ለመመስከር ምቹ አጋጣሚ ፈጠሩለት፡፡

ሆኖም እነዚያ አመታት የስጋትና በየሩሳሌም ከምትገኘው ቤተክርስትያን ምንም አይነት ድጋፍ ያላገኘባቸው አታካች የሆኑ የእስራት ጊዜያት ነበሩ፡፡ የተወሰኑት የቤተክርስትያን መሪዎቹም «ለተፈጠረው ምክንያት አልባ ጥላቻና ውግዘት ባብዛኛው ኃላፊነቱን መውሰድ ያለበት ጳውሎስ እንደሆነ ይሰማቸው ነበር፡፡» Ellen G. white, The Acts of the Apostles, P. 403

የዚህን ሳምንት ትምህርት አጥንተው ለመስከረም 12 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡

**እሑድ** **መስከረም 6**

## በፊሊክስ ፊት

ጳውሎስ ወደ ቄሳርያ ከተዘዋወረ ከአምስት ቀናት በኋላ ወሳኝ የሚባሉ የአይሁድ አመራሮች ሊቀ ካህናቱና አንዳንድ የሸንጎ አባላት ጠርጠሉስ ከተባለ እውቅ ጠበቃ ጋር በአንድነት ሆነው ከየሩሳሌም በመምጣት በጳውሎስ ላይ ያላቸውን ክሳቸውን በፊሊክስ ፊት አቀረቡ (ሐዋ. 24፡1-9)

በሐዋሪያት ስራ መጽሐፍ ውስጥ ከሳሾቹ ጠበቃ ቀጥረው የምናገኛቸው በዚህ ስፍራ ብቻ ነው፡፡ ጠርጠሉስ በንግግሩ ላይ የአገረ ገዥውን ይሁንታ ለማግኘት አስገራሚ ስትራቴጂ ለመጠቀም ጥረት አደረገ፡፡ በፊሊክስ አገዛዝ ወቅት አይሁዳውያን ለረጅም ጊዜ በሰላም ስለመኖራቸው የተናገረው ንግግር እውነት አልነበረም፡፡ እንደውም ከየትኛውም የአገዛዝ ጊዜ በበለጠ ጨቋኝና አስጨናቂ ከመሆኑ የተነሳ አይሁዳውያን በሮማውያን አመራር ላይ ያላቸው ጥላቻ እጅግ መራር እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ጠርጠሉስ ብዙ ብልሃትን በመጠቀም በዚህም ሁኔታ ቢሆን የራሱን የአገረ ገዥውን የአመራር ፖሊሲ ማለትም መራር የሆነ ጭቆናን ማሳደር ብቻ ፖለቲካዊ መረጋጋትን እንደሚያመጣለት ሊያሳምነው ጣረ፡፡

በመቀጠልም በጳውሎስ ላይ ሶስት ዝርዝር ክሶችን አቀረበ 1. በአገዛዙ ውስጥ በሚገኙ አይሁዳያን መካከል ሁከትን በማስነሳት ያውካል (ሐዋ. 24፡5) 2. የናዝራውያን ወገን ቀንደኛ መሪ ነው፤ (ሐዋ. 24፡5) ይህም የክርስትና እንቅስቃሴ ብጥብጥን ፈጣሪ እንደሆነ ያመላክታል 3. ቤተመቅደሱን ለማርከስ ሞክሯል (ሐዋ. 24፡6)

ሐዋ. 24፡10-19ን ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ ለቀረቡበት ክሶች የሠጠው ምላሽ ምን ይመስል ነበር?

_______________________________________________

_______________________________________________

ጳውሎስ ለክሱ ከሰጠው ምላሽ ሁለቱ የከሳሾቹን ክስ ያፈረሱ ነበሩ፡- 1. ከእስያ አውራጃ የመጡ ምስክሮች (ሐዋ. 24፡18-19) አለመኖራቸውና እነርሱ ቢኖሩ ኖሮ ክሱን ውድቅ ማድረግ እንደሚቻላቸው 2. በዚያ የነበሩት አይሁዶች ሊናገሩ የሚችሉት ከሳምንት በፊት በሸንጎ ፊት ሲቀርብ (ሐዋ. 24፡20) ስለ ሙታን ትንሳኤ ከማመኑ በቀር ሌላ ምንም የሚከሰስበት ነገር እንዳላገኙበት (ከሐዋ. 23፡6 ጋር ያነፃፅሩ) ተናገረ፡፡

ፊሊክስ ወዲያውኑ የጳውሎስ የመከራሪያ ነጥብ ሚዛን እንደሚደፋ ተረዳ፡፡ ይህም ምናልባት ባለቤቱ ድሩሲላ አይሁዳዊ ስለነበረች ከክርስትና ጋር በተወሰነ መልኩ የቀረበ ስለነበር ይሆናል፡፡ ስለዚህ ተጨማሪ ግፊት እስኪመጣ ድረስ ነገሩን በይደር አቆየው (ሐዋ. 24፡22)፡፡

የፊሊክስ ምላሽ (ሐዋ. 24፡24-27) የእርሱ ባህሪ ምን እንደሚመስል ገልጦ ያሳያል፡፡ ጉዳዩን በይደር አቆየው፤ ጉቦ ይቀበል ነበር፤ እንዲሁም አጋጣሚዎቹን ለራሱ ጥቅም የሚያውል ሰውም ነበር፡፡ ጳውሎስ እንደ ፊሊክስ ባለ ሰው ፍትሐዊ ፍርድ ለማግኘት ጥቂት እድል ብቻ ነበረው፡፡

ሐዋ. 24፡16ን ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ « በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ንጹህ ህሊና እንዲኖረው» ሁልጊዜ እንደሚጥር ተናግሯል ይህን ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህን ተመሳሳይ ነገር ለማለት መለወጥ የሚገባዎ ምን ነገር አለ ብለው ያስባሉ?

## ሰኞ መስከረም 7

## በፊስጦስ ፊት

አይሁዳውያንን ለማስደሰት ሲል ጳውሎስን ለሁለት አመት በእስር ካቆየው በኋላ ፊሊክስ በጶርቅዮስ ፊስጦስ ተተካ (ሐዋ. 24፡27)፡፡ ፊስጦስም ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከ60 እስከ 62 ዓ.ም. ድረስ መራ፡፡

ሐዋ. 25፡1-5ን ያንብቡ፡፡ ይህ እውነትን የሚሰብኩ ሰዎች ያንን ማመን በማይሹ ሰዎች አማካኝነት ስለሚደርስባቸው ጥላቻ እንድንገነዘብ የሚያግዘን እንዴት ነው?

ምናልባትም ፊሊክስ በጳውሎስ እንዲፈርድ ያደረጉት ጥረት ስላልሰመረላቸው መሪዎቹ በድጋሚ ሌላ እድል እንዲያመልጣቸው አልፈለጉም፡፡ ፊስጦስ ወደ ኢየሩሳሌም የመጀመሪያውን ጉብኝት ሲያደርግ አንድ ውለታ እንዲያደርግላቸው ማለትም የቀድሞውን ውሳኔ ቀይሮ ጳውሎስን ለነርሱ መልሶ እንዲሰጣቸውና በአይሁዳውያን ህግ መሰረት በሸንጎው እንዲዳኝ ጠየቁት፡፡

ነገር ግን ጥያቄያቸው የውስጥ ሴራቸውን ማለትም ጳውሎስን ለመግደል ያሰቡትን ኃሳብ ለመደበቅ ብቻ ታስቦ የመጣ ጥያቄ ነበር፡፡ ፊስጦስ ጉዳዩን ደግሞ ለማየት

ፈቃደኛ ቢሆንም ጉዳዩ መታየት ያለበት ኢየሩሳሌም ሳይሆን ቂሳርያ መሆን እንዳለበት ነገራቸው፡፡ ይህም ጳውሎስ የሚዳኘው በሮማውያን ህግ ነው ማለት ነው፡፡
ፊስጦስ ወደ ቂሳርያ እንደተመለሰ የሚመለከታቸውን አስጠርቶ የፍርድ ሂደቱ ተጀመረ፤ የጳውሎስ ባላንጣዎችም በጳውሎስ ላይ ያላቸውን ክስ ማቅረብ ጀመሩ (ሐዋ. 25፡7)፡፡ እዚህ ጋር ሉቃስ ሲተርክልን ስለክሱ ይዘት በድጋሜ አላነሳም፤ ነገር ግን የጳውሎስን ምላሽ መሰረት በማድረግ (ሐዋ. 25፡8) ከሁለት ዓመታት በፊት ያቀረቡትን ተመሳሳዩን ክስ እንዳቀረቡና ጳውሎስ አመጽን ስለሚያነሳሳ ለአገዛዙ ስጋት በመሆኑ ላይ አፅንዖት ስለመስጠታቸው መረዳት ይቻላል፡፡

ሐዋ. 25፡9-12ን ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ ንጉሱ ፊስጦስ በአይሁድ ዘንድ ፖለቲካዊ ድጋፍ ለማግኘት ሊጠቀምበት እንደሚችል ሲረዳ ምን ምላሽ ሰጠ?

________________________________________

________________________________________

በስተመጨረሻ ፊስጦስ በፖለቲካዊ ስትራቴጂው ከፊልክስ እምብዛም ያልተለየ አቋም አሳየ (ሐዋ. 24፡27)፡፡ ጳውሎስ ንጹህ ሰው እንደሆነ በማወጅ ገና ብዙም ሳያስተዳድር የአይሁዳውያንን ድጋፍ ማጣት ስላልፈለገ የመጀመሪያ ጥያቄያቸውን ለማስተናገድ አሰበ፡፡ ይህም ጳውሎስ ኢየሩሳሌም በሚገኘው የአይሁድ ሸንጎ እንዲዳኝ ማድረግ ነበር፡፡

ነገር ግን ይህ ኃሳብ በጳውሎስ ዘንድ ተቀባይነትን አላገኘም፤ ምክንያቱም ፍትሐዊ በሆነ ሁኔታ እንደማይዳኝና ለጠላቶቹ እንደሚሰጥ ስለተረዳ ነው፡፡ ስለዚህ የሮማዊነት መብቱን በማጉላት በሮማውያን ሸንጎ ጉዳዩ እንዲታይ መብት እንዳለውና በዚያ ካልሆነ ከዚህ አስጨናቂ ሁኔታ መውጣት እንደማይቻል በመገመት ወደ ላይኛው የሮም ፍርድ ቤት ማለትም ወደ አገረ ገዥው ይግባኝ አለ፡፡

ማክሰኞ **መስከረም 8**

## በአግሪጳ ፊት

ፊስጦስ ጳውሎስ ሮም ለመዳኘት ያቀረበውን የይግባኝ ጥያቄ ተቀበለ(ሐዋ. 25፡12)፡፡ በዚህ ወቅት ግን ለጉብኝት ወደርሱ የመጣውን ሄሮድስ አግሪፓን(2ኛው) ስለ ጳውሎስ ጉዳይ በተለይም ለሮም ገዢ መላክ ስለሚገባው ኦፊሴላዊ መረጃ ለማማከር ያገኘውን እድል ተጠቀመበት፡፡ ፊስጦስ በአይሁዶች ጉዳይ ብዙም ልምድ አልነበረውም እናም አግሪፓ ሊረዳው ይችል ነበር (ሐዋ. 26፡2-3)

ሐዋ. 25፡13-22ን ያንብቡ፡፡ ፊስጦስ ስለ ጳውሎስ ለአግሪጳ ምን ነገረው? ንጉሱስ ምን ምላሽ ሰጠ?

---

---

የሄሮድሶች የመጨረሻ የነበረው አግሪጳ(2ኛ) ወደ ቂሳሪያ ከእህቱ በርኒቄ ጋር የመጣው አዲስ የተሾመውን አገረ-ገዥ ፊስጦስን እጅ ለመንሳት ነበር፡፡

ፊስጦስ ስለ ጳውሎስ ጉዳይ በዝርዝር ሲያስረዳ ጉዳዩ ከፍተኛ(ትልቅ የሚባል) አለመሆኑ ወይም ከፖለቲካዊም ሆነ ከወንጀል ተግባር ጋር የማይያያዝ መሆኑ እንዳስደነቀው ገለፀ፡፡ ነገር ግን ክሶቹ ስለ አይሁድ ሃይማኖት በተለይም “ሞቶ ስለነበረውና ጳውሎስ ግን ህያው ነው ስለሚለው” ስለ ኢየሱስ ነበሩ(ሐዋ. ሥራ 25፡ 19)፡፡ ጳውሎስ አስቀድሞ በሸንጎው መማከርት ጉባኤ ላይ ለፍርድ የቀረበው በኢየሱስ ትንሳኤ በማመኑ የተነሳ እንደሆነ ገልጧል፡፡ አሁን ደግሞ ፊስጦስ ጉዳዩ በትክክልም ስለዚያ እንደሆነ አረጋገጠ፡፡

ሐዋ. ሥራ 25፡23-27ን ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ በአግሪጳ ፊት ስለቀረበበት ሁኔታ ሉቃስ የተረከው እንዴት ነበር?

---

---

“ጳውሎስ አሁንም በሰንሰለት ታስሮ በጉባኤው ፊት ቆመ፡፡ እዚህ ጋ አስገራሚ ንፅፅር አለ፤ አግሪጳ እና በርኒቄ ስልጣን ስለነበራቸው በአለም ተቀባይነትን አገኙ፡፡ በእግዚአብሔር እይታ ግን ያልተገባ ባህሪ ያላቸው ሰዎች ነበሩ፡፡ ህጉን የሚተላለፉ፤ ልባቸውም ህይወታቸውም የተበላሸ ነበር፡፡ ተግባራቸው በሰማይ ዘንድ አጸያፊ ነበር፡፡” Ellen G. White, The Acts of the Apostles, p. 434

ይህ ታሪክ የውጭ መልክ ለሰዎች አስደሳች ሆኖ ቢታይም ከእይታው በስተጀርባ ስላለው እውነታ ምን ያህል አታላይ ሊሆን እንደሚችል ምን ያስተምረናል? እኛስ ብንሆን እንዴት ነን? ከላይ የሚታየው ማንነታችን ከእውነታው ምን ያህል ይለያል?

**ረቡዕ** **መስከረም 9**

## የጳውሎስ መከላከያ

ከአገረ ገዥው ጎን ከፍተኛ መኮንኖች ተቀምጠው እስረኛው የመከላከያ ነጥቡን እንዲያቀርብ ተደረገ፡፡ ፊስጦስ ጉዳዩን ቀድሞ ስለሰማ በዋናነት አግሪጳ እንዲሰማ ታስቦ ነው ይህ የሆነው (ሐዋ. 25፡8-11)

ሐዋ. 26፡1-23ን ያንብቡ፡፡ በአግሪጳ ፊት ባደረገው ንግግር ጳውሎስ ምን አይነት መንገድን ተጠቀመ?

---

---

በርግጥም ጳውሎስ እየተናገረ የነበረው ከመለወጡ በፊትና ከተለወጠ በኋላ ስለሆነው የራሱ ግለ ታሪክ ነበር፡፡ የንግግሩ ይዘት በኢየሩሳሌም ለተሰበሰበው ህዝብ ያደረገውንና በሐዋ. ሥራ 22፡1-21 የሰፈረውን ንግግር የሚያስታውስ ነው፡፡

ሐዋርያው የአግሪጳን ይሁንታ በሚያረጋግጥለት መንገድ ንግግሩን ጀመረ፡፡ አግሪጳ ስለ አይሁድ ልማዶችና የውስጥ ጉዳዮች ጥሩ እውቀት ስለነበረው በዚያ ታዋቂ ሰው ፊት ጉዳዩን ለማቅረብ እድልን በማግኘቱ ምስጋናውን አቀረበ፡፡ በዚህ ምክንያት አግሪጳ የሮማው መሪ በጳውሎስ ላይ የተነሳው ክስ ሐሰት ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ትልቅ እገዛ ማድረግ የሚችል ሰው ነበር፡፡

ንግግሩም በሶስት ሊከፈል ይችላል፡፡ በመጀመሪያው ክፍል (ሐዋ. 26፡4-11) ጳውሎስ ፈሪሳዊ ስለመሆኑና ስለነበረው ቅናት በኢየሩሳሌም ያሉ በእድሜ አቻው የሆኑ አይሁዳውያንም እንደሚያውቁ ገለፀ፡፡ እንደ ፈሪሳዊነቱ ደግሞ የእስራኤል የዘመናት ተስፋ እንዲፈፀም አስፈላጊ ስለሆነ በሙታን ትንሳኤ ያምናል፡፡ ስለዚህ አይሁዳዊ መሠረት የሌለውን ነገር ስላላስተማረ አይሁዳውያኑ ትምህርቱን ሲቃወሙ ያልፀና አቋም እያሳዩ ነበር፡፡ ኃሳባቸውን በደንብ ተረድቷል፤ ያም በአንድ ወቅት እርሱ ራሱም እግዚአብሔር ኢየሱስን ማስነሳቱ የማይታመን ነገር አድርጎ ከማየቱ የተነሳ ኢየሱስ ተነስቷል ብለው የሚያምኑትን ሰዎች ያሳድድ ስለነበረ ነው፡፡

ሁለተኛው ክፍል (ሐዋ. ሥራ 26፡12-18) ላይ ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ላይ ኢየሱስን ከተገናኘና ለአህዛብ የወንጌልን መልእክት ለማድረስ ጥሪ ከተቀበለ በኋላ አመለካከቱ እንዴት እደተለወጠ ገለፀ፡፡

ጳውሎስ የዚህን ክፍል ንግግር ሲደመድም ያየው ነገር (ሐዋ. ሥራ 26፡19-23) እንዲታዘዝና የወንጌል ማዳረስ ተግባሩን እንዲፈፅም ከማስቻል ውጪ ሌላ አማራጭ እንዳይኖረው ተፅዕኖ እንዳሳደረበት ተናገረ፡፡ ወደ ሸንጎ የቀረበውም በዚህ ምክንያት ነበር፡፡ ስለዚህ ከመታሰሩ በስተጀርባ ያለው ትክክለኛ መንስኤ የአይሁድን ህግ መተላለፍ ወይም ቤተመቅደስን ማርከሱ አልነበረም፡፡ ይልቁንም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጣጣመውንና አማኝ የሆኑ አህዛብ እኩል የድነት መብት አግኝተው እንዲድኑ የሚፈቅደውን የኢየሱስን ሞትና ትንሳኤ በመስበኩ ነበር፡፡

ሐዋ. ሥራ 26፡18ን ያንብቡ፡፡ በዚህ ጥቅስ መሠረት በክርስቶስ ድነትን ባገኙ ሰዎች ላይ ምን ይሆናል? ይህንን እውነታ እርስም የተለማመዱት እንዴት ነው?

## ሐሙስ መስከረም 10

# ጳውሎስ በመሪዎች ፊት

ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ለአግሪጳ ቢሆንም በሐዋ. 26፡24 ላይ የመጀመሪያውን ምላሽ ሲሰጥ የምናገኘው ፊስጦስን ነው፡፡ ፊስጦስ ጳውሎስ ስለ ነፍስ አለመሞት እየተናገረ ቢሆን ኖሮ ግድ አይለውም ነበር፤ ነገር ግን ጥንታዊ የሮም ግሪካውያን እንኳን ሁለቱ እሳቤዎች ማለትም ነፍስ አትሞትምና የሙታን ትንሳኤ አብረው እንደማይሄዱ ያውቃሉ፡፡ ስለዚህ የመጀመሪያውን ተቀብለው ሁለተኛውን ኃሳብ ግን ተዉት፡፡ ጳውሎስ በሌላ ስፍራ ላይ ሲናገር ወንጌል ለአህዛብ ሞኝነት ነው ያለው ለዚህ ነው(1ኛ ቆሮ. 1፡23)፡፡

ጨዋነት በተሞላበት መንገድ ጳውሎስ የሀሳቡን ትክክለኝነት ሊያስተውለውና እየተናገረ ያለው ከዕብራውያን ነብያት ጋር እንደሚስማማ ሊያረጋግጥ ለሚችለው ለአግሪጳ ኃሳቡን አቀረበ (ሐዋ. 26፡25-26)፡፡

ሐዋ. ሥራ 26፡27-28ን ያንብቡ፡፡ ለጳውሎስ ያልተጠበቀ ጥያቄ የአግሪጳ ምላሽ ምን ነበር?

የጳውሎስ ጥያቄ አግሪጳን አጣብቂኝ ውስጥ ከተተው፡፡ እንደ አይሁዳዊነቱ በቅዱስ መጽሐፍ ላይ ያለውን እምነት ሊክድ አይቻለውም፤ በሌላ በኩል ደግሞ አዎንታዊ ምላሽ ልስጥ ቢል ኢየሱስን መሲህ እንደሆነ ከመቀበል ውጪ ሌላ ምርጫ ላይኖረው ነው፡፡ ብልሃት የተሞላበት ምላሹ ግን ከገባበት ወጥመድ አስመልጦታል፡፡ "እንዲህ በቀላሉ ክርስትያን የምታደርገኝ ይመስልሃል?" የሚለው (ሐዋ. 26፡28ን ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ጋር ያነፃፅሩ) ከተለመደው የግሪኩ ትርጉም ማለትም "ክርስትያን ልታደርገኝ ጥቂት ቀረህ" ከሚለው የተሻለ ነው፡፡

የጳውሎስ ምላሽ ለወንጌል ያለውን ቆራጥ የሆነ አቋም ያንፀባረቀ ነበር ‹‹አሁንም ሆነ ወደፊት አንተ ብቻ ስትሆን ዛሬ የሚሰሙኝ ሁሉ ከዚህ ከታሰርኩበት ሰንሰለት በቀር እንደኔ ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔርን እለምናለሁ፡፡›› (ሐዋ. 26፡29) በንግግሩ ማሳረጊያ ላይ ጳውሎስ ሰሚዎቹ ነጻ እንደሆኑት ነፃ ይሆን ዘንድ አልተማፀነም፤ በዚህ ፈንታ ከታሰረበት ሰንሰለት በቀር እንደርሱ ይሆኑ ዘንድ ተመኘ፡፡ የጳውሎስ የወንጌል እንቅስቃሴ ግለት ለራሱ ደህንነት ከመጠንቀቅም ያለፈ ነበር፡፡

ሐዋ. ሥራ 26፡30-32ን ያንብቡ፡፡ አግሪጳ ጳውሎስ ንፁህ እንደሆነ ስለማመኑ የገለፀው እንዴት ነበር?

____________________________________________

____________________________________________

ፊስጦስ የአግሪጳን እርዳታ የፈለገው ሪፖርቱን ሙሉ ለማድረግ ብቻ ነበር (ሐዋ. 25፡ 25-27)፡፡ ጳውሎስ ለቄሳር ይግባኝ ማለቱ ቀድሞውኑ ተቀባይነት አግኝቷል (ሐዋ. 25፡12)፡፡ እስረኛው ጳውሎስ ከዚህ በኋላ በአገረ ገዥው ፍርድ ስር አልነበረም፡፡

ሐዋ. 26፡24-28ን ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ በስተመጨረሻ ይግባኝ ያለው ነገር ምን ነበር? ለእኛስ በእምነታችን የመጨረሻ ስልጣን ሊኖረው ስለሚገባው ነገር ምን ያስተምረናል?

## ዓርብ | መስከረም 11

**ተጨማሪ ጥናት**፡- እነዚያ ቃላት የአግሪጳን ኃሳብ ወደ ቀደሙት የቤተሰቦቹ ታሪክ እና ጳውሎስ እየተናገረለት ያለውን(ኢየሱስን) ለማስቆም ወደ ተደረገው ፍሬ አልባ ጥረት ትውስታ መልሰውት ይሆን? ስለ ቅድመ-አያቱ ሔሮድስና በቤተልሔም ስለተጨፈጨፉት ንፁሀን ጨቅላ ህፃናት አስቦ ይሆን? ስለ አያቱ ወንድም ስለ አንቲጳስና ስለተገደለው መጥምቁ ዮሐንስስ? የራሱ አባት ስለነበረው አግሪጳ(1ኛ)ና

ስለ ሐዋርያው ያዕቆብ ሰማዕትነትስ? በነዚህ ነገስታት ወዲያው የመጡት ጥፋቶች እግዚአብሔር በርሱ አገልጋዮች ላይ በፈፀሙት ወንጀል ያልተደሰተ በመሆኑ ምክንያት የመጡ ስለ መሆናቸው ምልክት ሰጥቶት ይሆን? ይህ በደመቀ አቀባበል የታጀበ ስነ ስርአት በስልጣኑ ከርሱ ከፍ ብሎ ስለነበረውና በአንፀባራቂ ልብስ ስላሸበረቀው በዚያችም ከተማ ህዝቡ አምላክ ነው ብለው ስለጮሁለት ስለአባቱ ሁኔታ አስታውሶት ይሆን? ያ አድናቆት ከማብቃቱ በፊት እጅግ ጉረኛ በሆነው ንጉስ ላይ አስከፊና ፈጣን በቀል እንዴት እንደመጣ ረስቶ ይሆን? እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከአግሪጳ ትውስታ አልጠፉም ነገር ግን በፊቱ የሚታየው አስደናቂ ክስተት አእምሮውን ወሰደ፤ ኩራትና የራስ ክብር ክቡር ኃሳቡን አጠፋበት፡፡” Ellen G. White Comments, The SDA Bible Commentary, vol. 6, pp. 1066, 1067

## *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. በመወያያ ክፍሎቻችሁ ውስጥ ጳውሎስ ለቄሳርያ ይግባኝ ለመጠየቅ ስለ መወሰኑ ጉዳይ ተወያዩ፡፡ ውሳኔው ትክክል ነበርን? (ከሐዋ. 25፡25ና 26፡31-32 ጋር ያነፃፅሩ)? በእግዚአብሔር ጥበቃ ላይ ሙሉ በሙሉ ከመታመን ባለፈ ተገቢ በሆነ መንገድ ብልሃት የተሞላባቸውን ውሳኔዎች መወሰን የምንችለው እስከምን ድረስ ነው?

2. ጳውሎስ ለአግሪጳ የተናገረው ማለትም ‹‹እንግዲህ ንጉስ አግሪጳ ሆይ ከሰማይ ለታየኝ ራዕይ አልታዘዝም አላልኩም›› (ሐዋ. 26፡19) ይህ ስለ ጳውሎስ ምን ይነግረናል? እንደ ክርስትያንነታችን ለተጠራንበት ተልዕኮ ምን ያህል ታማኞች ነን(1 ጴጥ. 2፡9-10)?

3. ጳውሎስ ለሰዎች የጋለ ስሜትና ፍቅር ነበረው፡- ለቁጥር ብዛት ሳይሆን ለራሳቸው ለሰዎቹ፡፡ በቄሳርያ በነበረው የመጨረሻ ክስ ላይ ለአድማጮቹ የእርሱ የልቡ ጥማት ሁሉ እንደርሱ እንዲሆኑ ነበር፤ ያም በእግዚአብሔር ፀጋ እንዲድኑ ነበር (ሐዋ. 26፡29)፡፡ ለራሱ ነጻ መውጣት ወይንም ፍትህን ከመፈለግ ይልቅ እነርሱ የእግዚአብሔርን ማዳን እንዲለማመዱ ፈለገ፡፡ ከዚህ ምሳሌነት ምን የምንማረው ነገር አለ? ወንጌል ይስፋፋ ዘንድ ራሳችንን መስዋዕት ለማድረግ ምን ያህል ፈቃደኞች ነን?

4. አግሪጳ ከጳውሎስ አንደበት ወንጌልን ለመስማት እድልን አገኘ፡፡ ነገር ግን አልተቀበለውም፡፡ እንደዚህ አይነት ታላቅ እድሎች በፊቶቻችን ላይ ሳሉልን ሳያመልጡን በዕድሎቹ መጠቀም ያለብን እንዴት ነው? ማለትም መንፈሳዊነታችንን በዙሪያችን ካለው እውነታ ጋር ማዋሀድ የሚገባን እንዴት ነው?

# ፲፫ኛ ትምህርት ከመስከረም 12 - 18

# ጉዞ ወደ ሮም

ሰንበት ከሰዓት

*ለዚህ ሳምንት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡- የሐዋሪያት ሥራ 27 እና 28፤ ሮሜ 1፡18-20፡፡*

**<u>መታሰቢያ ጥቅስ</u> ፡- ‹‹ጳውሎስ ሆይ አትፍራ፤ በቄሳር ፊት መቆም ይገባሃል፤›› (ሐዋ. 27፡24)**

ጳውሎስ ሮምን የመጎብኘት ከፍተኛ ናፍቆት ነበረው፤ በኢየሩሳሌም መታሰሩ ግን ብዙ ነገሮችን ቀየረ፡፡ በኢየሩሳሌም ቤተክርስትያን ለሚገኙ መሪዎች የህጋዊነት ጫና እጅ ስለሰጠ በባህር ወደ ጣሊያን ያደረገውን ጉዞ ጨምሮ ወደ አምስት አመት ለሚጠጋ ጊዜ በሮም ጥበቃ ስር እንዲቆይ ተደረገ፡፡ ይህ ለውጥ የጳውሎስን ወንጌልን የማዳረስ ጉዞ እቅድ አበላሸበት፡፡

ምንም እንኳን ይህ እንቅፋት ቢገጥመውም ኢየሱስ ራሱ ሐዋሪያው በሮም ቆሞ እንሚመሰክርለት ቃል ገብቶለታል(ሐዋ. 23፡11)፡፡ ተስፋ ብናስቆርጠውም እግዚአብሔር በስራችን ከሚመጣብን መዘዝ ሁልጊዜ ባያተርፈንም እድልን ግን ይሰጠናል፡፡ ጳውሎስ እስረኛ ሆኖ ወደ ሮም መወሰዱ ብቻ ሳይሆን ስፔንን (እስጳንያን) ለመጎብኘት ናፍቆት ቢኖረውም (ሮሜ 15፡24) ወደዚያ ስለመሄዱ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ የለንም፡፡ ከመጀመሪያው የሮም እስራቱ ከተፈታ በኋላ ደግሞ በኔሮ አገዛዝ በ67 ዓ.ም. ታስሮ እንደ ሰማዕት ስቃይ ይደርስበታል(2ኛ ጢሞ. 4፡6-8)፡፡

አዎን ጳውሎስ ወደ ሮም ደረሰ በሰንሰለት ታስሮ በገዥው ፊት ለመቅረብ ቀንን ቢጠብቅም መናገሩን ግን አላቆመም (ኤፌ. 6፡20፤ ፊሊ.1፡13)፡፡ ወደርሱ የመጡትን ሁሉ ያለመከልከል አስተማረ (ሐዋ. ሥራ 28፡30-31)፤ ከመጡት መካከል ከቄሳር ቤተሰብ ጠቃሚ ሰዎችም ነበሩ (ፊሊ. 4፡22)፡፡

የዚህን ሳምንት ትምህርት አጥንተው ለ መስከረም 19 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡

**እሑድ** **መስከረም 13**

## በመርከብ ወደ ሮም መጓዝ

በቂሳርያ ለሁለት አመታት በእስራት ከቆየ በኋላ (ሐዋ. 24፡27) ጳውሎስ ወደ ሮም ተላከ፡፡ እኛ ብሎ በመተረኩና ወደ ኢጣልያ ያደረጉትን ረዥምና አስቸጋሪ ጉዞ በጣም ዝርዝር ባለ ሁኔታ በመግለፁ (ሐዋ.27፡1-28፡16) ሉቃስ ከጳውሎስ ጋር አብሮ እንደነበረ መናገር ይቻላል፡፡ አርስጥሮኮስ የተባለ ክርስትያንም አብሯቸው ነበር (ሐዋ. 27፡2) ፡፡ ሌላው በዚህ ታሪክ ውስጥ የምናገኘው ዋነኛ ገፀባህሪ የመቶ አለቃ የሆነው ዩሊዮስ ሲሆን ከእርሱም ጋር ሌሎች እስረኞችን በሃላፊነት እየወሰደ ነበር (ሐዋ. 27፡ 1)፡፡

ጉዞአቸውን የጀመሩት የበጋ ወቅት በሚገባደድበት ጊዜ ነበር፡፡ የጾም ጊዜ ተብሎ የተገለፀው (ሐዋ. 27፡9) ጊዜው በጥቅምት ወር ሁለተኛ አጋማሽ ውስጥ የሚካሄደው የመንጻት ቀን አካባቢ እንደነበረ የሚያመላክት ነው፡፡ የክረምት ወቅት እየጀመረ ስለነበረ ከህዳር እስከ መጋቢት ባለው ጊዜ ውስጥ የሚዴትራኒያን ባህር ላይ መጓዝ የማይታሰብ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ግን ከጅማሬው አንስቶ እክል ገጠማቸው፡፡ በቀርጤስ ውስጥ መልካም ወደብ ወደተባለችው ደሴት የደረሱት ብዙ ቆይተው ነበር (ሐዋ. 27፡8)፡፡

ሐዋ. 27፡9-12ን ያንብቡ፡፡ ወደ መልካም ወደበ እንደደረሱ ጳውሎስ በታሪኩ ውስጥ ጣልቃ ገብቶ የምናገኘው እንዴት ነው? እርሱ ጣልቃ ገብቶ በመናገሩ ምን ምላሽ አገኘ?

---

---

የጳውሎስን ምክር ባለመስማት ማረፊያ ወደብን በመፈለግ በምዕራብ አቅጣጫ 40 ማይል ያክል በመርከብ ለመሔድ ወሰኑ፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ የአየር ሁኔታው ድንገት ተቀየረና የመርከቧ መሪዎች መርከቧ ከመሬት ርቃ ወደ ደቡብ ምዕራብ እንድትጓዝ ከመፍቀድ ውጪ ምርጫ እስኪያጡ ድረስ በሃይለኛ ማዕበል ተያዙ፡፡ ቀጥለውም ውሃ ወደ መርከቧ እየገባ ስለነበረ ክብደቱን ለማቅለል ጭነቶቿን እንዲሁም የሸራ ማውጫና ማውረጃ መሣሪያውን ነቃቅለው ወደ ባህር መጣል ጀመሩ፡፡ ሁኔታው ድራማ ይመስል ነበር፡፡ ለብዙ ቀናት አነስተኛ የቀን ብርሃን በነበረበት ሁኔታ፣ በከባድ ዝናብና ወጀብ እየተናወጡ፣ የት እንደደረሱ እንኳን ሳያውቁ እጅግ በመዛላቸው "ለመትረፍ የነበራቸው ተስፋ ተሟጠጠ" (ሐዋ. ሥራ 27፡20) ፡፡

ሐዋ. ሥራ 27፡21-26ን ያንብቡ፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ ጳውሎስ ለሁለተኛ ጊዜ ጣልቃ ሲገባ ምን አለ?

---

---

ትንቢታዊ በሆኑ ቃላት ጳውሎስ ለመርከቡ መሪዎች ከእግዚአብሔር የተቀበለውን መልእክት ተናገረ፡፡ "ተስፋ ልትቆርጡና ልታዝኑ አይገባም፡፡ አሁንም ቢሆን አደጋና ችግር ይመጣል፤ ነገር ግን ሁላችሁም በሕይወት ትተርፋላችሁ" አላቸው፡፡

እንደጳውሎስ ያለ ታማኝና የተሰጠ አገልጋይ ለምን ተብሎ ነው ይህ ሁሉ አበሳ የደረሰበት? ከዚህ የህይወት ልምምዱ ምን የምንማረው ነገር አለ?

**ሰኞ** **መስከረም 14**

## የመርከቡ መሰባበር

በታሪኩ ላይ ጳውሎስ ለሁለተኛ ጊዜ ጣልቃ ገብቶ ሲናገር በመርከቡ ላይ ለሚገኙ 276 ሰዎች በሙሉ (ሐዋ. ሥራ 27፡37) ከዚያ በኋላ ነገሮች መልካም እንደሆኑ ባይቀጥሉም የሚሞት ሰው እንደማይኖርና መርከቧ ብቻ ጉዳት እንደሚደርስባት (ሐዋ. ሥራ 27፡22) አረጋገጠላቸው፡፡ ከአስራ አራት ቀናት በኋላ የሐዋሪያው ቃል ተፈጸመ፡፡ አሁንም ከባድ ማዕበል ገጥሟቸው መርከቧ ብትዋልልም ምናልባትም ውሃው ከድንጋይ(ከመሬት) ጋር ተጋጭቶ አረፋ ሲደፍቅ ስለሰሙ መርከበኞቹ ወደ መሬት የተቃረቡ መሰላቸው (ሐዋ. 27፡27) ፡፡ ከብዙ ድምፆች በኋላ መርከቡ ከቋጥኝ ጋር ይላተማል ብለው ስለሰጉ ከመርከቡ ጀርባ አራት መልህቆችን በመወርወር የመርከቢቱን ፍጥነት ለመቀነስ ጣሩ፡፡ አምላካቸውም የቀን ብርሃን እንዲሰጣቸው ለመኑ (ሐዋ. 27፡28-29) ፡፡

ሐዋ. ሥራ 27፡30-44ን ያንብቡ፡፡ ከዚህ ታሪክ የምንማረው ትምህርት ምንድነው?

---

---

በጉዟቸው መነሻ ላይ የመቶ አለቃው ጳውሎስን በጥሩ መንገድ ቢያስተናገደውም በጉዟቸው መካከል ላይ ወደፊት ስለሚገጥማቸው የነገረውን ንግግር ለማመን አልደፈረም፡፡ ከሁለት ሳምንት በኋላ ግን ነገሮች ተለወጡ፡፡ ስለ መርከቢቱ መሰበር ጳውሎስ የተናገረው ትንቢታዊ ንግግር በመቶ አለቃው ተሰሚነትን አገኘ (ሐዋ. 27፡21-26) ፤ ያም ሊፈፀም ቀርቦ ነበር፡፡

ጳውሎስ ሰዎቹን ምግብ እንዲበሉ ተማፀናቸው፤ ያ ካልሆነ ግን ለመዋኘትና ወደ ዳር ለመድረስ አቅም እንደማያገኙ ነገራቸው:: የመለኮት ሁኔታዎችን ማመቻቸት የእኛን የየእለት ተግባር እንዳናከናውን አያግድም:: "በዚህ ትረካ ውስጥ እግዚአብሔር ደህና እንደሚሆኑ በማረጋገጡና ሰዎቹም ይህ እንዲረጋገጥ ባደረጉት ጥረት መካከል መልካም የሆነ ሚዛናዊነት አለ" David J. Williams, Acts (Grand Rapids: Baker, 1990), p. 438

ማለዳው እየተቃረበ ሲመጣ መርከበኞቹ ዳር ዳሩ አሸዋማ የሆነ የባህር ሰርጥን አይተው መርከቢቱን ገፍተው ወደዚያ ለማድረስ ወሰኑ:: መርከቢቱ ግን ወደዛ የውሃ ዳርቻ ለመድረስ አልተቻላትም:: በዚህ ፈንታ ግን በአሸዋ ስትታነቅ በማዕበሉ ሀይል የተነሳ መርከቢቷ ተሰባበረች:: ወታደሮቹም እስረኞች እንዳያመልጧቸው በመስጋት ሊገድሏቸው ሲያስቡ መቶ አለቃው በዋነኝነት ጳውሎስ እንዲተርፍ ስለፈለገ ከለከላቸው:: በስተመጨረሻም እግዚአብሔር ቃል እንደገባላቸው አንዲትም ነፍስ አልጠፋችም::

ጳውሎስን በህይወት ለማትረፍ ሲባል ወታደሮቹ እስረኞችን ከመግደል ተከልክለዋል:: ይህ ስለ ጳውሎስ የምስክርነት ኃይል እና ባህሪ የሚያስተምረን ምን ነገር አለ?

## ማክሰኞ መስከረም 15

### በመላጥያ

በህይወት ተርፈው ወደ ዳርቻው ሲደርሱ ነበር በሜዴትራኒያን ባህር ከሲሲሊ በስተ ደቡብ በምትገኘው መላጥያ በምትባለው ትንሽ ደሴት መድረሳቸውን ያወቁት:: በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ በነፋሱ ኃይል አማካኝነት በባህሩ ላይ ከወዲያ ወዲህ እየዋለሉ ከመልካም ወደብ አንስቶ አራት መቶ ሰባ አምስት ማይል የሚያክል ርቀት ተጓዙ:: አሁን ጉዟቸውን ከመቀጠላቸው በፊት የክረምቱን ሶስት ወራት መጠበቅ ነበረባቸው (ሐዋ. 28፡11)

ሐዋ.28፡1-10ን ያንብቡ:: በመላጥያ ደሴት ጳውሎስ ምን ገጠመው? እግዚአብሔርስ እንዴት አድርጎ ተጠቀመበት?

---

---

የመላጥያ ሰዎች በጣም ደግና ጥሩ አቀባበል ማድረግ የሚያውቁ ሰዎች ነበሩ፤ ስለዚህም ለጳውሎስና አብረውት ለነበሩት ሰዎች በስብሰውና በርደኂቸው ስለነበር አንዲሞቃቸው እሳት አነደዱላቸው:: በዚህ ወቅት በመላጥያ የሚኖረው የሙቀት መጠን ከ50 ዲግሪ ፋራናይት አይበልጥም ነበር::

የእፉኝት እባብዋ ሁኔታ ሰዎች ትኩረታቸውን በጳውሎስ ላይ እንዲያደርጉ አደረጋቸው፡ ፡ በመጀመሪያ እነዚህ እግዚአብሔርን የማያምኑ ህዝቦች የተነደፈው እግዚአብሔር ስለተቆጣው እንደሆነ አስበው ነበር፡፡ ጳውሎስ ነፍሰ ገዳይ የነበረና መርከቢቱ ስትሰጥም ከሞት ቢያመልጥም ከግሪክ አማልክት የፍትህና የበቀል አምላክ በሆነችው «ዳይክ» በተባለችው አምላክ የተያዘ መሰላቸው፡፡ ሐዋሪያው ግን ሊሞት ባለመቻሉ ከብዙ አመታት በፊት በልስጥራ እንደሆነው እንደ አምላክ ተቆጠረ (ሐዋ. 14፡8-18) ፡ ፡ ምንም እንኳን ሉቃስ በዚህ ክፍል ላይ ትኩረት አድርጎ የበለጠ ነገር ባይጽፍልንም ጳውሎስ ግን ይህንን ክስተት እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም ስለሚያገለግለው አምላክ እንደ መሰከረ መገመት አይከብድም፡፡

ፑፕሊዮስ በሮማውያን የተሾመ ይሁን ወይንም የአካባቢው ባለስልጣን ባናውቅም ጳውሎስና ጓደኞቹ ለረጅም ጊዜ የሚቆዩበት ስፍራ እስኪያገኙ ድረስ ለ3ቀናት አስተናገዳቸው፡፡ የዚህ ሰው አባት ፈውስ ደግሞ ለጳውሎስ በመላጥያ ህዝቦች መካከል የፈውስ አገልግሎቱን እንዲያከናውን እድልን ፈጠረለት፡፡

እንደ ሉቃስ አገላለጽ ከሆነ አንድም ሰው ስለ መለወጡ ወይንም ጳውሎስ የመላጥያን ደሴት ተለይቶ ሲሄድ ትቶ ስለሄደው ህብረት አይነግረንም፡፡ ይህ ያልተፃፈው በአጋጣሚ ሊሆን ቢችልም ለአለም ያለን ተልዕኮ ግን ከጥምቀት ወይንም ቤተክርስቲያንን ከማቋቋም የዘለለ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ ስለ ሰዎችና ስለ ፍላጎቶቻቸው ጭምር ግድ ሊለን ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ የወንጌል ተግባራዊ ገፅታ ነው (ሐዋ. 20፡35ን ከቲቶ 3፡14 ጋር ያነጻፅሩ) ፡፡

እነዚህ ምንም አያውቁም የምንላቸው የደሴቱ ነዋሪዎች እንኳን ስለ መለኮት ፍትህ ያላቸው መረዳት በጣም አስደናቂ ነው፡፡ ይህ ከምን የመጣ ይመስሎታል? ሮሜ 1፡ 18-20ን ይመልከቱ፡፡

| ረቡዕ | መስከረም 16 |
|---|---|

## በስተመጨረሻ ጳውሎስ በሮም

ለ3 ወራት በመላጥያ ከቆዩ በኋላ ጳውሎስና አብረውት ያሉ ሰዎች ጉዞአቸውን ቀጠሉ (ሐዋ. 28፡11)፡፡ ወደ ፑቲዮሎስ ማለትም ዛሬ በኔፓል ባህረ ሰላጤ ፖዙሊ በምትባል ቦታ ደረሱ(ሐዋ. 28፡13)፡፡ ከዚህ ተነስተው በእግር መንገድ ወደ ሮም ተጓዙ (ሐዋ. 28፡11-16ን ይመልከቱ) ፡፡

የጳውሎስ የመምጣቱ ዜና በፍጥነት ወደ ሮም ደረሰ፤ የአማኞች ቡድን ከዚያ ተነስተው ወደ ደቡብ ብዙ ኪሎ ሜትሮችን ተጉዘው ጳውሎስን ለመቀበል ሄዱ፡፡ ከዚህ በፊት

ወደ ሮም የመጣ ባይሆንም ሐዋሪያው ግን በዚያች ከተማ አያሌ ወዳጆች፣ የስራ ባልደረቦች፣ የተለወጡ አማኞች፤ ዘመዶችና ሌሎች ቅርብ የሆኑ ሰዎች ነበሩት (ሮሜ 16፡3-16)፡፡ ጳውሎስ እስረኛ ሆኖ መምጣቱ ከመርከብ አደጋ ከመትረፉ ጋር ተደምሮ በአፍዮስ የተጓዙት መንገድ ልብ የሚነካ እንደነበር መገመት ይቻላል፡፡ ከተወደዱት ወዳጆች ካገኘው ልዩ የሆነ ፍቅርና እንክብካቤ የተነሳ ሐዋሪያው እግዚአብሔርን አመሰገነ፡፡ በገዥው ፊት ለፍርድ ሊቀርብ መሆኑን አስቦም ልቡ ተነካ፡፡

ህጋዊ በሆነ ደብዳቤው ውስጥ ፊስጦስ በሮማውያን ህግ መሠረት ጳውሎስ ምንም አይነት ወንጀል እንዳልፈፀመ ተናግሯል ተብሎ ይገመታል (ሐዋ. 25፡26-27፤26፡31-32) ፡፡ ምናልባትም እንደ ሮማውያን ልማድ በሰንሰለት ታስሮ ከወታደር ጋር ቢቆይም በእስር ቤት ወይም በጦር ሰፈር ከመቆየት ይልቅ የግል መኖርያ ተከራይቶ እንዲኖር የተፈቀደለት ለዚህ ይሆናል(ሐዋ. 28፡30)፡፡ ጳውሎስ ራሱ ቤቱን መከራየቱ የራሱን ስራ መስራትን እንደቀጠለ ፍንጭ ይሰጣል(ሐዋ.18፡3)፡፡

*ሐዋ. ሥራ 28፡17-22ን ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ በዛ ስፍራ ደርሶ እንዳረፈ ወዲያውኑ ያደረገው ምን ነበር?*

---

---

ጳውሎስ ወደ ምኩራብ መሄድ ባይችልም ምኩራቡ ግን ወደርሱ መምጣት ይችላል፡፡ ወድያው እንደ ደረሰ ቅድሚያ አይሁዶችን የማናገር ፓሊሲውን በመከተል(ሮሜ1፡16) የአካባቢውን የአይሁድ መሪዎች በአንድ ላይ ሰብስቦ ንፁህ ስለመሆኑና

ያለምክንያት እንደታሰረ በመግለፅ እርሱ የተናገረው ስለ እስራኤል ተስፋ ብቻ እንደነበር ገለጻላቸው(ሐዋ. 23፡6፤24፡15፤26፡6-8)፡፡ የርሱ የውስጥ ፍላጎት ራሱን መከላከል ሳይሆን ወንጌልን እንዲሰብክ በእነርሱ ዘንድ አመኔታን እንዲያመጣለት በማድረግ የኢየሱስ ትንሳኤ የእስራኤሎች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ተስፋ ፍጻሜ ስለመሆኑ ለመመስከር ነበር፡፡ ከኢየሩሳሌም ስለ ጳውሎስ የሰሙት ምንም ነገር አለመኖሩ ደንቋቸው አይሁዶቹ ከእርሱ መስማት ፈለጉ፡፡

*ሐዋ. ሥራ 28፡22ን ያንብቡ፡፡ በዚያ ጊዜም ቢሆን አማኞች ይገጥማቸው ስለነበረው ተቃውሞ ጥቅሱ ምን ይነግረናል? ሌሎች የኛን እምነት ተቃውመው ሲናገሩ እንኳን ታማኝ ሆነን መቆም የምንችለው እንዴት ነው?*

ሐሙስ                    መስከረም 17

## የወንጌል ድል አድራጊነት

በተቀጠረው ቀን አያሌ አይሁዳውያን የጳውሎስን የወንጌል ገለጻ ለመስማት መጡ (ሐዋ. ሥራ 28፡23)

ሐዋ. ሥራ 28፡24-31ን ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ የኢሳያስን ጥቅስ ለራሱ የንግግር አውድ የተጠቀመበት አላማ ምን ነበር?

---

---

ከኢሳ. 6፡9-10 የተወሰደው ኃሳብ ሰዎች የመለኮትን መልዕክት እንቢ ሲሉ ስለሚደርስባቸው ነገር ይገልጻል፡፡ አንዳንድ አይሁዶች ቢያምኑም ሌሎቹ ግን አላመኑም፤ በዚህም ክርክር በመፈጠሩ ምክንያት ሐዋሪያው አሁንም ፊቱን ወደ አህዛብ ከማዞር ውጪ ሌላ አማራጭ አልነበረውም (ሐዋ.13፡46-47፤18፡6)፡፡

ጳውሎስ በገዥው ፊት ለመቅረብ ሁለት አመት ሙሉ መጠበቅ ነበረበት፡፡ ምንም እንኳን በቤቱ የቁም እስረኛ ቢሆንም ወደርሱ ለሚመጡት ሰዎች ያለመከልከል ወንጌልን ያካፍል ነበር፡፡ የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ የመጨረሻው ትዕይንት የሚያውጠነጥነው በወንጌል ድል አድራጊነት ዙሪያ ነው፡፡ ምንም አይነት ኃይል አይሁዶችም ቢሆኑ ሮማውያን የወንጌሉን መስፋት ሊገቱ አልቻሉም፡፡

አንዳንድ መረጃዎች የጳውሎስ ጉዳይ ጠንካራ ማስረጃ ባለመገኘቱ ከእስር መለቀቁንና ሌላ የሚሽነሪ ጉዞ ማድረጉን ከዚያም በድጋሚ ተይዞ ወደ ሮም ተወስዶ መገደሉን (2ኛ ጢሞ. 4፡6-8) ስለሚጠቁሙ ሉቃስ የመጽሐፍ ትረካውን በዚህ ስፍራ ላይ ለምን እንዳበቃ ግልጽ አይደለም፡፡ ምናልባትም ከሉቃስ የጽሁፍ አላማ አንጻር ሩቅ በሆነቸው ሮም ሳይቀር ወንጌሉ በመሰበኩ «እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ»(ሐዋ. 1፡8) የሚለው ቃል በመፈፀሙ ሊሆን ይችላል፡፡ «ጳውሎስ ለረጅም ጊዜ ኢ-ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በእስር ሲቆይ በትዕግስትና በደስታ ነበር፤ ድፍረትና እምነቱም ቀጣይነት ያለው ስብከት ነበር፡፡ ይህም በአለም ላይ ካለው መንፈስ በተቃራኒ ከሁሉ በላይ የሆነው መንፈስ ከእርሱ ጋር እንደነበረ የሚመሰክር ነው፡፡ የርሱ ምሳሌነት እርሱ በህዝብ ፊት ለክርስቶስ መቆም ባይችልም ክርስትያኖች በበለጠ ብርታት ያንን እንዲያደርጉ አነሳስቷቸዋል፡፡ የሐዋሪያው ተፅዕኖ ይሄን ያክል ጠንካራ ነበር፤ በአይን ሲታይ የርሱ አቅምና ፋይዳ የደበዘዘ ቢመስልም የተወገደ

ከመሰለባቸው ማሳዎች እንኳን ብዙ የነፍሳት ነዶዎችን ለክርስቶስ ማርኮ አመጣ፡፡» Ellen G. white, The Acts of the Apostle, P.464

ከቤተክርስትያን ተልእኮ አንፃር የሐዋሪያት ስራ መጽሐፍ ወይንም ወንጌልን የማዳረስ ታሪክ ገና አልተጨረሰም፤ እያንዳንዳችን ወደዚህ ምስል የምንገባው እዚህጋ ነው፡፡ በምዕተ አመታት ታሪክ ውስጥ አያሌ አስደናቂና ድራማዊ የሆኑ ምዕራፎች አንዳንዴም ለእግዚአብሔር ታማኝ በሆኑ ምስክሮቹ ደም ጭምር ተፅፈዋል፡፡ አንድ ተጨማሪ ምዕራፍ ለመጻፍ አሁን ተራው የኛ ነው፤ ምናልባትም የመጨረሻው ምዕራፍ ይሆናል (ብለን ተስፋ እናደርጋለን)፡፡ የሱስ ለደቀመዛሙርቱ ትቶላቸው የሄደውን ተልዕኮ ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ተራው የኛ ነው «ከዚያም መጨረሻው ይመጣል» (ማቴ. 24፡14)

## ዓርብ | መስከረም 18

**ተጨማሪ ጥናት**፡- «ክርስቶስ ለቤተክርስትያን የተቀደሰ ሃላፊነትን ሰጥቷታል፡፡ እያንዳንዱ አባል እግዚአብሔር ለአለም የፀጋ ገፀ በረከቱንና ሊደረስበት የማይችለውን የክርስቶስን ብልጽግና የሚያስተላልፍባቸው የመተላለፊያ መሳሪያ ሊሆን ይገባል፡፡ አዳኛችን የሚሻው ትልቁ ነገር ቢኖር የእርሱ ወኪሎች የሆኑ ሁሉ የእርሱን መንፈስና ባህሪ ያንፀባርቁ ዘንድ ነው፡፡ የአዳኛችው ፍቅር በሰብአዊ ፍጡራት ላይ ተገልጦ የማየትን ያህል ይህ አለም የሚናፍቀው ነገር የለም፡፡ የክርስትና ኃይል የሚገለጥባቸውን ወንድና ሴቶች ሰማይ በናፍቆት ይጠብቃል፡፡» Ellen G. White, The Acts of the Apostles, p. 600

«የአገልግሎት መንፈስ ቤተክርስትያኒቱን ሁሉ ተቆጣጥሮ ሁሉም እንደችሎታው ለእርሱ ስራ ይተጋ ዘንድ እግዚአብሔር ይናፍቃል፡፡ የእግዚአብሔር ቤተክርስትያን አባላት ሁሉ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ጉድለት በሚታይባቸው ቦታዎች ሁሉ የተሰጣቸውን ሥራ በመስራት የወንጌልን ተልእኮ ሲፈጽሙ መላው አለም ማስጠንቀቂያው ይደርሰዋል፤ ጌታ የሱስ በኃይልና በታላቅ ክብር ወደ ምድር ይመለሳል» page 111

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ ወደ ሮም ባደረገው ጉዞ ሁሉ ውስጥ በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን እምነት ሉቃስ የገለፀው እንዴት ነው? በዚህ በሁኔታ ላይ ባልተመሰረተ ጠንካራ እምነት ሌሎቹ ሰዎች ተጽእኖ የተፈጠረባቸው እንዴት ነበረ?

2. ምንም ብዙ ነገሮች ቢያጋጥሙትም ጳውሎስ እምነቱንና ተልእኮውን አልተወም፡ ፡ በሮም የተሰጠው ነፃነት ውሱን ቢሆንም መስበኩን አላቋረጠም፡፡ ለአንድ ሰው ወንጌሉን ልንናገር ስንል እንድናቆም ስንፈተን ምን ማድረግ ይኖርብናል?

3. ሮሜ 1፡14-15ን ያንብቡ፡፡ ጳውሎስ ለሰው ሁሉ ወንጌልን የመስበክ ግዴታ እንዳለበትና ባለ እዳ እንደሆነ የተሰማው ለምንድነው? ታዲያ እኛ ከርሱ ያነሰ ግዴታ ነው ያለብን? ይህንን አባባል ያስቡበት “ክርስቶስን የሚያምን ሰው ሁሉ ነፍሳትን ማዳን የህይወት ሙሉ ስራው ሊሆን ይገባል፡፡ ከእግዚአብሔር የተሰጠንን ፀጋ፣ በእኛ ላይ የበራውን ብርሃንና የተገለጠውን ውብና ኃያል የሆነ እውነት ለመላው አለም ለማካፈል ባለ እዳዎች ነን” Ellen G. white, Testimonies for The church, vol, 4,53

4. ጳውሎስ የጠቀሰውን የኢሳያስ መጽሐፍ ክፍል ደግመው ያንብቡ፡፡ ይህ ኃሳብ እኛን የሚመለከተው እንዴት ነው? አዎን ትልቅ የሆነ እውነት ተሰጥቶናል፤ ነገር ግን ለዚህ እውነት ልባችን ጠጣር ከሆነና ከእኛ መሻትና ፍላጎት ጋር የሚጣረስ ከሆነ በመንፈሳዊነታችን ላይ የሚገጥመን አደጋ ምንድነው?

5. ጳውሎስን ለመጠበቅ ከርሱ ጋር ራሳችሁን ያሰራችሁ ወታደር አድርጋችሁ ራሳችሁን አስቡ፡፡ በቅርበት አብሮት ታስሮ ስለነበረው ሰው ምን የሚመለከት ይመስላችኃል?